# አህባሽ ማን ነው? ምንድነው?




ኡባህ አብዱሰላም ሰኢድ

ዙልቂዳህ 1432 ዓ.ሂ.

(ጥቅምት 2004 ዓ.ል.)

# አህባሽ ማን ነው? ምንድነው?




ኡባህ አብዱሰላም ሰኢድ

ዙልቂዳህ 1433 ዓ.ሂ

ጥቅምት 2004 ዓ.ል.

ማውጫ

አርእስት ገጽ

መግቢያ..... 4

ክፍል አንድ: "አህባሽ"- አጠቃላይ ዳሰሳ..... 7

ክፍል ሁለት: አህባሽና የአቂዳ ብክለት..... 11

ክፍል ሶስት፡ አህባሾች ሌት ተቀን የሚታገሉለት ዓላማ..... 16

ክፍል አራት፡ የአህባሽና የኢብን ተይሚያህ ግብግብ ..... 21

ክፍል አምስት፡ የአህባሽ መሰረታዊ ጠላቶች ..... 27

ክፍል ስድስት፡ የአህባሽ ልባዊ ወዳጆች ..... 31

ክፍል ሰባት፡ አህባሽ እና "ሱፊ" ..... 37

ክፍል ስምንት፡ "አህባሽ" እና "የአላህ አውሊያ"..... 44

ክፍል ዘጠኝ፡ አህባሽ እና "ሺዓ"..... 50

ክፍል አስር፡ በ"አህባሽ" ጥመት ላይ ሙስሊሞች ምን ይላሉ? ..... 54

ክፍል አስራ አንድ፡ "አህባሽ"፣ "ወሃቢያ" እና "የብሪታኒያው ሰላይ" ..... 57

ክፍል አስራ ሁለት፡ "አህባሽ፣ ቱርክና የ"ወሀቢያ ተረት"..... 62

ክፍል አስራ ሶስት፡ አራቱ አህባሾች..... 69

ክፍል አስራ አራት፡ የአህባሽ የሰበካ ስልቶችና የጥቃት ዒላማዎች..... 73

ክፍል አስራ አምስት፡ የኑፋቄ እና የጥመት ፊርቃዎች ከ"ሙርጂዓ" እስከ "አል-አህባሽ" ..... 77

ክፍል አስራ ስድስት፡ "አል-አህባሽ"ና ዘመናዊ የጥመት ፊርቃዎች..... 83

ክፍል አስራ ሰባት፡ "አህባሽ" እና የሙስሊሙ አንድነት..... 87

ከጥቂት ወራት ወዲህ "አህባሽ" የሚባለው ጀመዓ (አንጃ) የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች የመወያያ አጀንዳ ሆኗል። አንጃው የተለየ የእምነት ፍልስፍና በመያዙ አይደለም ትኩረትን የሳበው። የጡዘቱ መነሻ የወቅቱ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ሹማምንት የሁሉም ሙስሊሞች ተወካይ መሆናቸውን ከቁም ነገር ሳያስገቡት በዓለም ዙሪያ በኑፋቄ (heresy) እና ጥመት (deviation) የተወገዘው የአህባሽ ጀመዓ የእምነት ፍልስፍና በኢትዮጵያ ውስጥ የወደፊቱ ብቸኛ የእስልምና አቅጣጫ እንዲሆን በማድረግ ተግባር ላይ ተጠምደው መታየታቸው ነው። ይህንን ጉዳይ እጅግ አነጋጋሪ ያደረገው ደግሞ "አህባሽ"ን የማንገስ እቅዱ መጅሊሱ በልዩ ልዩ መድረኮች በምክንያትነት ከሚያቀርበውና "የሀይማኖት ጽንፈኝነትን መዋጋት አለብን" ከሚለው ሀሳብ ጋር በጭራሽ የማይገናኝ መሆኑ ነው።

የሀይማኖት ጽንፈኝነት በየትኛውም እምነት ውስጥ ሊከሰት ይችላል። "ለእስልምና ነው የምንታገለው" እያሉ የራሳቸውን ድብቅ አጀንዳ የሚያራምዱ ሀይሎች ሊኖሩ ይችላል። እንዲህ አይነት ሰዎች በሌሎችም እምነቶች ውስጥ አሉ። ለዚህ መድሀኒቱ የሁሉም እምነት ተከታዮች ጽንፈኝነትን እንዲያወግዙ ማስተማርና በጽንፈኝት ተነሳስተው ወንጀል የሚሰሩ ሀይሎችን ከመንግስት ጋር ሆነው እንዲከላከሉ መቀስቀስ ነው። ከክርስቲያን ወንድሞቻቸውና ከሌሎችም ወገኖች ጋር ለሺህ ዓመታት ተቻችለው የኖሩት ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጽንፈኝነትን እንዲዋጉ ማነሳሳቱ ደግሞ በጣም ቀላል ነው። ኢስላም ጽንፈኝነትን የሚያወግዝ እምነት ነው።

የመጅሊስ ሹማምንት ግን ይህንን በማድረግ ፈንታ አህባሽን በኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጫንቃ ላይ ለመጫን ነው የተነሱት። አንጃው ከኢስላም መንገድ ያፈነገጠ መሆኑ በተለያዩ መንገዶች ቢገለጽላቸውም *"እሱባልታ እየነዛችሁ ነው፤ አህባሽ የሚያስተምረው ትምህርት ለሀገራችን ሙስሊሞች በጣም አስፈላጊ ነው"* በሚል ጀብደኝነት አንጃውን በሙስሊሞች ላይ ለማንገስ የሚያደርጉትን ሩጫ ገፍተውበታል። ለወደፊቱ በሀገራችን መስጂዶችና መድረሳዎች በይፋ የሚሰበከው የአህባሽ ፍልስፍና ብቻ እንደሚሆንም እየሰማን ነው። በዚህም የተነሳ ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በከፍተኛ ስጋት ውስጥ ወድቀዋል።

የመጅሊሱ አካሄድ ወዴት እንደሚያደርሰን አላህ (ሱ.ወ) ብቻ ነው የሚያውቀው። ሆኖም ብዙሃኑ ሙስሊም ኡለማ፤ ምሁራንና ፀሀፍት "መጅሊሱ "እምነታቻችሁን ቀይሩ" የሚል ምርጫ እያቀረበልን ነው" የሚል ሀሳብ በማስተጋባት ላይ ነው ያሉት። ይህንንም ባለፉት ጥቂት ወራት

በወጡት የፕሬስ ውጤቶችና በኢንተርኔት መረቦች ላይ ከቀረቡ ጽሁፎች መረዳት ይቻላል።

እነዚህ ምሁራን በጽሁፎቻቸው በአመዛኙ በሁለት ነገሮች ላይ ነው ያተኮሩት። አንደኛው መጅሊሱ አህባሽን በህዝቡ ላይ ለመጫን የሚያደርገው ሩጫ ሙስሊሞች በህገ-መንግስቱ የተጎናጸፉትን የእምነት ነጻነት መብታቸውን የሚጋፋ መሆኑ ነው። ሁለተኛው መጅሊሱ እንደ ቅዱስ ነገር የሚከራከርለት የአህባሽ ፍልስፍና ከትክክለኛው የሙስሊሞች ስነ-መለኮት መስመር የወጣና በኑፋቄ የተሞላ እንደሆነ ለመላው ሙስሊሞች ማስረዳት ነው።

የዚህ መጽሀፍ አዘጋጅም ኢትዮጵያዊት ሙስሊም እንደመሆኗ የተወለደችበትን ህብረተሰብ ያጋጠመው ከባድ ፈተና በእጅጉ ያሳስባታል። በመሆኑም በርካታ ሙስሊሞች እያደረጉት ባለው ህዝቡን የማንቃት እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ሊኖረኝ ይገባል በሚል ስሜት "ፌስቡክ" በተሰኘው የኢንተርኔት ማህበራዊ ድረ-ገጽ ላይ አንዳንድ ጽሁፎችን ስትጽፍ ቆይታለች። የርሷ ጽሁፎች ያተኮሩትም "አህባሽ" የተባለውን አንጃ የእምነት ፍልስፍናዎች፤ ድብቅ ፍላጎቶች፤ የኑፋቄ ርእዮቶች፤ የማምታቻ ዘዴዎች ወዘተ... በማስረዳቱ ላይ ነው። ከነዚያ ጽሁፎች መካከልም ***"አህባሽ ማን ነው ምንድነው? በሚል ርእስ ሰር?"*** ከመስከረም 15 እስከ ጥቅምት 5/ 2004 ዓ.ል. ድረስ በተከታታይ ያቀረበቻቸውን ጽሁፎች በዚህ መጽሀፍ አሰባስባ ለአንባቢያን አቅርባለች።

በዚህ መጽሀፍ የተሰባሰቡት ጽሁፎች በፌስቡክ ከተነበቡበት አቀራረብና ይዘት ብዙም አልተቀየሩም። አዘጋጇ ጽሁፎቹን ስትጽፍ እንደ መነሻ የተጠቀመችው ከልዩ ልዩ የአህባሽ ጀመዓ አባላት ጋር ባላት የዝምድናና የጉርብትና ትውውቅ ባደረገቻቸው ውይይቶች ያገኘቻቸው መረጃዎች፤ በአህባሽ የማስተማሪያ ማእከላት በመገኘት የተከታተለቻቸው ዲስኩሮች (lectures) እና ከአስተማሪዎቻቸው ጋር ያደረገቻቸው ክርክሮች፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች ያነበበቻቸው የአህባሽ የማስተማሪያ መጽሀፍትና በራሪ ወረቀቶች፤ ከአህባሽ ድረ-ገጾች ያሰባሰበቻቸው መረጃዎች ወዘተ... ናቸው። የአህባሽን ፍልስፍና ከትክክለኛው ኢስላማዊ ርእዮቶች ጋር ለማነጻጸር በሚልም በርካታ የአህሉስ ሱንና መጽሀፍትንና ድረ-ገጾችን መጎብኘትና ድሮ ያነበበችውን ማሰላሰል ነበረባት። ነገር ግን ጽሁፎቹ በተጣበበ ጊዜ ውስጥ የተጻፉ በመሆናቸው አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር መረጃዎቹ የተገኙባቸውን ምንጮች ቃል በቃል መጥቀስ አልተቻለም።

አዘጋጇ መጽሀፉ ሙሉ በሙሉ ከስህተት የጸዳ ነው የሚል አመለካከት የላትም። ሙሉ በሙሉ ከስህተት የጸዳው መጽሀፍ አላህ ያወረደው ቅዱስ-

ቁርአን ብቻ ነው። ስለሆነም ለሚታያችሁ የመረጃ ስህተት ይቅርታ እንድታደርጉላት ትማጸናለች።

ኢስላምን ለኛ የመረጠልን አላህ ነው። ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) በሀቅ የላከው አሸናፊና ጥበበኛ አምላክ የሆነው አላህ ነው። እኛን የዚህ ውብ እምነት ተከታዮች ያደረገንም አላህ ነው። ይህ ዲን ጠላቶቹ በክፉ ቢተናኮሉትም እስካሁን ድረስ አለ። ለወደፊቱም ቢሆን ኢስላምን ከምድር ላይ የሚያጠፋው ሀይል የለም። የኢስላም ጠባቂ አላህ ነውና።

አላህ በርሱ መንገድ ላይ ያጽናን!

ኡባህ አብዱሰላም ሰኢድ

## ክፍል አንድ : አህባሽ- አጠቃላይ ዳሰሳ

አህባሽ የሚባለው አንጃ ከውጪ ሲታይ የሚከተሉት ገጽታዎች አሉት፡፡

1. “አህባሽ” የኢትዮጵያ ተወላጅ በነበሩት ሼኽ አብዱላሂ ሙሐመድ ዩሱፍ (ወይም ሼኽ አብዱላህ አል-ሐረሪ አል-ሐበሺ) ጠንሳሽነት በሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት ውስጥ በ1983 ዓ.ል. የተመሰረተ ፖለቲካና ሀይማኖትን አንድ ላይ አጣምሮ የሚራመድ አንጃ (ጀመዓ) ነው፡፡
2. አንጃው በአረብኛ አጠራር “ጀምኢያቱል መሻሪኢል ኼይሪያቱል ኢስላሚያ” ይባላል፡፡ የእንግሊዝኛ ስሙ “Association of Islamic Charitable Projects” የሚል ነው፡፡
3. “አህባሽ” የአንጃው ተከታዮች በጋራ የሚጠሩበት የቡድን ስማቸው ነው፡፡ እያንዳንዱ የጀመዓው አባል “ሀበሺይ” ይባላል (ሴት ከሆነች “ሀበሺያ” ትባላለች)፡፡ በሀገራችን ውስጥ ያሉት የአንጃው ተከታዮች ግን “አህባሽ” ከሚለው ስም ይልቅ “የሼኽ ጀመዓ ነኝ” ማለትን ይመርጣሉ፡፡
4. “አህባሽ” የሚለው ቃል ምንጩ “ሐበሻ” የሚለው የሀገራችን የዐረብኛ ስም ነው፡፡ ይህም የአንጃው መስራች የተወለዱበትን ሀገር (ኢትዮጵያን) ያመለክታል፡፡ የጀመኣው አባላት ይህንን ስም ይወዱታል እንጂ አይቃወሙትም፡፡ ስለዚህ እኛ የአህባሽ ተቃዋሚዎች ያወጣንላቸው ስም አድርጋችሁ እንዳታዩት ያስፈልጋል፡፡ (እውነቱን ለማወቅ አህባሾችን ራሳቸውን ጠይቋቸው፡፡ ዌብሳይቶቻቸውንና የፌስቡክ ቡድኖቻቸውን የሚጠሩበትንም ስም ተመልከቱ)፡፡
5. አንጃው በሄደበት ሀገር ሁሉ “መንግስታዊ ያልሆነ ማህበር” ተብሎ ነው የተመዘገበው፡፡ በመሆኑም ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰጡ አንዳንድ ተቋማትን (እንደ መድረሳና የጤና ክሊኒክ የመሳሰሉትን) ከፍቷል፡፡ በሀገራችን ውስጥ ግን እንዲህ አይነት ፕሮጀክቶችን የሰራ አይመስለኝም፡፡
6. አህባሽን የመሰረቱት “ሼይኽ አብዱላህ አል-ሀረሪ” ከሶስት አመታት በፊት ቢሞቱም እስካሁን ድረስ የአንጃው ከፍተኛ መንፈሳዊ መሪ ተደርገው ይታያሉ፡፡ በመሆኑም የጀመዓው አባላት “ሼይኹና” ወይም “ሰይዱና” ይሏቸዋል፡፡ በቤታቸው ግድግዳና በሌሎችም ቦታዎች (በሞባይል ስልካቸውም ጭምር) የመሪያቸውን ፎቶ ያስቀምጣሉ፡፡
7. የአንጃው ዋና ማዕከል (Head Quarter) ያለው በሊባኖስ ዋና ከተማ ቤይሩት ውስጥ ነው፡፡ በተጨማሪም በሶሪያ፣ ዮርዳኖስ፣ ግብጽ፤

አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ካናዳ፣ ጀርመን፣ ዴንማርክ፣ አውስትራሊያ ወዘተ... ቅርንጫፎች አሉት።

8. የአህባሽ በርካታ ተከታዮች ያሉትም እዚያው በሊባኖስ ሀገር ሲሆን አንጃው በአሜሪካ፣ ካናዳና አውስትራሊያም ጠንካራ ጀመዓ እንደመሰረተ ይታወቃል። ወደ ሀገራችን ከገባ ከአስር ዓመታት በላይ ቢሆነውም ብዙ ተከታዮችን መመልመል አልቻለም። (አብዛኛው ህዝብ አንጃው እዚህ መኖሩን እንኳ አያውቅም)።
9. አንጃው የሻፊዒይ መዝሀብ ተከታይ ነኝ ይላል። የዓቂዳ ትምህርቱም "አሸዐሪ" (ኢማም አቡል ሐሰን አል-አሸዐሪ ያስተማሩት መንገድ) እንደሆነ ያወሳል። የ"ሪፋዒያ" የሱፊ ጠሪቃ ተከታይ እንደሆነም ይገልጻል።
10. አንጃው ስብከቱን ለተከታዮቹ የሚያስተምርበት "መርከዝ" (ማእከል) አለው። በየመርከዙ የሚቀመጡ ሼይኾችንም በቤይሩት እያሰለጠነ በዓለም ዙሪያ ያሰራጫል። በመርከዙ ተምረው የሚወጡ ጎበዝ ተማሪዎችም ቤይሩት ሄደው የሚማሩበት የከፍተኛ ትምህርት እድል (scholarship) ይሰጣቸዋል።
11. የአንጃው መንፈሳዊ ትምህርቶች በአብዛኛው የሚያተኩሩት በአቂዳ፤ "ፊቅህ" እና "ሱፊያ" (Sufism) ላይ ነው። የትምህርት ቋንቋውም አረብኛ ነው።
12. አንጃው ተከታዮቹን ከሚያስተምርባቸው የመማሪያ መጽሀፍት መካከል በስፋት የሚታወቁት ሁለት ናቸው።
    12.1 ***"ሙኽተሰር አብዱላህ አል-ሐረሪ"***
    a) ይህ ጀማሪዎች የሚማሩበት መጽሀፍ ሲሆን የአቂዳ፤ ፊቅህ፤ ከላም (Speculative Theology) ትምህርቶችን አካቷል።
    b) መጽሀፉ የዛሬ 100 አመት ገደማ በአንድ የመናዊ ሼኽ እንደተጻፈ በመግቢያው ላይ ተጠቅሷል። "ሼኽ አብዱላህ የጻፉት ሸርሁን (ማብራሪያውን) ነው" ተብሎም ተጽፎበታል። ነገር ግን ከመጽሀፉ 70% በላይ የሚሆነው ክፍል የተያዘው በ"ሸርሁ" ነው።
    c) መጽሀፉ በእንግሊዝኛና በአማርኛ ተተርጉሟል። የእንግሊዝኛው ትርጉም ቀለል ባለ አቀራረብ የተዘጋጀ ሲሆን አማርኛው ግን ልክ እንደ አረብኛው "የመጽሀፉ አዘጋጅ እንደዚህ አሉ!" እያለ ነው ትምህርቱን የሚዘረዝረው። (የአረብኛው መጽሀፍ "ቃለል ሙአሊፉ" እያለ የሚሄድ የትረካ አቀራረብ አለው)።

d) የመጽሀፉ ዋና ክፍል ("ሽርህ" ያልሆነው) ላይ ላዩን ሲታይ እስላማዊ መንገድን የተከተለ ይመስላል። ነገር ግን በእስልምና ውስጥ የማይታወቁ አስገራሚ አቋሞች ይበዙበታል። ይህንን በትክክል የምትረዱትም ከዋናው ምንባብ ሳይሆን "ሽርህ" ተብለው ከቀረቡት አደገኛ ትንተናዎች ነው።

e) ከሁሉም በላይ ደግሞ "ይህንን ያላለ ይከፍራል"፤ "በዚህ ያላመነ ከኢስላም ወጥቷል" "ይህንን ያደረገ ካፊር ነው" የሚሉ አስፈሪ አባባሎች ስለሚበዙበት በትእግስት አንብቦ መጨረሱ ራሱ ከባድ ነው።

12.2 ሁለተኛው መጽሀፍ ***"ቡግየቱ- ጣሊብ"*** ተብሎ ይጠራል።

a) በዚህኛው መጽሀፍ የሚማሩት በትምህርት ከፍ ያሉ ተማሪዎች ናቸው። (ይህኛው መጽሀፍ በእንግሊዝኛና በአማርኛ ቋንቋዎች ስለመተርጎሙ አላውቅም)።

b) ቡግየቱ-ጣሊብ በስፋት ካልሆነ በስተቀር በይዘቱ ከሙኽተሰር ጋር አንድ ነው። ቢሆንም በሙኽተሰር ውስጥ የሌሉ በርካታ አስገራሚ ፈትዋዎች አሉበት።

13. አህባሽ በአለም አቀፍ ደረጃ የሚያሳትመው መጽሄት "መናረል ሁዳ" ይባላል። በቤይሩት ከተማ "ሰውቱል ኒዳ" የሚባል ሬድዩ ጣቢያ አለው። በአለም ዙሪያ በርካታ የኢንተርኔት መረቦችንም ዘርግቷል። ከነዚህም መካከል www.aicp.org ዋነኛው ዌብሳይት ነው።

14. ይህ አንጃ

14.1 በአፈጣጠሩ፣ በእድገቱ፣ በእምነት ፍልስፍናውና በድርጊቶቹ በጣም ግራ የሚያጋባ (controversial) ነው።

14.2 በጅምሩ ላይ ከሶሪያ ጋር ይቀራረብ ስለነበር በሶሪያ ተጽእኖ የሚመራ ይመስል ነበር። እስካሁን ድረስም ከሶሪያ መንግስት ጋር መልካም ግንኙነት አለው። ሌሎች ድርጊቶቹን ስናይ ግን *"አህባሽና ሶሪያ የጥቅም ግንኙት እንጂ የፍቅር ግንኙነት የላቸውም "* ማለታችን አይቀርም።

14.3 መላው የሊባኖስ ህዝብ በሹክሹታ እንደሚያወራውና በኢንተርኔት እንደሚጻፈው ከሆነ አህባሽ የእስራኤል የስለላ ቡድን (ሞሳድ) በረቀቀ ዘዴ የሚያሸከረክረው ድርጅት ነው። በመሆኑም በሊባኖስ ውስጥ ጸረ-እስራኤል አቋም ያላቸውን ማህበራትና የፖለቲካ ቡድኖች በሙሉ "ጠብ አጫሪዎች ናችሁ" እያለ ይቃወማል። የፍልስጥኤም የነጻነት ጥያቄን በሚመለከትም "በሰላማዊ መንገድ

ብቻ ነው መፈጸም ያለበት" የሚል ያልተብራራ አንቀጽ በፖለቲካ ማኒፌስቶው ላይ እንዳሰፈረ የዛሬ 15 አመት ገደማ ስለቡድኑ የጻፉት ኒዛር ሀምዛ ይገልጻሉ።

14.4 በቅርቡ እነ ሀጋይ ኤርሊችን የመሳሰሉ ጽዮናዊያን *"አህባሽ የሚከተለው ለዘብተኛ ኢስላማዊነት ለዓለም አስፈላጊ የሆነ የሰላም መድሀኒት ነው"* እያሉ መጻፋቸውም ከላይ የተባለውን ጥርጣሬ ወደ እውነታ ከፍ ያደርገዋል።

14.5 ከሁሉም በላይ አህባሽ በአለም ዙሪያ ያሉ ሙስሊሞችን ያስደነገጠው በሶስት አቋሞቹ ነው።

a) በቅድሚያ ከየት እንደተገኙ የማይታወቁ የእምነት ፍልስፍናዎቹን የማይቀበሉ ሙስሊሞችን በጅምላ "ካፊር ናቸው" በማለት ይፈርጃል።

b) በሁለተኛ ደረጃም ከምዕራባዊያን ጋር ቅጥ ያጣ የወዳጅነት ትስስር አለው። ሙስሊሙን እንደጠላት ለሚያዩት ምዕራባዊያን አህባሽ ውድ ልጃቸው ነው። በተለይ ከሴፕቴምበር 11/2001 ወዲህ ተፈላጊነቱ ጨምሯል።

c) በሶስተኛ ደረጃም ሙስሊሞችን ለጥቃት የሚያሳድድ "ሙስሊም ነኝ" ባይ አንጃ መሆኑ በጣም እያነጋገረ ነው። አንጃው በይፋ ሲናገር "ጠላቶቹ ወሀቢዎች ናቸው" ይላል። ይህ ግን የአንጃው የማስመሰያና የመከፋፈያ ስልት መሆኑን ቡድኑን በቅርበት የሚያውቁ ምሁራን ይገልጻሉ። "ጠላቶቹ መላው ሙስሊሞች ናቸው" በማለትም ያስረዳሉ።

አህባሽ በጥቅሉ ሲታይ ይህንን ይመስላል። በሚቀጥሉት ክፍሎች ሽፋኑን እየገለጥን በዝርዝር እናየዋለን።

**ክፍል ሁለት: *አህባሽና የአቂዳ ብክለት*፡**

አህባሽ "ለአቂዳ ጥራት የምታገል ነኝ" ይላል። የጀመዓው ተከታዮች *"ዋነኛው ኃይማኖታዊ ዓላማችን በወሃቢዎች ተንኮል የተበከለውን የጥንቱን እውነተኛ የአህሉ ሱንና አቂዳ በተገቢው መንገድ ማስተማር ነው"* ይላሉ። ይህ ግን አህባሽን በትክክል ለሚያውቁ ሰዎች አይዋጥላቸውም። እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት "የአህባሾች ፍላጎት ተውሂድን ማጥራትና ሰዎች አላህን ብቻ እንዲገዙ ማስተማር ሳይሆን እስላማዊውን የአምልኮ ህግ ማውደም ነው"። ይህንን ለማስረዳትም አህባሾች ሽንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩባቸውን ነጥቦች እንድናስተውል ይመክራሉ (የዚህን ዝርዝር በክፍል ሶስት እመጣበታለሁ)።

እኔም የአህባሽ አላማ አቂዳን ማጥራት እንዳልሆነ ስለማውቅ ወደዚህ ርእስ ለመግባት አልፈልግም ነበር። አህባሾች ርዕሱን በፍርሀት የተውኩት እንዳይመስላቸው ስል ብቻ አንዳንድ ነገሮችን እነካካለሁ። ይህንን ሳደርግ ግን ኡለማ በ"ኺላፍ" የተለያዩባቸውን ነጥቦች አልነካም። የአህባሾች አንዱ ባህሪም እነዚህን የ"ኺላፍ" ጉዳዮችን ማራገብና አንድነታችንን መበጥበጥ ነው- አላህ ከተንኮላቸው ይጠብቀንና።

1. አቂዳን በተመለከተ ዋነኛው ጥያቄ *"ስለ አሸዐሪ አቂዳ እየደጋገሙ የሚናገሩት አህባሾች በትክክል የ"አሸዐሪ" መንገድ ተከታዮች ናቸው ወይ?"* የሚለው ነው። መልሱ "አይደሉም" የሚል ይሆናል።
   "አሸዐሪ" ኢማም አቡል ሐሰን አል-አሸዐሪ ያስተማሩት የአቂዳ መንገድ ሲሆን የአል-አዝሐር ዩኒቨርሲቲ በይፋ የሚያስተምረው ይህንን የአቂዳ መንገድ (creed) ነው። በእስልምና ውስጥ ከሚታወቁት ሶስት የአቂዳ መንገዶችም አንዱ ነው። የተቀሩት ሁለት መንገዶች "ማቱሪዲ እና "አሠሪ/ሀንበሊ" ይባላሉ። እነዚህ ሶስት መንገዶች "አቂደቱ ጠሃዊያ" የተባለውን ዝነኛ መጽሀፍ "ትክክለኛ የአህሉ-ሱንና አቂዳ" ነው በማለት ያምኑበታል።
   አንዳንድ ሰዎች ግን አህባሽን የጎዱ እየመሰላቸው በኢማም አቡል ሐሰን አል-አሸዐሪ እና በኢማም አቡሐሚድ አል-ገዛሊ ላይ ውርጅብኝ ሲያወርዱ ይታያል። እነዚህ ሰዎች የአሸዐሪን ማንነት ለመረዳት "አህባሽ"ን ሳይሆን በትክክለኛው የአሸዐሪ አቂዳ የሚያምኑትን የኢማም ዩሱፍ አል-ቀርዳዊን መጽሀፎች ማንበብ ወይም የአል-አዝሐር ዩኒቨርሲቲን መጠየቅ ነበረባቸው። ስለዚህ ይህ ስህተት መደገም የለበትም ።

2. “አህባሾች” በአቂዳቸው በጥንት ዘመን ከተነሱት “ሙዕተዚላ” እና “ጀህሚያ”ን ከመሳሰሉ የኑፋቄ (heretic) ቡድኖች ጋር ይቀራረባሉ። ይህንን በደንብ ለማመዛዘን ከፈለጋችሁ ስለ“ሙዕተዚላ”ና ስለ “ጀህሚያ” ማንነት በስፋት የሚዘረዝሩትን የሚከተሉትን ዌብሳይቶች ተመልከቱ።
http://www.mutazila.com/ba/bio/mutazila/mutazila.htm
http://en.wikipedia.org/wiki/Mu%27tazili
http://en.wikipedia.org/wiki/Jahmites
http://en.wikipedia.org/wiki/Jahm_bin_Safwan
3. አሁን ያሉት ሁሉም ኢስላማዊ የአቂዳ መንገዶች አላህ በራሱ የገለጻቸው ባህሪያትና መልክ መልካም ስሞች እንዳሉት ያስተምራሉ። ለምሳሌ ሙስሊሞች በሙሉ “*አላህ ይናገራል፤ ያያል፤ ይሰማል፤ ይደሰታል፤ ይቆጣል፤ ይምራል፤ ይቀጣል፤ ይችላል፤ ያደርጋል.. ወዘተ..*” በማለት እናምናለን። በእነዚህ የአላህ ባህሪያት የምናምነው ግን “ቢላ ኬይፍ” (“እንዴት!” የሚል ጥያቄ ሳናስከትል) ነው። የአላህን ባህሪያት ከፍጡራኑ ባህሪዎች ጋር ማመሳሰልም (“ተሸቢህ” ማድረግ) ክልክል ነው። በቁርአንና በሐዲስ ከተነገረው በላይ እየሄዱ መፈላሰፍም አይፈቀድም። ስለፍጡራኑ ራሱ በትክክል መረዳት ያቃተን ሰዎች ስለፈጣሪ የምንፈላሰፍበት ምክንያት የለምና።
አህባሾችም እነዚህን የአላህ ባህሪያት ይቀበሉና “ፈጣሪ ከፍጡራን ጋር አይመሳሰልም” በሚል ስሜት አስገራሚ የፍልስፍና ትንተናዎች ውስጥ ይገባሉ። *“አላህ ባህሪዎቹን በቁርአን እንደዚያ ብሎ የገለጸው ለኛ በሚገባን ቋንቋ በደንብ ለማብራራት ፈልጎ ነው እንጂ ባህሪያቱ በዚያ ቋንቋ ከተነገሩት ጋር አንድ ናቸው ብሎ መናገር ክልክል፤ እንደዚህ ብሎ ማመን ፈጣሪን ከፍጡራን ጋር ማመሳሰል ስለሆነ ኩፍር ነው”* በማለት የትኛውም ሙስሊም የማያምንበትን አቋም ያራምዳሉ። በአህባሾች አነጋገር መሰረት በቁርአን ውስጥ ተገለጸው “አላህ ሰሚና ተመልካች ነው” የሚለው ቃል ሌላ የአላህን መስማትና ማየት አይገልጽም ማለት ነው። በዚህም “አላህ ዛት እንጂ ሲፋት የሉትም” ከሚሉት የጥንቶቹ ሙዕተዚላዎችና ጃህሚያዎች ጋር ይመሳሰላሉ።
4. እኛ ሙስሊሞች እንደምናምነው በየውመል ቂያማ ከሚቀርቡልን አስጨናቂ ፈተናዎች አንዱ የ“ሲራጥ” ፈተና ነው። ይህ በጀሀነም ላይ የሚዘረጋ አስጨናቂ ድልድይ መሳይ መንገድ በቅጥነቱ ከጸጉርም

ያንሳል። በስለቱ ግን ከምላጭ እንኳ ይብሳል (አላህ ከመከራው ይጠብቀን)።

አላህ የፈቀደለት ሰው "ሲራጥ"ን ያለምንም ችግር ያልፈዋል። እርሱ ያልወደደለት ሰው ከሲራጥ ይንከባለልና ወደ ጀሀነም እሳት ይወድቃል። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሀዲስ ያስተማሩት ይህንን ነው።

የአህባሾች መጽሀፍት ግን *"ሲራጥ ከጸጉር የቀጠነና ከምላጭ የሰላ ነው የተባለው የስቃዩን ክብደት ለማሳየት እንጂ ሲራጥ በእውነት እንደዚያ ስለሆነ አይደለም፤ ሰዎች መራመድ የሚችሉበት ስፋት አለው"* ይላሉ። በዚህ አቋማቸው የሙዕተዚላን አይነት ስነ-አመክንዮ (rationalism) እንጂ እምነትን አለመከተላቸው ግልጽ ሆኖ ይታያል ነው። የነቢዩንም ሀዲስ አስተባብለዋል።

5. ሙስሊሞች በሙሉ *"አላህ ጀንነትንና ጀሀነምን ለመመላት የገባው ቃል በትክክል ይፈጸማል"* ባዮች ነን። አህባሾችም በዚህ ያምናሉ። ሆኖም ከዚህ ጋር አብሮደው የሚናገሯቸው በርካታ ፍልስፍናዎች አሏቸው። ለምሳሌ አህባሾች ***"አላሁማ አጂርኒ ሚነናር (አላህ ሆይ! ከጀሀነም እሳት ጠብቀን)"*** ብሎ ለሁሉም ሙስሊሞች ዱኣ ማድረግ ክልክል ነው፤ ማንም ሰው እንዲህ አይነቱን ዱኣ ማድረግ ያለበት ለራሱ ብቻ ነው" ይላሉ። "ምክንያቱ ምንድነው?" ተብለው ሲጠየቁ ***"አላህ ጀሀነምን ለመመላት የገባውን ቃል መቃረን ነው!" ይላሉ።*** እንዲያውም የአህባሾቹ ሰሪሁል በያን መጽሀፍ ገጽ 217 ላይ ተጽፎ እንደሚታየው "ይህ ዱኣ በሙርጂእ አቂዳ እንጂ በአህሉ ሱንና አቂዳ ውስጥም የለም። ለሁሉም ሙስሊሞች አላህ ምህረት እንዲያደርግ መለመን ያከፍራል" ይላል።

በዚህ ትንተና መሰረት የሚከተለው የቁርኣን አያህ ተቀባይነት የለውም ማለት ነው።

"እነዚያ (ሙእሚኖች) :- "ጌታችንን ሆይ! የጀሀነም ቅጣትን ከኛ ላይ መልስልን፤ ቅጣቷ የማያልቅ ነውና" የሚሉት ናቸው።"

(አል-ፉርቃን፡ 65)

አስተግፊሩላህ!! አላህ ባወረደው የቁርአን አያህ የፈቀደልንን በጋራ ዱኣ የማድረግ መብት ልንነጠቅ ነው እንዴ?!!

6. አሁን በቅርቡም ሌላ አስፈሪ አባባል ከአህባሾች በኩል ሰምቻለሁ። እነርሱ እንዳሉት "የአቂዳ" ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሀዲሶች "ሙተዋቲር" (በብዙ ዘጋቢዎችና በበርካታ ሰንሰለቶች ከሰው ወደሰው እየተላለፉ ወደኛ የደረሱ) መሆን አለባቸው። "መተዋቲር" ያልሆኑ ሀዲሶች

("አሀድ" የሚባሉት) ግን ለሌሎች ጉዳዮች እንጂ አቂዳን ለተመለከቱ ጉዳዩች አይሰሩም። ለምሳሌ አህባሾች "ኢስቲዋእ" የሚለውን ቃል "አላህ ከዐርሽ በላይ ነው!" ብሎ የሚፈታ ዘገባ ሀዲስን ለሰበሰቡት ምሁራን የደረሰው "ሙአዊያ ኢብን ያህያ" በተባለ ሰው ብቻ ነው፤ ስለዚህ ሀዲሱ ፉርሽ ነው" ይላሉ። (እነርሱ የሚሉትን ዘጋቢ የአባት ስም በትክክል አልያዝኩትም። ቢሆንም እነርሱ የሚሉት ሀዲስ በሀዲስ መጽሀፍት ውስጥ ያለ አይመስለኝም።)

ሱብሀነላሕ!! የጥንቱ የሙዕተዚላ ኡለማ *"ቀደር ለሰድስቱ የኢማን መሰረቶች ውስጥ አይመደብም"* በማለት ቀደርን ከአርካኑል ኢማን ውስጥ የሰረዙት እኮ በዚህ ደካማ አቋማቸው ነው!! ሙዕተዚላዎች "ስለቀደር የተነገረው ሀዲስ አንድ ዘጋቢ ብቻ ያወራው ሀዲስ ነው" በማለት "ቀደር"ን ከስድስቱ የኢማን መሰረቶች ሰርዘውታል። (በዚህኛው ነጥብ ላይ ግን "ሙዕተዚላዎች" እንኳ ከአህባሾች ተሻለዋል። ምክንያቱም ሙዕተዚላዎች ከላይ በጠቀስኩት አቋማቸው ላይ *"ቀደር ለሰድስቱ የኢማን መሰረቶች መካከል እንደሚመደብ በግልጽ የተጠቀሰበት ቦታ በቁርአን ውስጥ የለም"* የሚል ነገር አስከትለውበታል። አህባሾች ግን ይህንን እንኳ አላመዛዘኑም።)

7. እኛ ሙስሊሞች እንደምናምነው ከሙስሊም ወላጆች የተገኘ ልጅ ሙስሊም ነው። ወላጆቹ ስለተውሂድና እስልምና እያስተማሩ ያሳድጉታል። እንዲህ አይነቱ ልጅ ለአላህ መጠን ሲደርስ በሙስሊምነቱ ይቀጥላል እንጂ እንደ አዲስ ወደ እስልምና አይገባም። የአህባሾቹ *"ሙሽተሰር አብዱላህ አል-ሐረሪ"* ግን *"ማንም ሰው ለአላህ መጠን ሲደርስ በአዲስ መልክ ሸሀዳ መያዝ አለበት"* ይላል። ይህ ከኛ ጋር የሰፋ ልዩነት ባላቸው ሺዓዎች እንኳ የማይታወቅ ባእድ ፍልስፍና ነው። አህባሾች፤ "ሸሀዳ ያዙ!" እያሉ ህዝቡን የሚያስጨንቁት በዚህ አቋማቸው ሳይሆን አይቀርም።
8. ከዚሁ ጋር የሚያያዝና "ከሙሽተሰር" ያነበብኩት አንድ ግራ የሚያጋባ ነገር ደግሞ እንዲህ የሚል ነው።

"አንድ ሰው በጁምዓ ቀን ወደ እስልምና ለመግባት ፈልጎ ኢማሙ ኹጥባ በሚያደርግበት ጊዜ ወደ መስጊድ ቢመጣና ሸሀዳ የሚያስይዘው ሌላ ሰው በአካባቢው ከሌለ ኢማሙ ኹጥባውን አቁሞ ሰውዬውን ሸሀዳ ማስያዝ አለበት"።

እንዲህ ማለቱ ለምን አስፈለገ? ደግሞስ ኹጥባ አቋርጦ ሸሃዳ ማስያዝ እንዴት ይፈቀዳል?

(ምሁራን በዚህ ላይ አስተያየታቸውን መስጠት አለባቸው)።

9. ይህንን ጽሁፍ ከማጠናቀቁ በፊት አንድ ግራ የሚያጋባ ነገር ልጨምርበት።

   የአህባሾች "መኽተሰር" መጽሀፍ *"አቡ በክር የነቢያችን ሰሀባ አይደሉም ያለ ሰው ይከፍራል። ምክንያቱም አላህ በቁርአኑ አቡ በክር የነቢዩ ሰሀባ ናቸው ብሎ ተናግሯል፤ ይህንን የሚያስተባብል ሰው ቁርአንን ያስተባበለ ሰው በመሆኑ ካፊር ነው። ሌሎች ሰሀባዎች የነቢዩ ጓደኞች አይደሉም ያለ ሰው ግን አይከፍርም"* ይላል።

   ይህ ነጥብ በአንድ መልኩ ሲታይ ቁርአንን ማስተባበል የለብንም የሚል ስሜት ይሰጣል። በዚህ በኩል ጥሩ ይመስላል። *"ሌሎች ሰሃባዎች የነቢዩ ጓደኞች አልነበሩም ያለ ሰው አይከፍርም"* የተባለውስ ለምንድነው? ሰሀባዎችን እንዲህ መለያየት ተገቢ ነው? የሸሪዓ ሰዎች በዚህ ላይ የሚሉን እንጠብቃለን።

   እኔ እንደምጠረጥረው ግን ይህ አባባል አህባሾች በፊስቅ (አመጸኛነት) እና በዲል (ጠማማነት) የሚወነጅሏቸውን እነ ሙአዊያ አቡ ሱፊያንና ዙቤይር ኢብኑል አዋምን በመሳሰሉ ሰሀባዎች (ረ.ዐ) ላይ የሚያካሄዱትን የስድብና የእርግማን ዘመቻ ሸሪዓዊ መልክ ለማስያዝ ከሚጠቀሙባቸው ማታለያዎች አንዱ ነው። በዚህ አባባል እየተመሩ ሙአዊያን ይሰድቡና "ለምን የነቢዩን ሰሀባ ትሳደባላችሁ" ሲባሉ "ሙአዊያ የነቢዩ ሰሃባ አይደለም" የሚል መልስ ይሰጡናል ማለት ነው። ጉድ እኮ ነው?!!

ያ ጀመዓ! አህባሾች አቂዳ የሚባል ነገር አያውቁም ። እንዳያችሁት በ"ኢማም አቡል ሐሰን አል-አሽዐሪ" ስም ማንኛውም ሙስሊም የማይቀበላቸውን የተበከሉ ፍልስፍናዎችን ነው የሚያራምዱት። ስለዚህ ለአቂዳ የሚጨነቁ እየመሰላችሁ ለክርክር እንዳትጠንቸው አደራ እላችኋለሁ።

በርቱ ያ ጀመዓ!

## ክፍል ሶስት፡ አህባሾች ሌት ተቀን የሚታገሉለት ዓላማ

አህባሾች እንደ ትልቅ ግኝት የሚናገሩት አንድ አባባል "*አላሁ መውጁዱን ቢላ መካን*" (አላህ ያለ ቦታ ነው ያለው) የሚል ነው። ከየትኛውም የአህባሽ ጀመዓ አባል ጋር ብትቀራረቡና በኢስላማዊ ጉዳዮች ላይ ብትወያዩ የንግግራችሁ መነሻና መጨረሻ ሆኖ የምታገኙት ይህንን አባባል ነው። አንዳንድ ሰዎች አባባሉን ሲሰሙ አህባሾች በአቂዳ ጉዳዮች ላይ "ጁህድ" (ልዩ ጥረት) የሚያደርጉ ይመስላቸውና ለክርክር ይጋበዛሉ።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ይህ አህባሽን አለማወቅ ነው። የአህባሾች ፍላጎት በሌላ አቅጣጫ ላይ ነው ያለው። በዚህ ክፍል ይህንን ልዩ ፍላጎታቸውን እናያለን።

### *ተብሩክ፣ እና ተወሱል*

ኢስላም የተውሂድ (አሃዳዊ) ሃይማኖት ነው። አላማው ሰዎች አላህን ብቻ እንዲገዙ ማስተማር ነው። በኢስላም ህግ መሰረት ሰዎች አላህን ሲያመልኩ ከርሱ ጋር አንድም ነገር ማጋራት የለባቸውም። ኢባዳቸውንም በፍጹምነት (በኢኽላስ) ማከናወን ይጠበቅባቸዋል። አላህ የፍጥረቶች ሁሉ አስገኝ፤ አድራጊና ፈጣሪ፤ ህይወት የሚሰጥና የሚነሳ፤ ፍጥረታት በሙሉ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን መሰረታዊ ፍላጎቶች የሚያሟላላቸው ብቸኛ ጌታ እንደሆነ ማወቅና በዚህም ላይ በጽናት መቆም ይጠበቅባቸዋል። ማንም ሰው ጥሩ ነገር ሲገጥመው ምስጋናውን ለአላህ ብቻ ማቅረብ አለበት። በጭንቀት ጊዜም ልመናውን ማቅረብ ያለበት ወደ አላህ ብቻ ነው ። በቁርአንና በሐዲስ የተረጋገጠውና ያልተሸራረፈው የሙስሊሞች የተውሂድ መንገድ ይህ ነው።

ወደ አህባሾች ስንመጣ ግን ኢስላማዊው የተውሒድ መንገድ ህልውናውን ያጣል። የአንጃው መስራች አኩራፊ ባህሪ ያመነጨችም ይህንን የተውሂድ መንገድ ሙሉ በሙሉ ለመቀበል ባለመፈለጋቸው ነው። በርሳቸው ዙሪያ የተሰለፉ ቀደምት ተከታዮችም የዚህ የተወላገደ አመላከከት አራማጆች ነበሩ።

አህባሾች ተውሂድን ለመበከል እንደ መከራከሪያ የሚያነሷቸው ነገሮች ሁለት ናቸው። እነርሱም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

1. ***ተብሩክ***- በሸሪዓው መሰረት አላህ የሚወዳቸውን ነገሮች እያወሱ የርሱን በረከት መጠየቅ ማለት ነው።

ለምሳሌ በጁምኣ ቀን ኢማሙ ኹጥባ እያደረገ በመሀሉ የተወሰኑ የቁርአን አያቶችን ይቀራና ***"ባረከላሁ ሊ ወለኩም ቢል-ቁርአኒል አዚም"*** ብሎ ዱኣ ሲያደርግ አይታችኂል (አላሁ በረከቱን ለኔና ለናንተም እንዲሰጠን በቁርአን እርሱን እንለምናለን" ማለት ነው)። ተበሩክ የሚባለው ይህ ነው። እንዲህ አይነቱ ድርጊት በሸሪዓው የሚፈቀድ ከመሆኑም በላይ በጣም ተወዳጅ ነው።

2. ***ተወሱል፤*** አላህ የሚፈቅድላቸውን ወገኖችና መልካም ስራዎች በማስቀደም የአላህን ምልጃ መጠየቅ ማለት ነው።
ለምሳሌ አንድ ሰው በጭንቅ ላይ ቢወድቅ ድሮ የሰራቸውን መልካም ስራዎች በማውሳት *"ያ አላህ! ያንን ሰራ ላንተ ሰል ነው የሰራሁት። ዛሬ ደግሞ እንዲህ አይነት ጭንቅ ላይ ወድቄያለሁና ከመከራው ገላግለኝ!!"* በማለት አላህን መለመን ይችላል። በሌላ ምሳሌም ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ) በየውመል ቂያማ የሚቆሙልን ምልጃ ራሱ ተወሱል ነው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ምልጃውን የሚጠይቁልን አሁን ሳይሆን ለምርመራ አላህ ፊት ስንቆም ነው። የነቢዩን ምልጃ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በኢባዳው መጠንከርና የርሳቸውን ፈለግ (ሱና) ጠበቅ አድርጎ መያዝ ይጠበቅበታል።

አህባሾች የተውሂድ ሽፍጥ የሚሰሩት በነዚህ ሁለት ድርጊቶች ላይ ነው። በተበሩክና በተወሱል ስም ከባህልና ከባእድ አምልኮ የተወረሱ ድርጊቶችንና እምነቶችን እስልምና የሚፈቅዳቸው ህጋዊ ነገሮች በማድረግ ያጸድቃሉ። ይህንን የተቃወመውን ሰው "ወሀቢ" ብለው ይወርፋሉ። ***"ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አትገዙ፤ እርሱን ብቻ እርዳታ ጠይቁ"*** የሚለው የተውሂድ ቃል ነቢያት ሁሉ የለፉበትና የተዋደቁለት ዓላማ ሆኖ እያለ አህባሾች ይህንን ንጹህ እስላማዊ መንገድ በ"ተበሩክ" እና "ተወሱል" ስም ለመበከል መነሳታቸው እጅግ በጣም ይመራል። በዚህ ላይ ኢማም አል-ሻፊዒንና ኢማም አቡል-ሐሰን አል-አሸዐሪን እንደ ማስረጃ መጥራታቸው ደግሞ የለየለት ወንጀል ነው።

አህባሾች በተበሩክና በተወሱል ስም ከሚያጸድቋቸው ኢ-እስላማዊ ድርጊቶችና አመለካከቶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. በአህባሾች አመለካከት የነቢያትና የሷሊሆችን (ደጋግ የአላህ ባሪያዎች) መቃብር በልዩ ሁኔታ መገንባት (በመቃብሩ ላይ "ደሪህ" መገንባት፤ ቀለም እየቀቡ ማሳመር"፤)፤ መቃብሮቹን እየሄዱ በመሳም በረካቸውን መጠየቅ፤ በመቃብሮቹ አካባቢ ግብጥዎችን እያደረጉ ወሊዮችን

ማሞገስ (በድቤ ጭምር በማጀብ) የመሳሰሉት ድርጊቶች በሙሉ ሙስሊሞች ሊያደርጓቸው የሚገቡ ተግባራት ናቸው። እነዚህን ድርጊቶች የተቃወመ ሰው "አላህ ሀላል ያደረገውን ነገር የተቃወመ በመሆኑ ይከፍራል" ይላሉ።

2. ሰዎች ተውሂድን በመቃረን የሚናገሯቸው እንደ "ገውሰል አዘም፤ "ጅላሌ መጀን" (ሼይኽ አብዱልቃዲር አል-ጂይላኒን መጥራታቸው ነው)፤ "የባሌው ኑር ሁሴን ባንተ ልመጀን"፤ "አባድር ጦም አያሳድር፤" ወዘተ የመሳሰሉ አባባሎች "የአውሊያዎችን እርዳታ የሚያስገኙ በመሆናቸው በጣም አስፈላጊ ናቸው። አላህ ዘንድ በቀላሉ ለመድረስ ከፈለግን መንገዳችን በአውሊያዎቹ በኩል መሆን አለበት።" በማለት ያስተምራሉ።
3. በአህባሾች አመለካከት መሰረት "አውሊያዎቹ በተወለዱበት ቀናቸው ለእርዳታ ብንጠራቸው ፈጣን ምላሽ ይሰጡናል። ለምሳሌ ማክሰኞ የባሌው ኑር ሁሴን ቀን ነው። ዕሮብ የአብዱልቃዲር አል-ጂይላኒ ቀን ነው። ሀሙስ የሼኽ አባድር ቀን ነው። ቅዳሜ የሰይድና ኸድር ቀን ነው። እነዚህን አውሊያ በቀናቸው ስንጠራ እርዳታቸው ይደርስልናል።"
4. በተጨማሪም "አረፋ፤ ሻዕባን፤ሙሀረምና ሰፈር በተባሉት ወራት ሰዎች ለዚያራ ወደ አውሊያዎች መቃብር እየሄዱ በረካ ማግኘት አለባቸው" በማለት ያስተምራሉ። (ድሮ "ሀጅ መሄድ ያቃተው ወደ ባሌው ኑር ሁሴን ቢሄድ ሀጃው ይሞላለታል" ሲባል የሰማነው ተረት በአህባሾች ዘንድ "እውነት" ነው።)
5. በልጅነቴ የሰማሁት አንድ አባባል አለ። እንደዚህ የሚል!
"አውሊያዎችን ያከበረና በነርሱ ስም ተወሱል የገባ ሰው በምድር ላይ ሲኖር እርዳታቸው አይለየውም። ኢዝራኢል ሩሑን (ነፍሱን) ሊወስድ በሚመጣበት ጊዜ ሰውዬው ሸሀዳ እንዳይይዝ ሸይጣን "ኸምር" የመሰለ ጎምዛዛ መጠጥ በቅል ይዞበት ይመጣል። በዚያን ጊዜ አውሊያው ከሸይጣን ጋር ይጋፈጥና ቅሉን ይሰብርለታል።"
አህባሾች ይህንን አባባል ሲናገሩ ባልሰማቸውም ነገራቸው ሁሉ በእንዲህ አይነቱ አባባል የተሞላ ነው። (አንዳንዴ ከዚህም የሚብስ አባባል ትሰማላችሁ)።
6. በአህባሾች አመለካከት መሰረት "ዝናብ ሲጠፋ ወይም ተላላፊ በሽታ በአካባቢው ሲገባ ምእመናን ለተወሱል ወደ አውሊያዎች መቃብር መሄድና ልመና ማቅረብ አለባቸው"።

7. “ከአውሊያ መቃብር ቦታ የሚቆፈረው አፈር (“ጀውሀር” ይሉታል) ለበሽታ ከፍተኛ ፈውስ ከመሆኑም ሌላ ለበረከቱ ስንል በየቤታችንን ብናስቀምጥ ሸይጣን በበራችን ላይ አያልፍም” የሚለው ልማድ አህባሾች በግልጽ የሚሟገቱለት እምነት ሆኖ ይገኛል።
8. የነቢዩን የልደት ቀን ማክበር ራሱ በሙስሊሞች መካከል ትልቅ ጭቅጭቅ ፈጥሮ ሳለ አህባሾች “የአውሊያ መውሊድን ማክበር ትልቅ በረካና ምንዳ ያስገኛል” ይላሉ።
9. ወዘተ..

አህባሾች በተበሩክና በተወሱል ስም ሸንጣቸውን ገትረው የሚከራከሩላቸው ለነዚህ ኢ-እስላማዊ የሽርክና የባዕድ አምልኮ ድርጊቶችና አመለካከቶች ነው። “ተውሂድን እንከተላለን” የሚል ጀመዓ ይህንን ይናገራል ትላላችሁ?

አህባሾች ማለት እነዚህ ናቸው። ይህንን እምነታቸውን አልቀበልም ያለውን ሰው ነው ነጋ ጠባ “ወሃቢ” እያሉ የሚዘልፉት። ሌላው ቀርቶ ድሮ የምንሰማቸውን “ጉጉት ከጮሀ ሰው ይሞታል፤ ማታ ማታ ጨው መሸጥ ለኪሳራ ይዳርጋል”፤ “ቤት ውስጥ ጥፍር ከተቆረጠ በረካ ይጠፋል ወዘተ” የመሳሰሉ ደካማ አባባሎችን የሚቃወመውን ሰው እንኳ “የወሀቢ በሽታ ይዞሃል” ይሉታል።

ያ ጀመዓ! የአህባሾች ትልቁ ፍላጎት ይህ ነው። አቂዳን በማስተማር ስም ቢያጭበረብሩም አንጃው የተመሰረበት ዋነኛ ምክንያት ይህ ነው። በተበሩክና ተወሱል ስም ሽርክና ባእድ አምልኮን ማንገስ!! አስተግፊሩላህ!!

ሙስሊሞች በተውሂድ ላይ ቀልድ አያውቁም!! ይህ የመዝሀብ ጉዳይ ወይም የሱኒና የሰለፊ ጉዳይ አይደለም። ይህ የሁላችንም መታወቂያ ነው። ተውሂድ ጠፋ ማለት ኢስላም ጠፋ ማለት ነው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከሂጅራ በፊት በነበረው የነቢይነት ዘመናቸው ያደረጉት ብቸኛ ትግል ተውሂድን ማስተማር ነው።

ዛሬ ተውሂድ ተስፋፍቷል። ለአላህ ምስጋና ይድረሰውና!! በተለያዩ የሙስሊም ሀገራትና መንደሮች ተንሰራፍቶ የነበረው ሽርክና ባእድ አምልኮ እየተወገደ ነው። አህባሾች ግን በኢስላም ጠላቶች እየታገዙ ሽርክና ባእድ አምልኮ ስር እንዲሰድ ለማድረግ ተነስተዋል። አላህ ደግሞ ለጠላቶቹ እንዲህ ይላቸዋል።

“እርሱ (አላህ ማለት) ያ መልእክተኛውን ቀጥተኛውን መመሪያ (ቁርአን) እና እውነተኛውን ሀይማኖት (ኢስላምን) አስይዞ በሁሉም ሀይማኖት ላይ የበላይ

ሊያደርገው የላከው ነው! አጋሪዎቹ (ሙሽሪኮቹ) ቢጠሉትም እንኳ!!" (ሱረቱ አል-ሰፍ፡ 9)

አላህ እውነትን ተናገረ!!!

## ክፍል አራት፡ የአህባሽና የኢብን ተይሚያህ ግብግብ

አህባሾች እንደ ትልቁ ጠላታቸው የሚያዩት ማንን ነው? *አቡ ጀህል፤ አቡ ለሀብ፤ ፊርአውን፤ ወሊድ ኢብን ሙጊራ፤ ቃሩን፤* ወዘተ ከመሰላችሁ ተሳስታችኋል። ጽዮናዊ አይሁዳዊያን፤ ሙናፊቆች፤ ሙሽሪኮች ወዘተ... የመሳሰሉ ጸረ-ኢስላም ሀይሎችም አይደሉም። አህባሾች ከነዚህ የአላህ ጠላቶች በላይ የሚጠሉት አንድ ሰው አለ።

ይህ ሰው ኩፍርና ኑፋቄን ወደ ኢስላም ካስገቡት የሙዕተዚላ እና የጀህሚያ ሰዎች፤ ማለትም ከነ ዋሲል ኢብን አጣእ እና ሰፍዋን ኢብን ጀህም ጋር የሚመደብ የኑፋቄ አቀንቃኝ (heretic) አይደለም። ሙስሊሞችን በግፍ ከጨፈጨፉት ጀንጂስ ኻን እና ሁላጉ ኻን (ሁለቱም የሞንጎል መሪዎች ናቸው) ጋርም አይሰለፍም። በአንጻሩ ግን በኢስላማዊ የብርሃን ጎዳና ላይ ከታዩት አብሪ ከዋክብት መካከል የሚመደብ ውድ የኢስላም ልጅ ነው። ኡለማእ ለርሱ ትልቅ ክብር አላቸው። ከዚህ በማስከተልም የዚህን ታላቅ ሰው ኢስላማዊ ተጋድሎና አህባሾች እርሱን የሚጠሉባቸውን ምክንያቶች እናያለን።

### *ሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህ- ታላቁ ሙጀዲድ*

በሶሪያና በቱርክ ድንበር አቅራቢያ የተወለደው *አቡል **አባስ ተቂዩዲን አህመድ ኢብን ተይሚያህ* በኢስላማዊው አለም ከታዩት አቡ ሀኒፋ፤ ኢማም ማሊክ፤ አል-ሻፊኢይ፤ ኢብን ሐንበል፤ አል-ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ አል-ጠበሪ፤ አል-ቁርጡቢ፤ አል-ገዛሊ፤ አል-ጠሃዊ፤ አል-ሱዩጢ፤ ወዘተ ከመሳሰሉት ድንቅ ምሁራን ጎራ ይመደባል። ይህ ሰው እስትንፋሱ ጸጥ እስክትል ድረስ ለኢስላም ለፍቷል። እንደ ኢብን ከሢር፤ አል-ደሀቢ፤ ኢብኑል ቀይም፤ አል-ሚእዚ ወዘተ.. የመሳሰሉትን ምርጥ የኢስላም ልጆች ያስተማረውም እርሱ ነው። ለዚህም ነው ዑለማእ *"ሼይኹል ኢስላም"* በሚል የክብር ስም የሚጠሩት። ("ምርጥ ኢስላማዊ ምሁራንን ያስተማረው ሼይኽ" ለማለት ነው)።

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በአንድ ሀዲሳቸው "ነቢዊያው ሱና ፈሩን እንዳይለቅ በሚል አቋም ከፍተኛ ትግል የሚያደርጉ እና በሱናው ላይ የሚዘፈዘፉ እድፎችን የሚያጠሩ የተሃድሶ ፈር ቀዳጆች (ሙጀዲዶች) በየምእተ አመቱ ይነሳሉ" በማለት ተናግረዋል (ሀዲሱን ቃል ቃል አልጠቀስኩትም፤ መልእክቱ ግን ይኸው ነው)።

በርግጥም ነቢያዊው ፈለግ ሳይበጠስ ለዚህ ዘመን የደረሰው አላህ የተሃድሶ ፈር ቀዳጆችን (ሙጀዲዶችን) በተለያዩ ዘመናት በማስነሳቱ ነው። ***ሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህም*** ከነዚያ የተሃድሶ ሀዋሪያዎች መካከል አንዱ እንደሆነ የአራቱም መዝሐብ ምሁራን ተስማምተውበታል።

## *አነጋጋሪው ምሁር*

ኢብን ተይሚያህ በሙስሊሙ አለም እጅግ አነጋጋሪ የሆነ ምሁር ነው። ሰበቡ ግን ሰውየው "ምግባረ-ብልሹ" ስለሆነ አይደለም። ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

1. ኢብን ተይሚያህ ከሰለፎች በኋላ ቀስ በቀስ እየተበላሸ የመጣውን ኢስላማዊ የህይወት መንገድ ከእድፍ ለማጥራት ያደረገው ትግል የብዙ ወገኖችን ጥቅምና ፍላጎት የነካ በመሆኑ "ሙስሊም ነን የሚሉ" በርካታ አከራፊዎች የስም ማጥፋት ዘመቻ ስለከፈቱበት
2. ኢብን ተይሚያህ ጸረ-ኢስላም ሀይሎች በኢስላም ላይ የሚያካሄዷቸውን ስውር ደባዎች በማጋለጡ የተቆጨት ጽዮናዊያን እና "የኢስላም ሳይንስ አዋቂዎች ነን" ባይ ኦሬንታሊስቶች (Orientalists) ነጋ ጠባ ስለሚያብጠለጥሉት
3. በሌላ ጽንፍ ያሉትና "የርሱን ስራ እናደንቃለን" የሚሉ አንዳንድ ጠማማ አንጃዎች (እንደ "ተክፊር ወል ሂጅራ" የመሳሰሉት) ለሚያካሄዷቸው አፈንጋጭ ድርጊቶች የኢብን ተይሚያህን ፈትዋዎች እንደማስረጃ የሚያቀርቡ በመሆናቸው እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ነው።

## *አህባሾችና ኢብን ተይሚያህ*

በክፍል ሶስት ጽሁፌ እንዳስረዳሁት አህባሾች በተበሩክና በተወሱል ስም በርካታ የሽርክና የባእድ አምልኮ ድርጊቶችን ይፈቅዳሉ። ለዚህም የቁርኣን አያዎችና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲሶችን እያጣመሙ በመተርጎም እንደማስረጃ አድርገው ያቀርባሉ። (ደኢፍ ሀዲሶችንና "መውዱእ" የሚባሉትን የፈጠራ ሀዲሶች መጠቀማቸው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው።)

ኢብን ተይሚያህ (ከተማሪዎቹ ጋር) ህይወቱን በሙሉ ሲታገለልት የኖረለት ታላቅ አላማ ከላይ የጠቀስኳቸው የሽርክ፤ የባእድ አምልኮ እና የኢ-አማኝነት (atheist) ተግባራት ከእስላማዊው አለም እንዲወገዱ ማስተማር ነው።

በተጨማሪም ሙስሊሞች በሰለፎች ዘመን የማይታወቁና በሸሪኣው ላይ የተለጣጠፉ አዳዲስ ፈጠራዎችን (ቢድዓ የሚባሉትን) እንዲተው ለማድረግ በሚል ኒያ የእድሜ ልክ ልፋት አድርጓል። እንደዚህ አይነት አቋም የነበረው ሰው ደግሞ የአህባሾች የጥቃት ዒላማ መሆኑ አይቀርለትም። ምክንያቱም ፍላጎታቸውና ጥቅማቸውን ነክቶባቸዋልና!

ዛሬ አህባሾች በተበሩክ፤በተወሱልና በተሰውፍ ስም የሚያጭብረብሩባቸውን ድርጊቶች ሁሉ ኢብን ተይሚያህ ከ700 አመታት በፊት በዝርዝር ጽፎልናል። "አስመሳዮች እንዳያታልሏችሁ!" በማለትም አስጠንቅቆናል። በሌላ በኩል አህባሾች እንደ ቅዱስ ጎዳና አድርገው የሚያሞግሱትና በተሰውፍ (Sufism) ስም በርካታ የኩፍርና የሽርክ ተግባራት የሚፈጸምበትን "የሪፋኢያ ጠሪቃ" በማስረጃ እየሞገተ ባዶውን አስቀርቶታል።

ነገሩ ግን ይህ ብቻ ነው? አይመስለኝም። አህባሾች በኢብን ተይሚይህ ላይ የከፈቱት ዘመቻ ሌሎች በርካታ መነሻዎችም ያሉት ሆኖ ነው የሚሰማኝ። ከነርሱም መካከል ሁለቱን ልጥቀስላችሁ።

1. አህባሾች *"መሕየዲን ኢብን ዐረቢ"* (1165- 1240) ለሚባለው ሱፊ ነኝ ባይ ልዩ ፍቅር አላቸው። ለታላቁ ቃዲ ለሼይኽ አብዱልቃዲር አል-ጀይላኒም ፍቅር እንዳላቸው ይናገራሉ። ኢብን ተይሚያህ ደግሞ ሁለቱን ሰዎች በተለያዩ ባህሮች ውስጥ ያሉ ፍጡራን አድርጎ ነው የሚያያቸው። ሼይኽ አብዱልቃዲር አል-ጀይላኒን እጅግ በጣም ይወዳቸዋል። "ታላቅ የአላህ ባሪያ" ይላቸዋል። ኢብን አረቢን በተመለከተ ግን ***"ሙስሊም ነው ከማለት ፈላስፋ ነበር ማለቱ ይቀላል"*** ይላል።

   ኢብን ተይሚያህ ሀቁን ነው የተናገረው። ምክንያቱም ራሱን "የበቃና የነቃ የተሰውፍ ኤክስፐርት" አድርጎ የሚመለከተው ኢብን አረቢ ***"ባሪያው ወደ ጌታ በተጠጋ ቁጥር የጌታው ጌታ ይሆናል፤ ጌታውም ወደ ባሪያው ሲጠጋ የባሪያው ባሪያ ይሆናል"*** በማለት ያስተምር ነበር። እንዲያውም ***"ጌታውና ባሪያው ሁለቱም አንድ ናቸው"*** ይላል። (ለማብራሪያው እነዚህን ዌብ ሳይቶች ተመልከቱ http://en.wikipedia.org/wiki/Ibn_Arabi http://www.scribd.com/doc/17234271/Syakh-alAkbar-Ibn-Arabi-brief-biography)

ይህ ምን ማለት ነው? "ኩፍር" አይደለም እንዴ? ኢስላም እንዲህ አይነት ፍልስፍና ያስተምራል? አላህና ባሮቹ በየትኛው ሚዛን ነው አንድ የሚሆኑት?

አህባሾች እንዲህ አይነት ፍልስፍና ያስተማረውን ሰው ነው "እንደ ታላቅ ሱፊ" አድርገው የሚጠቀሱት። ስለዚህ ኢብን ተይሚያህ ይህንን "ታላቅ ሼይኻቸውን" ስለነካባቸው በርሱ ላይ ቂም የማይይዙበት ምክንያት የለም ።

2. አህባሽን እየጠጋነኑ በሁለት እግር እንዲቆም ያስቻሉት ጽዮናዊያን እስራኤሎች ናቸው ይባላል። በርግጥም አንጃው የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ከጽዮናዊያን ጋር ጥብቅ ሽርክና እንዳለው ያስረዳሉ። እነ ሀጋይ ኤርሊች ***"ለወሃቢያ በሽታ ፍቱን መድኃኒት ነው"*** በማለት አህባሽን የመረጡልን ያለምክንያት አይደለም። ነገር ግን አንጃው በዚህ ብቻ የተገደበ አይደለም።

አህባሽ ከአሜሪካና ከእስራኤል ጋር እንደሚመሳጠረው ሁሉ "አረባዊነት እንጂ ኢስላማዊነት አውሬነት ነው" ከሚሉት የሶሪያ መሪዎችም ጋር "መርፌና ክር" ነው (ለስሙ ግን ሶሪያና እስራኤል ጠላቶች ናቸው)። ለመሆኑ "የአረባዊቷ ሶሪያ መሪዎች ምንድናቸው?" ብላችሁ ራሳችሁን ጠይቃችሁ ታውቃላችሁ?

በርግጥም እነ ሀፊዝ አል-አሳድና ባሻር አል-አሳድ አረቦች ናቸው። ሆኖም በዚህ አረባዊነት ላይ ሌላ አረማዊነት አለባቸው። እነዚህ ሰዎች ሙስሊሞች አይደሉም። ክርስቲያኖችም አይደሉም። እምነታቸው "*አለዊ*" ይሰኛል። (ይህ አምነት ***"ኑሰይራኒ"*** በሚል ስያሜም ይታወቃል)።

አንዳንድ ሰዎች "*አለዊ*" የሚባለውን እምነት ከ"ሺዓ ሙስሊሞች" አንጃ እንደ አንድ ቅርንጫፍ አድርገው ያዩታል። ይህ ግን ሙሉ በሙሉ ስህተት ነው። ሺዓዎቹ እንኳ "አለዊዎች" "ካፊሮች ናቸው" ነው የሚሉት። ምክንያቱ ደግሞ ግልጽ ነው። አለዊዎች *"አሊ ኢብን አቢ-ጣሊብ" በሰው መልክ የተገለጸው አምላክ ነው"* ይላሉ። እንዲህ የሚል ሺዓ በየትኛውም ሀገር የለም።

ስለ አለዊ በለጠ ለማወቅ የሚከተሉትን ዌብሳይቶች መርምሩ
http://en.wikipedia.org/wiki/Alawi
http://www.globalsecurity.org/military/intro/islam-alawi.htm)

አህባሾች እንደዚህ አይነት እምነት ያላቸውን የሶሪያ መሪዎች ነው የተጠጉት። እነርሱን ለማስደሰትም ልዩ ልዩ ችሮታዎችን በጉቦ መልክ

መክፈል ነበረባቸው። ለምሳሌ በሺላፋ ጉዳይ ከታላቁ ሰሀባ ከአሊ ኢብን አቡ-ጣሊብ (ረ.ዐ) ጋር የተጋደሉትን ሌላኛውን ታላቅ የኢስላም ልጅ ሞአዊያ ኢብን አቡ-ሱፍያንን (ረ.ዐ) "ፋሲቅ ወይንም "አወናባጅ" በማለት ሰድበዋቸዋል። ይህ ደግሞ የአለዊዎችን ፍቅር አስገኝቷል።

አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት አህባሾች ይህንን የሚያደርጉት "የሺዓ" አንጃዎችን ለማስደሰት አስበው አይመስለኝም። ከሺዓዎች ጋር ቢፋቀሩ ኖሮ በኢራን ከሚደገፈውና ሂዝቡላህ ከተሰኘው የሺዓ ቡድን ጋር በርካታ ውጊያዎችን ባልገጠሙ ነበር።

አህባሾች አለዊዎችን ለማስደት በሚል ምክንያት የሚከፍሉት ሌላኛው "ጉቦ" ደግሞ ሸይኹል ኢስላም አብን ተይሚያህን መሳደብ ነው። የዚህኛው መነሻ ደግሞ የሚከተለው ይመስለኛል።

በሶሪያ የተወለደው ኢብን ተይሚያህ እነዚህን "አለዊዎች" በደንብ ያውቃቸዋል። በመሆኑም ስለ- እምነታቸው ተጠይቆ በሰጠው አንድ ዝነኛ ፈትዋ

"እነዚህ ኑሰይራኒዎች (አለዊዎች) የለየላቸው አዋጣዊያን ናቸው፤ አይሁዶችና ክርስቲያኖች አንኳ ከነርሱ ይሻላሉ።" በማለት ተናግሮ ነበር።

(የኢብን ተይሚያህን ፈትዋ ከዚህ ዌብሳይት ማንበብ ትችላላችሁ http://shaykhulislaam.wordpress.com/2009/08/13/ruling-on-the-nusayrialawi-sect/...)።

ታዲያ አህባሾች በሁለት እግር እንዲቆሙ የረዷቸውን የአለዊ ተከታዮች ማንነት በዝርዝር ባጋለጠው ኢብን ተይሚያህ ላይ የበቀል ዘመቻ አያካሂዱም ትላላችሁ? እርግጠኛውን ነገር አላህ ነው የሚያውቀው። እኔ እንደማምነው ግን አህባሾች ከኢብን ተይሚያ ጋር የሚያካሄዱት ከላይ በዘረዘርኳቸው በርካታ ምክንያቶች ሳቢያ የተለኮሰውን የራሳቸውን ጦርነት ብቻ ሳይሆን አለዊዎችን ለማስደት በሚል ሰበብ የገቡበትን የውክልና ጦርነት ጭምር ነው።

## *የውግዘት ታክቲክ*

አህባሾች ኢብን ተይሚያህን ሲያወገዙ ልዩ ታክቲክ ነው የሚጠቀሙት። ከነርሱ ጋር ስትወያዩ የኢብን ተይሚያህን "ጥፋቶች" የሚዘረዝሩላችሁ "ተወሰሉ"ን እና "ተበሩክ"ን በማስቀደም አይደለም። እንደዚያ ካደረጉማ

ማንነታቸው ይጋለጣል። ከላይ የዘረዘርኳቸውን የኢብን አረቢና የአለዊ ጉዳዮችንም አያነሱትም። (እንዲያውም በእምነቱ ውስጥ ከቆዩት ጠንካራ ተከታዮቻቸው በስተቀር አዲስ ገቢዎቹ እንዲህ አይነቱን ነገር አያውቁትም። ቆየት ያሉት አባላቶች ወደ ዝርዝር ባይገቡም ላይ ላዩን ይነካኩታል)።

አህባሾች የኢብን ተይሚያህን ጉዳይ በቀጥታ የሚያያይዙት ከ"አቂዳ" ጋር ነው። በነርሱ አስተሳሰብ ኢስላማዊውን አቂዳ መበከል የጀመረው እርሱ ነው። አህባሾች "ዛሬ ወሃቢዎች የሚያራምዱትን አቂዳ ማስተማር የጀመረው ኢብን ተይሚያህ ነው" ይላሉ። ይህንን ለማጠናከርም እርሱ ያልተናገራቸውንና ያላደረጋቸውን ቅጥፈቶችንም ይጨምራሉ። (በዚህ ላይ ወደ ዝርዝሩ አልገባም። ነገሩን በጥልቀት ለማየት የሚፈልግ አንባቢ www.aicp.org የተሰኘው የአህባሾች ዌብሳይት በኢብን ተይሚያህ ላይ የሚያቀርባቸውን የፈጠራ ክሶች ይመልከትና http://shaykhulislaam.wordpress.com በተባለ ዌብሳይት ላይ ከተፃፈው ትክክለኛው የኢብን ተይሚያህ ታሪክ ጋር ያገናዝበው። ከዚያ በኋላ ሚዛናዊ ፍርዱን ይስጥ!!)

ያሳዝናል!! አህባሾች ሲፈልጉ "የወሃቢያ መንገድ በእንግሊዞች አሻጥር በአረቢያ በረሃ ላይ ሙሀመድ አብዱል ወሃብ በተባለ ሰው የተጀመረ ነው" ይላሉ። የ"ወሀቢ" ውግዘታቸውን የሚጀምሩት ግን ሼይኽ ሙሀመድ አብዱል ወሀብ ከመወለዳቸው 400 አመታት ያህል ቀድመው በኖሩት በሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህና በኢማም ኢብኑል ቀይም ነው።

አንድ ነገር ተናግሬ ላብቃ!! ሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህ ሌላው ቢቀር ለሙስሊሙ ኣለም ፋና ወጊ የሆኑ ተማሪዎችን አፍርቷል። እርሱን ያልወደደ ሰው ቢያንስ በዚህኛው ተግባሩ ብቻ ሊያከብረው በተገባው ነበር። ኢብን ተይሚያህ ካስተማራቸው ተማሪዎች አንዱ የሆነው ኢማዱዲን ኢብን ከሢር የሰራቸው ስራዎች ብቻ በዚህ ዘመን ትውልድ የሚታሰቡ አይደሉም።

ኧረ ለመሆኑ ሰዎችን ወደ አላህ መንገድ ከመጥራት ይልቅ ታላላቅ ኡለማዎችን ማክፈሩን እንደሙያ የያዙት አህባሾች ለኢስላም የሰሩት ጥሩ ነገር ምንድነው? መልስ የለም።

አላህ እንደነርሱ አያድርገን!!!

## ክፍል አምስት፡ *የአህባሽ መሰረታዊ ጠላቶች*

በክፍል አራት ጽሁፌ እንደገለጽኩት አህባሾች በመሰረታዊ ጠላትነት የሚፈርጁት እኛ የኢስላም ጠላቶች የምንላቸዉን ወገኖች አይደለም። የነርሱ ጠላቶች የሚከተሉት ናቸው። (ለማብራሪያው ነሐሴ 20/2003 የወጣውን ሰለፊያ ጋዜጣ፤ www.islamonline.net የተባለውን ዌብሳይት፤ እና የአህበሾችን ዌብሳይት ተመልከቱ)።

1. ***"ወሀቢያ"*** :- አህባሾች "ወሀቢያ" የሚሉት ከነርሱ ጋር በአቂዳና በመዝሀብ የተለየውን ሰው ብቻ አይደለም። እነርሱ የፈጠሩትን ጸረ-ተውሂድ የሆነ የአምልኮ ፍልስፍና የማይቀበለውን ሰው፤ ቡድን፤ ድርጅት በሙሉ "ወሀቢ" ነው የሚሉት። በዚህ ላይ የመዝሀብ ወይም የአቂዳ ልዩነት አያደርጉም። ሰውዬው አህባሾች የሚያምታቱበት የሻፊዒይ መዝሀብ ተከታይ ሆኖ ጸረ-ተውሂድ ፍልስፍናቸውን የማይቀበል ከሆነ "ወሃቢ" ይሉታል። ማንም ባልሰጣቸው ስልጣን "የተክፊር አዋጅ" ያውጁበታል።

   በዚህ መሰረትም የወሃቢያ ክሳቸውን ሺርክንና ባእድ አምልኮን ለማጥፋት በጽናት ከታገሉት የጥንቶቹ ሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህና ሼኽ ሙሀመድ አብዱል ወሃብ ይጀምሩታል። በማስከተልም በቅርቡ የሞቱትን እነ ሼይኽ ኢብን ባዝ፤ ሼይኽ አል-ኡሠይሚን፤ ሼይኽ አል-አልባኒ የመሳሰሉ ምሁራንን "ወሀቢ" በማለት ይወርዱባቸዋል። ወደኛ ዘመን ሲሻገሩም እንደ ዶ/ር ዛኪር ናይክ፤ ኢማም ዩሱፍ አል-ቀርዳዊና ዶ/ር አምር ኻሊድን የመሳሰሉ አለምአቀፍ ዳኢዎችን በውግዘታቸው ያዳርሳሉ።

   ከድርጅቶች መካከል ደግሞ "ራቢጠቱል ኢስላሚያ" (በሳኡዲ አረቢያ ያለ)፤ የአለም ሙስሊም ወጣቶች ማህበር (ዋና ጽህፈት ቤቱ በሳኡዲ አረቢያ የሚገኝ)፤ የአፍሪካ ሙስሊሞች ድርጅት (በኩዌት ሀገር የሚገኝ)፤ የመዲና ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ፤ የአፍሪካ አለም አቀፍ ኢስላማዊ ዩኒቨርሲቲ (በሱዳን ሀገር የሚገኝ) ወዘተ.. "የወሀቢያ ተቋማት" ተብለው ተፈርጀዋል።

   ክሱ ወደ መንግስታት ሲሸጋገር ሳኡዲ አረቢያን፤ ኳታርን፤ የተባበሩት አረብ ኢሜሬትንና ሱዳንን ይጨምራል። (አህባሾች በነዚህ ሀገሮች ምንም አይነት እንቅስቃሴ አያደርጉም)።

2. *"ኢኽዋነል ሙስሊሚን"፦* ይህ ላይ ላዩን ሲታይ የግብጹን "ኢኽዋነል ሙስሊሚን ፓርቲ" (The Muslim Brotherhood) የሚያመለክት ይመስላል። ነገሩ ግን እንደዚያ አይደለም። አህባሾች "ኢኽዋን" የሚሉት ስለሙስሊሞች አንድነትና በሸሪአ ህግ የመተዳደርን አስፈላጊነት የሚያበረታታ ማንኛውንም ግለሰብና ቡድን ነው። "ሙስሊሞች ከኢኮኖሚ ጥገኝነት ተላቀው ራሳቸውን መቻልና በአለም ዙሪያ ትልቅ የለውጥ ሀይል መሆን አለባቸው" የሚል ዜጋ፤ ፓርቲና እና መንግስት በአንድነት "ኢኽዋን" ተብሎ ይፈረጃል።

በሙስሊም ሀገሮች መካከል አለም አቀፍ ትስስር እንዲኖር ጥረት የሚያደርጉ ዳኢዎችና ምሁራን፤ ሀገሮች፤ የሀገር መሪዎች፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የሲቪክ ተቋማት ወዘተ... "ኢኽዋነል ሙስሊሚን" ተብለው ይወገዛሉ።በዚህ መሰረት አሁን በህይወት ከሌሉት ሙስሊም ምሁራን መካከል የግብጹ ሀሰን አል-በንና፤የፓኪስታኑ አቡል-አእላ መውዱዲ፤ የቱርኩ ነጅሙዲን ኤርባካን ወዘተ... "ኢኽዋን ተብለው" ተፈርጀዋል። ከፖለቲካ ፓርቲዎችም የግብጹ ኢኽዋነል ሙስሊሚን፤ የፓኪስታኑ ጀማአቱል ኢስላሚያ እና ሬፋህ የሚባለው የቱርክ ፓርቲ (እ.ኤ.አ. በ1998 "ህግ ወጥ" ተብሎ የፈረሰ) በዚህ ስር ይካተታሉ።

አህባሾች "ኢኽዋን" ብለው የፈረጇቸው መንግስታትና የአለም መሪዎች ስለመኖራቸው የማውቀው ነገር የለም (ማለትም በጽሁፎቻቸው ውስጥ አላነበብኩም፤ በኡስታዞቻቸው አንደበት ሲነገርም አልሰማሁም)። እንደምገምተው ከሆነ ግን የአሁኑን የቱርክ መንግስትና አመራሮቹን በኢኽዋንነት ሳይፈርጇቸው አይቀርም። የቀድሞው የማሌዥያ ጠቅላይ ሚኒስትር መሃቲር ሙሐመድም በአህባሾች ምዘና "ኢኽዋን" ሳይባሉ አይቀርም።

አህባሾች ግለሰቦችንና ድርጅቶችን "ወሀቢያ" በማለት የሚፈርጁበትን ምክንያት ከላይ ጽፌዋለሁ (ጸረ-ተውሂድ የሆነውን የእምነት ፍልስፍናቸውን ካልተቀበልን ነው "ወሃቢ" የምንባለው)። "ኢኽዋን" የሚለውን ፍረጃ የሚያካሄዱበት ምክንያትስ ምንድነው? ማለትም እነዚህ ግለሰቦች፤ ቡድኖችና ድርጅቶች በግልጽ ሲናገሩም ሆነ ሲጽፉ አህባሾች እንዳይነካባቸው በሚፈልጉት ጸረ-ተውሂድ አመለካከቶችና ድርጊቶች ላይ አያተኩሩም። አህባሾች "ወሃቢዎችን" የሚከሱበትን የአቂዳ ጉዳይ ሲሰብኩም አይታዩም።

ለምሳሌ ግብጻዊው ሀሰን አል-በንና "በሙስሊሞች መካከል ወንድማዊ ትብብርን ከፈጠርን ቀስ በቀስም ኢስላማዊውን መንግስት መመስረት

እንችላለን" የሚል ትምህርት ነበር ያስተማሩት። ፓኪስታናዊው መውዱዲ ደግሞ ሙስሊም ወጣቶች በካፒታሊዝምና በሶሻሊዝም አይድዮሎጂ እንዳይበከሉ በሚል ሀሳብ በርካታ ኢስላማዊ መጽሀፍትን ሲያዘጋጁ ነው የምናውቃቸው (አንዳንዶቹ መጽፍት ለልዩ ዓላማ የተጻፉ ቢሆንም እንኳ)። እንዲህ አይነት ሀሳብ ያንጸባረቀ ሰው በምን ስሌት ነው የአህባሾች ጠላት ሊሆን የቻለው?

መልሱን ባለፈው ክፍል ከጻፍኩት ጽሁፍ ታገኙታላችሁ። ማለትም አህባሾች የራሳቸውን ጦርነት ብቻ ሳይሆን የውክልና ጦርነትም ያካሄዳሉ። የጦርነቱን ሰፖንሰር ወደፊት እንመጣበታለን።

3. "***ኸዋሪጆች***"- "ኸዋሪጃ" የሚባል አንጃ በዘመናችን አለ? ለዚህ ጥያቄ የሚሆን አጥጋቢ ምላሽ የለኝም። እኔ እንደማምነው ግን "ኸዋሪጅ" ቢኖርም እንኳ ከጥንቱ አመፀኛ ቡድን ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም። ለምሳሌ በአማን ሀገር "ኢባዲ" የሚባል ቡድን አለ። ይህ አንጃ ስረ-መሰረቱ የጥንቱ የኸዋሪጃ አንጃ ነው ይባላል። ሆኖም የዘመናችን "ኢባዲ" ከጥንቱ "ኸዋሪጅ" በጣም ይለያል። ጥንታዊው ኸዋሪጃ "ሀጢአት የሰራ ሰው ይከፍራል" ይል ነበር። የአሁኑ ኢባዲ ግን "ወደ ኩፍር የማያደርሱ ሀጢአቶችን የሰራ ሰው ወንጀለኛ ይሆናል" ነው የሚለው እንጂ "ይከፍራል" አይልም። (ለዝርዝሩ ይህን ዊብሳይት ተመልከቱ http://en.wikipedia.org/wiki/Ibadism )

አህባሾች ግን በርካታ ምሁራንን፤ ግለሰቦችንና፤ ኢስላማዊ ቡድኖችን "ኸዋሪጅ" በማለት ይፈርጃሉ። የዚህኛውም ምክንያት እነርሱ "ወሀቢያ"ን ከፈረጁበት ሰበብ ጋር አይያዝም። ምክንያቱ በጌቶቻቸው የታዘዙበት የውክልና ጦርነት ነው።

አህባሾች "ኸዋሪጅ" የሚሏቸው ሙስሊም ህዝቦች አመጸኛ መሪዎችን እንዲታገሉ፤ የሸሪዓ ህግን በሚችሉት መንገድ (በጂሀድም ጭምር) ተግባራዊ እንዲያደርጉና ዲናቸውን ከጽዮናዊያንና ከምዕራባዊያን ስውር ደባዎች እንዲጠብቁ ያስተማሩ ምሁራንን ነው። ሀገራቸውን ነጻ ለማውጣት የሚታገሉ ኢስላማዊ የነጻነት ንቅናቄዎችንም "ኸዋሪጅ" ይሏቸዋል።

በዚህ መሰረት አህባሾች "የኸዋሪጅ" ክሳቸውን ሲጀምሩ 100 አመታት ወደ ኋላ ይሄዱና ሰይድ ጀማሉዲን አል-አፍጋኒን ያወግዛሉ። ይህ ሰው የሙስሊም ሀገራትን በወረራ የያዙት ቅኝ ገዥዎች (ኮሎኒያሊስቶች) በሙስሊሞች ላይ በሚፈጽሙት ግፍ ልቡ በመነካቱ *"የዓለም ሙስሊሞች ከዚህ ውርደት መውጣት የሚችሉት አንድ ሆነው*

በሚያደርጉት የተሳሳተ ትግል ነው" የሚል ታላቅ ራእይ ይዞ ሲያስተምርና በአለም ዙሪያ ሲንከራተት ነበር የኖረው። አህባሾች ግን "ሽዋሪጅ ነው" ይሉታል። ከርሱ በማስከተልም የሶሪያውን ሪሺድ ሪዳን ይረግማሉ።

በሶስተኛ ላይ ግን በግብጻዊው ሰይድ ቁጥብ ላይ ባለ በሌለ ሀይላቸው ይረባረቡበታል። አስገራሚ የፈጠራ ክሶችንም ያከናንቡታል። አህባሾች ከኢብን ተይሚያህ ቀጥሎ የሚጠሉት ሰው ቢኖር ሰይድ ቁጥብ ነው። ከዚያም በዚህ ረድፍ በሚሰለፉት እነ ፈትሒ የኩን (የሊባኖስ ኢስላማዊ ፓርቲ መሪ) ላይ ውግዘታቸውን ይወረውራሉ። ወደ ኢራን ይሻገሩና አያቱላህ ሩሑላህ ኾሜይኒን የሚችሉትን ያህል ይረግማሉ (በዚሕኛው ክስ ሱኒና ሺዓን አይለዩም)።

ከድርጅቶች ደግሞ "ኢስላማዊ ነኝ" የሚለውን የነጻነት ታጋይ በሙሉ ያወግዙታል። ለፍልስጥኤም ነጻነት የሚታገሉት ሀማስና ጂሀዱል ኢስላሚያ፤ ሊባኖስን ከእስራኤል ነጻ ለማድረግ የሚታገለው ሂዝቡላህ፤ ለሶሪያ ህዝብ ነጻነት የሚታገለው ሀረካቱል ኢስላም (ብዙ ሀይል የለውም) ወዘተ... ይዘለፋሉ። የእርግማን ናዳ ይወርድባቸዋል። በርካታ የፈጠራ ክሶችም ይቀርብባቸዋል።

አህባሽ ጠላቶቹን በዚህ መልኩ ፈርጇቸዋል። ከላይ እንዳያችሁት አንጃው "ጠላቴ ናቸው" የሚላቸው በሙሉ ሙስሊሞች ናቸው። አስተግፊሩላህ!!

ለመሆኑ አንጃው ማን ላይ ቆሞ ነው ይህንን ፍረጃ የሚያጧጡፈው? የልብ ወዳጆቹ እነማናቸው? ይህንን ጉዳይ በሚቀጥለው ክፍል እንዳስሰዋለን።

አላህ ከአህባሽና ከፈተናው ይጠብቀን። እርሱ የመረጠልንን ቀጥተኛውን ሀይማኖት በጥበቡ ይጠብቀው። አሚን!!

## ክፍል ስድስት፡ *የአህባሽ ልባዊ ወዳጆች*

በክፍል አንድ ጽሁፌ አህባሽን የሚወክለው "ጀምኢያቱል መሻሪኢል ኼይሪያቱል ኢስላሚያህ" (Association of Islamic Charitable Projects) የሚባል ድርጅት እንደሆነ ተናግሬአለሁ። ይህ ድርጅት በዋናነት የአህባሾችን ፍልስፍና ያስፋፋል። የድርጅቱን የገቢ ማሰባሰቢያ ስራዎችንም ያከናውናል። በተወሰነ መልኩም በማህበራዊ አግልግሎት ተግባራት ላይ ሲሳተፍ ይታያል።

ድርጅቱ በገሀድ እንደሚታየው በጣም ጽንፈኛ (fanatic) ነው። በዚህም የተነሳ በሙስሊሞች ያለው ተቀባይነት የደከመ ነው (በሰላሳ አመታት ውስጥ ግማሽ ሚሊዮን ተከታዮችን እንኳ አላፈራም)። እንደ ማህበር ሲታይ ግን በጣም ጠንካራ ነው። መዋቅሩ ውስብስብ ነው። የሀብቱ ብዛት ከአቅሙ በላይ ነው። በአለም ዙሪያ ያልደረሰበት ቦታ የለም።

በየሀገሩ የየራሱ መስጂዶች፤ የሰበካ መርከዞች፤ መድረሳዎች፤ ላይብረሪዎች፤ የስብሰባ አዳራሾች፤ የሬዲዮ ጣቢያዎች፤ ጅምናዚየሞች፤ማተሚያ ቤቶች፤ የኢንተርኔት መረቦች ወዘተ... አሉት። እነዚህን ተቋማትና አገልግሎቶች የሚያንቀሳቅስበት በቂ የሆነ ሀብትም አለው። ታዲያ ግማሽ ሚሊዮን ያህል ተከታዮችን እንኳ ለማፍራት ያልቻለው ይህ አንጃ በአለም ዙሪያ ሊዳረስ የቻለው እንዴት ነው? የፋይናንስ ምንጩ ከወዴት ነው? በዚህ ክፍል በነዚህ ጉዳዩች ዙሪያ ቆይታ እናደርጋለን።

### *አህባሽና የምዕራብ ወዳጆቹ*

አህባሾች ከምእራባዊያን ጋር የተወዳጁት መቼ ነው? ይህ በቀላሉ የማይመለስ ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ሙስሊሞች የአህባሽን መኖር የሰሙት ከምስረታው በኋላ በጣም ዘግይቶ ነው። ሆኖም በሁለት ነገሮች ላይ መግባባት ይቻላል።

- አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት አህባሽ ከምዕራቡ ጎራ ጋር መፋቀር የጀመረው ከሴፕቴምበር 11/2001 ወዲህ አይደለም። ከዚያ በፊት 6 ዓመታት ቀደም ብሎ እንኳ ከምዕራባዊያን ጋር ሚስጢራዊ ግንኙት አለው ተብሎ ይነገር እንደነበር ኒዛር ሐምዛ እና አር. ሀሬር ዲክሜጆን የተባሉት የቤይሩት የአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ ምሁራን "A Sufi Response to Political Islamism: Al-Ahbash of Lebanon" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፍ ገልጸዋል፡

- ከሴፕቴምበር 11/2001 ወዲህ ግን ተፈላጊነቱ ጨመረ። አሜሪካና ሌሎችም ምዕራባዊያን እርሱና መሰሎቹን ማጠናከርና ማስፋፋት ጀመሩ።

አህባሽ ምዕራባዊያንን ለመሳብ የቻለው በሶስት ምክንያቶች ነው።

1. አንጃው "እስላማዊ መንግስት" የመመስረት አላማ ያላቸውን የፖለቲካ ድርጅቶችና የነጻነት ንቅናቄዎች በሙሉ ይቃወማል። ይህ ተቃውሞ "በሀጋዊ መንገድ በምርጫ ተሳትፈን እናሸንፋለን" የሚሉትን ፓርቲዎችንም ይጨምራል። እንዲህ አይነት አቋም ደግሞ ምእራባዊያንን ይማርካል።
2. አንጃው ዘመናዊነትንና እስልምናን አንድ ላይ ማጣጣም ይቻላል ባይ ነው። በመሆኑም የዘመኑ እድገት ባስገኛቸው ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች መጠቀም አለብን ይላል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች ከሸሪዓ ህግ ጋር የሚቃረኑ ቢሆኑም እንኳ ዘመኑ ያስገኛቸው በመሆኑ እና ከዓለም ተጨባጭ ሁኔታ ውጭ መሆን ስለማንችል ለኛ በሚስማማ መልኩ አስተካክለን መጠቀም አለብን ባይ ነው። ("አህባሾች የባንክ ወለድን ከካፊሮች እንጅ መብላት ይቻላል" የሚሉት በዚህ ስሌት ነው)።
   ከዚህ ሌላ አንጃው ዘመኑን የሚመለከትበትን መነጽር ምዕራባዊያኑ በሚፈልጉበት መንገድ አስተካክሏል። ለምሳሌ "አህባሾች በዚህ ዘመን ዳእዋ እንጂ ጂሀድ አያስፈልግም። ዘመኑ የጭንቅላት እንጂ የጉልበት ዘመን አይደለም" ባይ ናቸው።
3. ሌላው አስገራሚ ነገር አንጃው "እስልምና ሁሉን አቀፍ የህይወት መንገድ ነው" የሚለውን እስላማዊ እውነታ የማይቀበል መሆኑ ነው። ለምሳሌ አንጃው "እስልምና የአካባቢውን ባህል ሳይነካ ነው መፈጸም ያለበት" ይላል።

ከላይ የዘረዘርኳቸው ነጥቦች በሙሉ የምእራባዊያንን ፍላጎት ያማሏሉ። ለዚህም ነው ለአህባሽ እውቅና ሰጥተው በአለም ዙሪያ የበተኑት። አውሮፓ አውስትራሊያ፤ ጃፓን፤ እስያ ላቲን አሜሪካ፤ አፍሪካ ያልደረሰበት ቦታ የለም።

## አህባሽና ጽዮናዊያን

በአህባሽ መመስረት ከማንም በላይ የተደሰቱት ጽዮናዊያን ናቸው። እነዚህ ሀይሎች "ለሁለት ሺሕ አመታት ተሰቃይተን የመሰረትናትን የቅድስት ሀገራችንን (የእስራኤልን) ህልውና የሚፈታተነው ብቸኛ ሀይል እስልምና በመሆኑ ባለን አቅም ሁሉ እርሱን ማዳከም አለብን" ከሚል አቋማቸው ተነስተው ይህንን ቡድን ተጠግተውታል። ከእርሱ የሚጠብቁት በርካታ ነገር አለ። እርሱን ከመናገሬ በፊት የተወሰኑ ማስተካከያዎችን መስጠት እፈልጋለሁ።

"አህባሽ በጽዮናዊያን ይደገፋል የሚለውን አባባል" አንዳንድ ሰዎች "የአንጃው መስራች ራሳቸው ይሁዲ ናቸው" በማለት ይወስዱታል። ይህ ፍጹም ስህተት ነው። ሰውዬው በሀገር ቤትም ሆነ ከሀገር ውጪ በደንብ የሚታወቁ ሰው ናቸው። ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸውም ይታወቃሉ። ይሁዲ የሚባል የዘረግ ሀረግ የለባቸውም። ያለ ማስረጃ "ይሁዲ ናቸው" ብሎ መናገር ሀጢአት ይመስለኛል። ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። ደግሞም ከርሳቸው ጋር በአስተሳሰብ የማይጣጠሙ በርካታ ዘመዶችና አማኞች ስላሏቸው የነርሱን ሞራል መጠበቅ ግዴታችን ነው። (ለምሳሌ ከሼኽ አብዱላህ ሐረሪ ጋር እድሜ ልካቸውን ሲፋለሙ የኖሩት ሀጂ ዩሱፍ አብዱራህማን የሼኽ አብዱላህ አማች ናቸው።)

"ሼኽ አብዱላህ በ1948 እስራኤልን ጎበኙ" የሚባለውም ስህተት ነው። እሳቸው አልቁድስን (እየሩሳሌምን) ነው የጎበኙት። አል-ቁድስ ከ1967 በፊት በዮርዳኖስ ስር ነበረች እንጂ የእስራኤል ግዛት አይደለችም። እስራኤል በ1967 የስድስቱ ቀን ጦርነት አል-ቁድስን፤ ምእራባዊ ዳርቻን፤ የሲናይ በረሃን፤ የጎላን ኮረብታንና ጋዛን በወረራ ነጠቀች። የሲናይ በረሃን በ1979 ለግብጽ ስትመልስ ሌሎቹን ግን እስካሁን እንደያዘች ነው።

ሆኖም አል-አህባሽ "የጽዮናዊያን ተልእኮ አሰፈጻሚ ነው" የሚለው አባባል በደንብ ያስኬዳል። ለዚህ ቀላሉ ማስረጃ አቋሙና ድርጊቱ ነው። ስለዚህ በዚህኛው ላይ "ሐጢአተኛ" የምንባልበት ምክንያት የለም። ከድርጊቶቹም መካከል በሊባኖስ ህዝብ የሚታወቁትን ልጥቀስ።

1. አህባሽ በሊባኖስ ውስጥ በሚያደርገው እንቅስቃሴ በእስራኤል ላይ መሳሪያ ያነሱ ሀይሎችን በሙሉ ይቃወማል።

2. የፖለቲካ ማኒፌስቶውና ሌሎች ሰነዶቹ ስለ ፍልስጥኤም ነጻነት ቢናገሩም አህባሽ "በሰላማዊ መንገድ እስከተፈጸመ ድረስ" የሚል አቋም ነው ያለው። በአህባሽ አመለካከት በወረራ የተያዙት ፍልስጥኤማዊያን እሰራኤልን ከመለመን ውጪ ለነጻነታቸው መዋጋት የለባቸውም።
3. ከፍልስጥኤም ድርጅቶች መካከል የፈትሕ አንጃን (PLO) ይደግፋል። እንደ ሀማስና ጂሀዱል ኢስላሚያ (Islamc Jihad) የመሳሰሉትን ይቃወማል። "ለፍልስጥኤም ነጻነት ደንቃራ የሆኑት እነዚህ ጦርነት ናፋቂ የ"ሽዋሪጃ" ቡድኖች ናቸው ይላል"።
4. በ2006 በእስራኤልና በሒዝቡላህ መካከል በተደረገው ውጊያ መላው የሊባኖስ ህዝብ፤ የፖለቲካ ቡድኖች፤ ሲቪክ ማህበራትና የሀይማኖት መሪዎች የሊባኖስን ሉአላዊነት ላለማስደፈር ለሚዋጋው ሂዝቡላህ ድጋፋቸውን ሲሰጡ አህባሽ ግን ሂዝቡላህን ይቃወም ነበር። (ጦርነቱ ሲጀምር ሂዝቡላህን "በጠብ አጫሪነት" ከሰሰው። የእስራኤል ጥቃት ሲበረታ ደግሞ "ያለ አቅሙ ጦርነት ጀምሮ ህዝባችን አስጨፈጨፈ" ይል ነበር። ደግነቱ ግን ህዝቡላህ በጦርነቱ ማብቂያ ላይ በዘመናዊው አረብ-እስራኤል ጦርነት ታሪክ ተሰምቶ የማይታወቅ ድል ነው የተጎናጸፈው)።
5. ሊባኖስ ውስጥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የፍልስጥኤም ስደተኞች አሉ። ከሊባኖስ ክርስቲያኖች መካከል አክራሪ የሆኑት "ፍልስጥኤማዊያኑ ሊወጡን ነው፤ ወደ ሀገራቸው ይለመሱ" የሚል ቅስቀሳ በየጊዜው ያካሂዳሉ። አህባሾችም ከነዚህ ቡድኖች ጋር ወግነው "ፍልስጥኤማዊያኑ ከዚህ ይጥፉ፤ ሽብር የሚያስፋፉት እነርሱ ናቸው" በማለት ይቀሰቅሳሉ። (ችግሩ የመጣው እስራኤል ፍልስጥኤማዊያኑን አላስገባም በማለቷ ነው እንጂ ፍልስጥኤማዊያኑ ወደ ሀገራቸው መመለሱን ስለጠሉት አይደለም። አህባሾች ይህንን አያውቁም ማለት ነው? በደንብ ያውቁታል!)

ይህን ሁሉ የሚፈጽመው "አል-አህባሽ" የእስራኤል ደጋፊ እንዳይባል ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል። በእስራኤል ውስጥ የሚያደርገው እንቅስቃሴ የለም። በሊባኖስ ውስጥ እንኳ ከይሁዲዎች ጋር ሽር ጉድ አይልም። ይህ ዘዴኛነቱ እንኳን ለእኛ አህባሽን በደንብ ለሚያውቁት ሊባኖሳዊያን ግራ ነው። ታዲያ የግንኙነት መስመሩ እንዴት ነው? ይህ ፈታኝ ጥያቄ ነው። ነገሩን በደንብ ስናስተውልና አንዳንድ መረጃዎችን ስናመዛዝን ግን የሚከተለውን እናገኛለን።

አህባሽ ከምእራባዊያን ጋር ያለውን ግንኙነት አይደብቅም (ልደብቅ ቢል እንኳ አይችልም)። ከጽዮናዊያኑ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ግን በቀጥታ አይከናወንም። በምዕራባዊያን፤ እንደ አህባሽ በ"ወሃቢ" ላይ ቂም ካላቸውና ለጸረ-እስላም ሀይሎች ነፍሳቸውን ከሸጡ "ሙስሊም ነን" ባይ መንግስታት፤ የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች አማካኝነት ነው የሚፈጸመው። ስንቶቹ በዚህ ሰልፍ ውስጥ እንደሚገቡ መናገሩ ይከብዳል። የተወሰኑት ግን የሚከተሉት ይመስሉኛል።

1. ***የዮርዳኖስ መንግስት*** - "በሼይኽ ሙሀመድ አብዱል ወሃብና በሙሀመድ ኢብን ሱኡድ የተመሰረተው የወሀቢያ ንቅናቄ በመካና መዲና ላይ የነበረኝን ሙሉ ስልጣን ወስዶብኛል" የሚለው የዮርዳኖስ መንግስት "ወሀቢ" የሚለውን ቡድን ለሚቃወም ሀይል ሁሉ እጁን በሰፊው ይዘረጋል። ከ1980 ወዲህ ደግሞ ከእስራኤል ጋር የነበረውን ቂም ረስቶ ፍቅር በፍቅር ሆኗል። አህባሽም በዚህ በኩል ወደ እስራኤል የማይደርስበት ምክንያት የለም።
2. ***ቱርክ***- የአሁኑ የቱርክ መንግስት ለእስልምና ተቆርቋሪ ነው። ከዚያ በፊት የነበሩት መንግስታት ግን ጸረ-ሙስሊም ናቸው። እነዚያ ሀይሎች ከስልጣን ቢወርዱም አሁንም ጠንካራ ናቸው።
   ቱርኮች ልክ እንደ ዮርዳኖስ "በወሃቢያ" ላይ ከፍተኛ ቂም አላቸው። እነርሱም በፈንታቸው "በመላው የሙስሊም አለም የነበረንን የኡቶማን ቱርኮች ሰፊ የሆነ የሽሊፋ ስልጣን የገረሰሰብን የወሀቢያ ንቅናቄ ነው" ይላሉ።
   ቱርኮች ከእስራኤል ጋር ያላቸው ግንኙነት የታወቀ ነው። ስለዚህ አህባሽ በዚህኛውም መንገድ ወደጽዮናዊያኑ ሊደርስ ይችላል። የአህባሽ-እስራኤል ግንኙነት የሚቀላጠፈው ግን በመንግስት ደረጃ ብቻ አይመስለኝም። በርካታ ግለሰቦችና የይሁዲ ቡድኖች ይሳተፉበታል። በኢስታንቡል የሚኖሩት ከ30 ሺህ የሚበልጡ ይሁዲዎች አንዱ ስራቸው እንዲህ አይነቱን የግንኙነት ሰንሰለት ማጥበቅ ነው።
3. ***አሜሪካና እንግሊዝ***- እነዚህ መንግስታት በዚህ ጨዋታ ውስጥ የገቡበት ምክንያት በደንብ ስለሚታወቅ ወደ ዝርዝሩ አልገባም።

የአህባሽ ልባዊ ወዳጆች እነዚህ ናቸው። "አህባሽ ከወዳጆቹ ምን ጥቅም ያስገኛል" የሚለውን ጥያቄ መመለስ አያስፈልግም! ስንት እንደሚከፈለውም በትክክል አናውቅም። አህባሽ ለነርሱ የሚፈጽመው ተልእኮ ግን ወደኛ ድረስ

መጥቷል። ይህ ጉደኛ ቡድን "ወሃቢዎች ያጠፉትን አቂዳ አስተካክላለሁ" ነው የሚለው!! ይገርማል። ኢስላምን እያጠፉ አቂዳን ማስተካከል?!!

እነርሱ ኢስላምን ለማጥፋት መጥተዋል። አላህ ግን ኢስላምን ይጠብቀዋል። አላሁ አክበር!!

## ክፍል ሰባት፡ አህባሽ እና "ሱፊ"

በቅርቡ የአንድ ታላቅ መስጊድ ኢማም በሱፊያ ላይ ያተኮረ ኹጥባ ማድረጋቸውን ሰማሁ። ታዲያ አንዳንድ የፌስቡክ ጓደኞቼ ኢማሙ "እኛ ወሀቢዎች አይደለንም፤ እኛ ሱፊ ነን፤ አሁን ጊዜው የሱፊያ ነው፤ ሱፊያ ደግሞ የሰሀባዎችና የነቢያችን መንገድ ነው፤ ወዘተ..." ብለው ተናግረዋልና ስለዚህ ጉዳይ የምታውቂው ነገር ምን አለ?" የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝ።

በሰማሁት አባባል በእጅጉ ተገረምኩ። አዘንኩ!! ምን እንደማደርግም ግራ ገባኝ። ኢማሙ እንዲህ አይነት ተራ ንግግር በኹጥባ ላይ ማድረጋቸውን ለማመን ቢከብድም በራሴ መንገድ ባደረግኩት የማጠራት ሙከራ ነገሩ እርግጥ መሆኑን ተረዳሁ።

በሌላ በኩል በዚያች ለነዚያ ጓደኞቼ የሚሆን ምላሽ በዚያች ቅጽበት መስጠቱ ከበደኝ። ምክንያቱም የተሰውፍ መጽሀፍት በአጠገቤ የሉም (መካሺፉል ቁሉብ ከሚለው የኢማም አቡ-ሐሚድ አል-ገዛሊ መጽሀፍ በስተቀር)። በኢንተርኔት ላይ በተሰውፍ ስም የተለቀቁ ዌብሳይቶች ደግሞ ከጥቂቶቹ በስተቀር ምንም እምነት የሚጣልባቸው አይደሉም። ነገር ግን አህባሽ ሙስሊሞችን ከሚያጭበረብርባቸው ዘዴዎች አንዱ "እኛ ሱፊዎች ነን" የሚለው ፕሮፓጋንዳ እንደሆነ ስለማውቅ ዝም ከማለት የቻልኩትን ያህል ልጻፍቸው በማለት ተነሳሁ።

ወደ ዋናው ጽሁፍ ከመግባታችን በፊት ግን መጠነኛ ማሳሰቢያ አለኝ። ይህንን ጽሁፍ ስጽፍ መነሻ የሆነኝ በአብዛኛው ድሮ ካነበብኩት ሀሳብ የተረፈኝ መጠነኛ እውቀት እንጂ በቅርብ ጊዜ ያነበብኩት መረጃ አይደለም። ስለዚህ የመረጃ ክፍተት ሊኖር እንደሚችል አምናለሁ። የጽሁፌን መልእክት ለማገናዘብ የሚፈልግ አንባቢያ ሰይድ አቡል-አእላ መውዱዲ የጻፉትን Towards Understanding Islam፤ አቡል ሐሚድ አል-ገዛሊ የጻፉትን አል-ኢሕያእ ኡሉመ·ድዲን እና መካሺፉል ቁሉብ፤ ሼኽ አብዱልቃዲር አል-ጀይላኒ የጻፉትን "አል-ጉንያ ሊጣሊብ ጠሪቀል ሐቅ"፤ ታዋቂው ገጣሚ ፈሪዱዲን አጣር የጻፈውን "ተዝኪራቱል አውሊያ" ወዘተ.. የመሳሰሉ መጽሀፍትን መመርመር ይችላል።

## ተሰውፍ

“ተሰውፍ” (Sufism) በጥሬ ትርጉሙ “ሱፍ መልበስ” ማለት ነው። በተገቢው መንገድ ሲተረጎም ግን “የልብ ጥራት” ማለት ነው። ሙስሊም የሆነ ሰው ልቡ በአካሉ ከሚያደርገው ኢባዳ ጋር በእኩል ሁኔታ እንድትራመድለት ሲፈልግ ልዩ ልዩ ጥበባዊ ዘዴዎችን የሚማርበት መንገድ ነው- “ተሰውፍ”። ይህም ልብን ከልዩልዩ የልብ በሽታዎች ማጥራት ማለት ነው።

በቁርአንና በሀዲስ በስፋት እንደተገለጸው ሰዎች ከፈጣሪ ጋር ያላቸውን ትስስር የምታበላሽባቸው አንዲት አካል አለች። እርሷም ልብ ናት። ሙእሚኖች ቁርኣናዊ ግዳጃቸውን በተገቢው መንገድ ለመወጣት ከፈለጉ ልባቸውን ከበሽታ ማጥራት አለባቸው። በሌላ በኩል ፈጣሪያችን አላህ (ሰ.ወ.) ለምንሰራቸው መልካም ስራዎች የሚከፍለንን ምንዳ (አጅር) የሚወስነው የልባችንን ጥራት በመመዘን ነው። በከፍተኛ የልብ ጥራት የአንድ ብር ሰደቃ የሰጠ ሰው ከፍተኛ ሽልማት አለው። ሰውየው መካከለኛ የልብ ጥራት ካለው ሽልማቱ ያንስበታል። የልብ ንጽህናው በጣም የጎደፈ ሰው ደግሞ ሽልማቱ እጅግ ዝቅተኛ ነው (ሰውዬው መቶ ብር ቢሰጥ እንኳ በንጹህ ልብ አንድ ብር የሰጠውን ሰው ያህል ሽልማት አያገኝም)። ልቡ ሙሉ በሙሉ የቆሸሸ ሰው ግን ከአላህ ዘንድ ምንም ሽልማት አያገኝም።

እንግዲህ ይህንን የልብ ጥራት ማምጣት የሚቻለው እንዴት ነው? ኡለማ ለዚህ ጥያቄ የሚሆን ምላሽ ሲፈልጉ ነው “ተሰውፍ” የሚባለው አስገራሚ (አንዳንድ ጊዜ አወዛጋቢ) ኢስላማዊ የትምህርት ዘርፍ የተወለደው።

ተሰውፍን እንደ አንድ የትምህርት ዘርፍ አድርጎ ማስተማር መቼ እንደተጀመረ በትክክል አይታወቅም። በርካታ ምንጮች ታዋቂዎቹን የበስራ ምሁራን ሐሰን አል-በስሪንና ራቢአቱል አደዊያን እንደ ጀማሪዎች ይጠቅሳሉ። ለመጀመሩ ሰበብ የሆነውም በጊዜው የነገሰው የልዩ ልዩ ፊርቃዎች (ሺዓ፤ ኻዋሪጅ፤ ሙርጂአ፤ ጀህሚያ፤ ሙእተዚላ፤ ቀደሪያ፤ ጀብሪያ ወዘተ...) ሽኩቻ እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ።

በተሰውፍ ላይ የሚያተኩሩ መጽሀፍት መጻፉንም ማን እንደጀመረው በርግጥ አይታወቅም። እንደሚመስለኝ ከሆነ የተሰውፍ መጽሀፍት መጻፍ የጀመሩት ከሂጅራ በኋላ በ4ኛው መቶ አመት ገደማ፤ ማለትም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ከ900 አ.ል. በኋላ ሳይሆን አይቀርም። በ10ኛው፤ በ11ኛውና በ12ኛው ክፍለ

ዘመናት ፈሪዱዲን አጣር፤ አቡ ሀሚድ አል-ገዛሊ፤ አህመድ አል-ሪፋኢ፤ ሼኽ አብዱልቃዲር አል-ጁይላኒ ወዘተ... የመሳሰሉ ምሁራን በተሰውፍ ላይ ያተኮሩ በርካታ መጽሀፍትን አበርክተዋል።

## *ተሰውፍና የልብ በሽታዎች*

ልባችን የሚቆሸሸው በተለያዩ በሽታዎች ነው። እነዚህ የልብ በሽታዎች ያሉበት ሰው ኢባዳውን በወጉ አያደርግም። ውሎውና ድርጊቶቹ ከእስላማዊ አዳብ ጋር አይገጥሙለትም። ከግለሰቦችና ከማህበረሰቡ ጋር ያለው ግንኙነትም የተስተካከለ አይደለም። ይህ ደግሞ በዚህች አለም ብቻ ሳይሆን በወዲያኛውም አለም ታላቅ አደጋን ያስከትልበታል። ስለዚህ ከአደጋው ለመዳን ልቡን ከበሽታ ማጥራት ይጠበቅበታል።

የሰውን ልብ ከሚያደርቁትና ኢማንን ከሚያጎድሉት በሽታዎች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- ኒፋቅ፡- የሙናፊቅነት ስሜት
- ጡግያን፡- ጥመት
- ኪብሪያእ፡-ኩራት
- ጁብር፡ ትዕቢት
- ሪኣእ፡- ልታይ ልታይ ማለት
- ዘን፡- ከንቱ ጥርጣሬ
- ገፍላን፡- መሰላቸት
- ሻህዋእ፡- ከገደብ ያለፈ ስጋዊ ፍላጎት
- ወዘተ...

አላህና መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ከነዚህ በሽታዎች እንድንጠቀቅ አስተምረውናል። የተሰውፍ ሰዎች ከነዚህ በሽታዎች የሚሆኑ መድሓኒቶችን ነው የሚያስተምሩት። የነዚህ መድሃኒቶች ምንጭ ቁርአንና ሱንና ነው። ልቡን ከነዚህ በሽታዎች ያጠራ ሰው ዒባዳውን በታላቅ ኹሹእ (የአላህ ፍራቻ) ማከናወን ይችላል።

የተሰውፍ ኣላማ ከላይ ለተዘረዘሩት በሽታዎች መድሀኒት ማስገኘት ነው። ከነዚህ መድሀኒቶች መካከል ከሁሉም የሚበልጠው ዚክር (አላህን ማስታወስ ) ነው። ቁርኣን "ልቦች በዚክር ይረጥባሉ" በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷልና!!

እንግዲህ "ሱፊ" የሚባል ሰው ልቡን ከበሽታ ለመጠበቅ ሲል የተሰውፍን ጥበብ የሚከተል ማለት ነው። ይህ የተሰውፍ ጥበብ ደግሞ ከቁርአንና ከሀዲስ ጋር የማይጋጭ መሆን አለበት። በተጨማሪም ሰውየው ሌላውን ኢባዳ ትቶ ተሰውፍን ብቻ የሙጥኝ ብሎ መያዝ አይችልም። "ተሰውፍ" ሰውዬው በኢባዳ ላይ ብርቱ ሆኖ እንዲቆይ የሚረዱትን ጥበባዊ ዘዴዎች ያስተምረዋል እንጂ በራሱ የቆመ ለየት ያለ ኢስላማዊ ጎዳና ወይም የሽሪኣ ዘርፍ አይደለም።

ማንም ሰው የተሰውፍ ዘዴዎችን ሳይማር ኢባዳውን ማድረግ ይችላል። "ልቤ በትእቢትና በኩራት ተወጥራለችና ምን ይበጀኛል?" ብሎ የሚጨነቅ ከሆነ መድሓኒቱን ከተሰውፍ መንገድ መፈለግ ይፈቀድለታል።

እዚህ ላይ የታዋቂውን የሱፊ ጥበብ አዋቂ የሼኽ አብዱልቃዲር አል-ጂይላኒን ምሳሌዎች ልጥቀስ። ሼይኽ አል-ጂይላኒ "አል-ጉንያ ሊጣሊብ ጠሪቀል ሀቅ" በተባለ መጽሀፋቸው ውስጥ እንዲህ ይላሉ።

- መቼም ቢሆን አትማል፤ መማል ካስፈገለ ግን በአላህ ስም ብቻ ማል!
- በምላስህ አትዋሽ! ጥሩ ነገር ብቻ ተናገር!
- በመንገድ ላይ በእድሜው ካንተ የሚያንስ ሰው ቢያጋጥምህ "ከርሱ የተሻልኩ" ነኝ ብለህ አታስብ። ከዚህ ይልቅ በልብህ "ይህ ልጅ በምድር ላይ የኖረበት ዘመን ከኔ እድሜ ያንሳል። ስለዚህ ሀጢአቱም ከኔ ያነሰ ነው" በል።
- በእድሜው የሚበልጥ ሰው ከገጠመህ ደግሞ "ይህ ሰው በዚህች ምድር ላይ ከኔ እድሜ ለሚበልጥ ጊዜ ኖሯል፤ ስለዚህ ለአላህ ባደረገው ኢባዳ ከኔ ይበልጣል" በል እንጂ በመጥፎ ነገር አትጠርጥረው።

ደስ ይላል አይደል? ከማስደሱ ጋር መጠየቅ ያለበት ጥያቄ "ሼኽ አብዱልቃዲር የተናገሯቸው ነገሮች ከኢስላማዊው ሸሪዓ ጋር ይቃረናሉ ወይ?" የሚለው ነው።

ሼኽ አብዱልቃዲር የጻፉት ነገር ከኢስላማዊ ሸሪዓ ውጪ አይደለም። ይልቅ ኢስላማዊ ሸሪዓን በትክክል ለመተግበር ያግዛል። ተሰውፍ ማለትም እንዲህ ነው።

በዚህ መሰረት ነው ሙስሊሞች ልባቸውን ከበሽታ የሚፈውሱባቸውን ልዩ ልዩ ምክሮች የሚሰጡ መጽሀፍት መጻፍ የተጀመሩት። አንዳንድ መምህራንም

ሙሉ ጊዜያቸውን ለዚሁ ሰጥተው የማስተማሪያ ማእከላትን ያቋቋሙት ለዚሁ አላማ ነው።

## ተሰውፍ ሲበላሽ

ጥንት በሰላማዊ ሁኔታ የተጀመረው ተሰውፍ ከዘመናት በኋላ መስመሩን ሳተ። ሰዎችን በሸሪአ ላይ የሚያበረታታ መሆኑ ቀርቶ ከሸሪአ የሚያስወጣ መሆን ጀመረ። ለምሳሌ፤

- በተሰውፍ ስም ከሸሪአ ጋር የሚቃረኑ ተግባራትን መፈጸም ተጀመረ፤ ዳንስና ሙዚቃ እንኳ በተሰውፍ ስም ተፈቀዱ (ለምሳሌ በቱርክ ያሉትና “Whirling Dervishes” የሚባሉት የመውላዊ ጠሪቃ ተከታዮች የሚያደርጉትን የዳንስ ትርኢት “ዚክር” ነው ይሉታል። አስተግፊሩላህ!!)
- እንደ አል-ሀለጅ እና ኢብን አረቢ የመሳሰሉት “ሱፊ” ነን ባዮች ደግሞ ግልጽ የወጣ ኩፍር ውስጥ የሚያስገቡ ፍልስፍናዎችን በተሰውፍ ስም መጻፍና ማስተማር ጀመሩ።
  ለምሳሌ አለ-ሀለጅ “ማነው ሀቅ?” በሚል ጥያቄ ጀመረና “አነል ሀቅ”፤ ማለትም “አል-ሀቅ እኔ ነኝ” የሚል ፍልስፍና ላይ ደረሰ። እኛ ሙስሊሞች “አል-ሀቅ” የምንለው አላህን ብቻ ነው። ሰውዬው ግን ራሱን “አል-ሀቅ” ብሎ ጠራ። ይህንን እንዲተው ቢመከር እንቢ አለ። በዚህም የተነሳ በጊዜው የነበረው የባግዳድ ኸሊፋ በስቅላት ቀጣው።
- ከአይሁድና ክርስቲያን መነሻሳት ጋር የተቀራረቡ ሙስሊሞች በበኩላቸው በተሰውፍ ስም ምንኩስናን ወደ ኢስላም አስገቡ።
- በኢራን የነበሩት እነ ዑመር አል-ኸያም ተሰውፍን ከልብ ንጽህና አርቀው ከአላህ ጋር በቀጥታ የምንነጋገርበት ጥበብ ነው እያሉ ከሸሪዓው ያነፈገጡ የግጥም ውዳሴዎችን የሚያቀርቡበት መድረክ አደረጉት።
- አንዳንዶቹ ከዚህም ራቅ ብለው ተሰውፍን ከአላህ በስተቀር ማንም ሊደርስበት የማይችለውን ስውር አለም (ገይብ) የሚመረምሩበት መነጽር አደረጉት።
- ተሰውፍ ኢስላማዊ ባህልን መከተል ሲገባው የባእዳን ባህል ተከታይ የሆነበት ሁኔታም ተፈጠረ።
- ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ነገሩ ሁሉ ተቀየረና የጥንቱ ተሰውፍ የአውሊያ መቃብሮች የሚመለኩበት የሽርክ ጋሻና መከታ ሆነ።

ተሰውፍ በስተመጨረሻው ላይ እንደዚህ ውጥንቅጡ የወጣ ዝባዝንኬ ነገር ሆነ። ለዚህ ሁሉ ምክንያት የሆነው "ጠሪቃ" እና "ሀድራ" የሚባሉ ነገሮች መከሰታቸው ነው።

"ጠሪቃ" የተሰውፍ ዚክር ከአንዱ ሼኽ ወደሚቀጥለው ሼኽ የሚተላለፍበት መንገድ ነው። በጠሪቃው ውስጥ የሚታቀፉት ሼኾች እንደ ተማሪና መምህር ሳይሆን እንደ ጌታና ባሪያ ነው የሚተያዩት። ሀድራ ደግሞ አንድ ሼኽ ዚክርን የሚያስተምርበት ማእከል ማለት ነው። በኋላ ላይ ግን ሼኹ ራሱ የሚመለክበት ማእከል ሆኖ ተገኘ። ከዚህ ሌላ የሀድራ ሼኾች ራሳቸውን ወደ ፈውዳላዊ ባላባቶች እየቀየሩ ሀብት ያግበሰብሱ ገቡ። እነዚህን አላማዎች የሚደግፉላቸውን የቅጥፈት ወሬዎች፤ ተረቶች፤ ታሪኮች ወዘተ ማስወራት ጀመሩ። አላህ በቁርአኑ የተናገረው "የአላህ አውሊያ" የሚለው አባባል ትልቅ የማጭበርበሪያ ዘዴ ሆነ።

በዚህ ውጥንቅጡ የወጣ ሁኔታ ውስጥ ነው በርካታ የተቃውሞ ድምጾች በተሰውፍ ላይ የተነሱት። ከነዚህ ድምጾች መካከል በጣም ከፍ ብሎ የተሰማው የሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህ ድምጽ ነው።

ሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያ በተሰውፍ ስም የሚነገድበትን አይን ያወጣ ኩፍር፤ ሽርክ፤ ቢድአና ባእድ አምልኮ በሀይለኛ ሁኔታ ተቃውሟል። ነገር ግን ኢብን ተይሚያህ አሁን እንደሚባለው ተሰውፍን ሙሉ በሙሉ ውድቅ አላደረገውም። ሙስሊሞች በዚክር ከልብ በሽታ የሚፈወሱበትን "ተሰውፍ" በእጅጉ ደግፏል። ኢብን ተይሚያህ እነ ሼይኽ አብዱልቃዲር አል-ጀይላኒ ያስተማሩትን እውነተኛ ተሰውፍ በጣም ያበረታታ ነበር። እርሱ የተቃወመው በተሰውፍ ስም የሚካሄዱትን ከላይ የገለጽኳቸውን አስነዋሪ የሆኑ ኢ-ስላማዊ ድርጊቶችና አመለካከቶችን ነው።

### *አህባሾችና የተሰውፍ አመለካከታቸው*

ከላይ የቀረበውን ትንተና ያነበበ ሰው አህባሾች በተሰውፍ ላይ ያላቸውን አመለካከት በቀላሉ ይረዳል ብዬ አምናለው። ስለዚህ ነገሩን በዚሁ እናሳጥረው። ለመሰናበቻ አንድ ምሳሌ ልስጣችሁ።

በተለምዶ "ገሪባ" ሲባል ሰምታችኋል? ምን ማለት ነው? አህባሾች "ሱፊ" የሚሉት ልቡን ከበሽታ ለማንጻት የሚታገለውን እውነተኛ ሱፊ ሳይሆን ነፍሱን ለሼይኽና ለአውሊያ አምልኮ የሰጠውን እንደ "ገሪባ" አይነት ሰው

ነው፡፡ የአውሊያ መቃብሮችን በየጊዜው እንድንዘይርና እንድንስም ለማድረግ ሲባል አህባሾች እንደ ምክንያት ከሚያቀርቡልን ሰበቦች አንዱ “ተሰውፍ” ነው፡፡ ነኡዙ ቢላህ!! በተሰውፍ ስም ግልጽ ሽርክ??

አላህ ከሽርክ ይጠብቀን!! በተሰውፍ ስም ሽርክን ከሚያበረታቱ አሳሳቾችም ይጠብቀን!!

አሚን!!!

**ክፍል ስምንት፡ "አህባሽ" እና "የአላህ አውሊያ"**

አሁንም አህባሾች የሚያጭበረብሩበትን ቀጥተኛ ርዕስ ነው የመረጥኩት። በዚህ ርእስ ዙሪያ እያወጋን የአህባሾችን ጉድ አብረን እናያለን።

***"የአላህ አውሊያ"***

በቁርአንና በሀዲስ እንደተገለጸው አላህ ቀጥተኛውን መንገድ የሚመራቸው ሰዎች በአራት ቦታ ይመደባሉ።

1. ነቢዮች (ነቢይዩን)
2. እውነተኞች (ሲዲቂን)
3. ሸሂዶች (ሹሀዳ)
4. ደጋግ ሰዎች (ሷሊሂን)

እነዚህ ሙእሚኖች በጥቅሉ ሲጠሩ የአላህ ወዳጆች (አውሊያ) ይሰኛሉ። አላህ ወሊይ የሚባለውን ሰው ማንነት ሲነግረን እንዲህ ይላል።

"ንቁ! የአላህ ወዳጆች በነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም። እነርሱም እነዚያ ያመኑትና እርሱን የሚፈሩት ናቸው።" (ዩኑስ፡ 62-63)

ከነዚህ የቁርአን አያዎች እንደምትረዱት በአላህ ያመነና አላህን የሚፈራ ሰው ሁሉ "ወሊይ" ይባላል። አላህ ሁሉንም ሙእሚኖች ነው "ወዳጆቼ" ብሎ የጠራው። ሰለዚህ ነቢይም ሆነ ሰሀባ፤ ሰለፍም ሆነ በአሁኑ ዘመን ያለ ሙእሚን በሙሉ ወሊይ ነው የሚባለው። ሁሉም በጋራ የሚመሳሰሉት በአላህ ያመኑና አላህን የሚፈሩ በመሆናቸው ነው።

አንዳንድ ጊዜ ግን የወሊይ ትርጉም ሲጠብ ይታያል። ለምሳሌ ብዙ ሰዎች ነቢያትና ሰሀባዎችን እንደ ወሊይ አያዩም። ምክንያቱም ነቢያትንና ሰሀባዎችን "ወሊይ" በሚለው ቃል ከጠራን ደረጃቸውን ዝቅ ማድረግ ይሆንብናል ብለው ስለሚያስቡ ነው።

በእውነትም ነቢያትና ሰሃባዎች ከኛ ጋር በደረጃ አይስተካከሉም። ቢሆንም "ወሊይ ማለት በአላህ ያመነና፤ አላህን የፈራ ሰው ነው" የሚለው ቃል በቁርአን የተነገረ ስለሆነ ሁሉም ሙእሚኖች ወሊይ ናቸው ብንል ክፋት የለውም።

## ወሊይ እና ወሊይነት በዝርዝር ሲታይ

ከላይ የቀረበው ትንተና ጥቅል ነው። አሁን ደግሞ አስፈላጊ ወደሆነው ጉዳያችን እንገባለን!!

አላህ ወዳጆች (አውሊያ) እንዳሉት እናምናለን። ከነርሱ አንዱ እንዲያደርገንም እንለምነዋለን። "ወሊይ" እንድንሆን ደግሞ በኢባዳና በዳእዋ መበርታት ይጠበቅብናል። "ጁህድ" (ጥረት) ሳናደርግ ወሊይ መሆን አይቻልምና።

በኢባዳ፤ በዳእዋ፤ ኼይር በመስራት፤ የሰዎችን ሀቅ በመጠበቅ፤ ለኢስላምና ለሙስሊሞች ጠበቃ በመሆን ከበረታን ወሊይ የማንሆንበት ምክንያት የለም።

ወሊይነት በዘር ሀረግ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ ቅርስ አይደለም። ወሊይነት ለአንድ ቤተሰብ፤ ጎሳ፤ ብሄረሰብ፤ መንደር ወዘተ.. በሞኖፖል የተሰጠ ስጦታ አይደለም። ወሊይነት በአላህ ያመነና አላህን የፈራ ማንኛውም ሰው ሊያገኘው የሚችለው ክብርና ስጦታ ነው።

### አውሊያ እና ከራማ

ስለ ወሊይ ሲወራ በቶሎ ወደ ጭንቅላታችን የሚመጣው ነገር "ከራማ" ነው። ይህም አላህ ለወሊዮች የሚሰጣቸውና በሌሎች ሰዎች ላይ የማይታዩ ለየት ያሉ ባህሪያት፤ የመናገርና ነገሮችን የማድረግ ችሎታዎች፤ ወይም ለሰውየው የተገለጹ ልዩ ክስተቶችን ያጠቃልላል። ለምሳሌ አንድ በአላህ የሚያምንና አላህን የሚፈራ ሙእሚን ቁርአንን እየቀራ ሰዎችን ከበሽታ መፈወስ የሚችል ከሆነ "ከራማ" ተሰጥቶታል እንላለን። እንዲሁም አንድ ሙእሚን የሆነ የአረብ ሰው በጭራሽ ሰምቶት የማያውቀውን የአማርኛ ቋንቋ በድንገት መናገር ቢጀምር "አላህ ከራማ ሰጥቶታል" ማለት ይቻላል። እዚህ ላይ ግን ሁለት ነገሮች መታወቅ አለባቸው

- አላህ ለወሊዮቹ "ከራማ" የሚሰጣቸው ሰዎች የአላህን የማድረግ ችሎታ ተረድተው በአላህ ላይ ሙሉ እምነት እንዲኖራቸውና፤ ኢማን ያልገባቸው ሰዎችም ወደ ኢስላም እንዲመጡ ለማስተማር በሚል ነው።
- አንድ ሰው ወሊይ ለመሆን የግዴታ "ከራማ" ሊኖረው አይገባም። አላህ ከራማ የሚሰጠው ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ነው። አብዛኛው ወሊይ

ከራማ የለውም። የወሊይነት መለኪያው የከራማ ብዛትና ጥንካሬ ሳይሆን የኢማን ጥንካሬና የተቅዋ ብዛት ነው።

አላህ ከራማ የሚመስልና "አል-ኢስቲድራጅ" የሚባል አሳሳች ችሎታ "ወሊይ ነን" በማለት ለሚያጭበረብሩ ሰዎችም ይሰጣል። በዚህም የሰዎችን እውነተኛ ኢማን ይፈትናል። በአላህ በትክክል ያመኑ ሰዎች የሰውዬውን ኢማን ሳያገናዝቡ "ሰውዬው ወሊይ ነው" ለማለት አይደፍሩም። ምክንያቱም "ከራማ" የወሊይነት ሸርጥ (መስፈርት) አይደለምና። የወሊይነት ሸርጥ "ኢማንና ተቅዋ" ብቻ ናቸው። ከራማ ተጨማሪ ስጦታ ነው እንጂ ሸርጥ አይደለም።

እዚህ ላይ ዝነኛው ገጣሚ ፈሪዱዲን አጣር ከጻፈው ***"ተዝኪራቱል አውሊያ"*** ያነበብኩትን አንድ ደስ የሚል ታሪክ ልንገራችሁ።

አንድ ምሽት ሀሰን አል-በስሪ ራሳቸውን ለዋውጠው ወደ ታዋቂዋ የአላህ ባሪያ "ራቢአቱል አደዊያ" ቤት ሄዱ (ሐሰን አል-በስሪ የራቢአ መምህር ናቸው)። ከሌላ ሀገር የመጡ ታላቅ ወሊይ መሆናቸውንም አስታወቁ።

ራቢዓ ሰውዬውን (ሐሰን አል-በስሪን) እንዲህ በማለት ጠየቁ። "አንተ ሰው! ታላቅ ወሊይ ነኝ ብለሀል የወሊይነትህ ማስረጃው ምንድነው?"

- ሐሰን አል-በስሪ፡- "ከራማ አለኝ! በከራማዬ ማንም ሰው ሊያደርጋቸው የማይችላቸውን ድርጊቶች አደርጋለሁ"
- ራቢኣ፡- "እስቲ እንዴት ያሉ ድርጊቶችን ነው የምትፈጽመው"
- ሐሰን፡- "በውሃ ላይ መሄድ እችላለሁ"
- ራቢኣ፡- "ይህንንማ እንቁራሪቶችም ያደርጉታል። ሌላ ችሎታ ካለህ ንገረኝ እስቲ!"
- ሐሰን፡- "እሺ! በሰማይ ላይ መብረር እችላለሁ።"
- ራቢኣ፡- "ይህም ወፎች በየቀኑ የሚያደርጉት ነገር ነው። እስቲ ሌላ ችሎታህን ንገረኝ።"
- ሐሰን፡- "በከራማዬ ጠዋት ቁርሴን በጸሀይ መውጫ በልቼ ምሳዬን በጸሀይ መግቢያ ላይ መብላት እችላለሁ።"
- ራቢኣ፡- "አንተ እንዲያውም ቀርፋፋ ነህ። ኢብሊስ እኮ በአንድ ሰዓት ውስጥ ነው ይህቺን አለም የሚያዳርሳት"።

ነገሩ ያላዋጣቸው ሀሰን አል-በስሪ "ታዲያ እነዚህ አስገራሚ ችሎታዎቹ የወሊይነት ማስረጃ ካልሆኑኝ የወሊይነት ትርጉሙ ምን ሊሆን ነው?" በማለት ጠየቁ።

ራቢአም "የወሊይነት ትርጉም በቁርአን ተነግሮናል። ከዚህ ውጪ ሌላ ትርጉም አትፈልግ" በማለት ትክክለኛውን መልስ ሰጡ። ሀሰን አል-በስሪ በተማሪያቸው የማስተዋል ችሎታ በጣም ተደነቁና ማንነታቸውን አስታወቁ።

ትክክለኛው የሙስሊሞች እምነት ወሊይነትን የሚያስረዳው እንደዚህ ነው። ከዚህ ውጪ ሌላ ትርጉም አያስፈልግም።

## *ወሊዮችና የወሊዮች ሀቅ*

ወሊዮች የአላህ ወዳጆች ናቸው። በኛ ላይ ያላቸው ሀቅ እነርሱን መውደድ ነው። ወሊዮችን ከጠላን የአላህ እውነተኛ ወዳጆችን ጠላን ማለት ነው። ስለዚህ እኛም በአላህ እንጠላለን። ታዲያ ዋነኛው ጥያቄ "ማንን ወሊይ ብለን እንጥራ?" ነው።

ከላይ የቀረበው ትንተና እንዳለ ሆኖ ወሊይ የሚባሉት

- አላህ በቁርአኑ የጠቀሳቸው ጻድቃን ሰዎች (ለምሳሌ ሉቅማን፤ ዙል-ቀርነይን ወዘተ..)
- የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰሀቦች
- ለዚህ ኡማ ታላላቅ ተግባራትን የፈጸሙ ቀደምት ሙስሊሞች (ለምሳሌ አራቱ ኢማሞች፤ እነ ቡኻሪና ሙስሊምን የመሳሰሉ የሀዲስ ምሁራን፤ እንደ አል-ጠበሪ፤ አል-ቁርጡቢና ኢብን ከሢር ያሉ የተፍሲር ኡለማ ወዘተ..)
- መላው የሙስሊም ህዝብ ስለ-ቅድስናቸውና ኢማናቸው የመሰከረላቸው መሪዎችና አሊሞች (ለምሳሌ ሸሊፋ ዑመር ኢብን አብዱል አዚዝ፤ሸሊፋ ሀሩን አል-ረሺድ፤ ሀሰን አል-በስሪ፤ ራቢአቱል አደዊያ፤ ሼይኽ አብዱልቃዲር አል-ጂይላኒ ወዘተ...)
- በሀብታቸውና በእውቀታቸው ኢስላምን ያገለገሉ ደጋግ ሰዎች (ለምሳሌ በርካታ መስጊዶችና መድረሳዎችን ያስገነቡ በጎ አድራጊዎች፤ በሺህ የሚቆጠሩ ደረሳዎችን አስተምረው ያስመረቁ አሊሞች ወዘተ..)

ታዲያ ወሊይ የሚባለውን ሰው ስንመዝን አላህ በቁርአን ያስቀመጣቸውን ቀዳሚ መመዘኛዎች መርሳት የለብንም። እነርሱም ኢማንና ተቅዋ ናቸው።

ወሊዮች በቂያማ እለት ከአላህ ምልጃ ሊጠይቁልን ይችላሉ። ይህ ግን አሁን የሚፈጽሙት ሳይሆን በየውመል ቂያማ የሚያደርጉት ነገር ነው። የነቢያችንን (ሰ.ዐ.ወ)፤ የሲዲቆችን፤ የሸሂዶችንና የወሊዮችን ሸፈዓ (ምልጃ) ለማግኘት የሚፈልግ ሰው በአላህ ማመን፤ እርሱን መፍራትና ኢባዳውን በተገቢው መንገድ ማከናወን ይጠበቅበታል። ኢባዳ የማያደርገውን ሰው ወሊይ ይቅርና ነቢዩ እንኳ ከአላህ ቅጣት ሊያስጥሉት አይችሉም።

## *አህባሾችና የወሊዮች ሀቅ*

አህባሾች እኛን ከሚወቅሱባቸው ነገሮች አንዱ "ወሊዮችን ትጠላላችሁ" የሚል ነው። ይህ ግን ተራ ቅጥፈት ነው። እኛ ሙስሊሞች የአላህ ባሮችን በፍጹም አንጠላም። እንወዳቸዋለን። እናከብራቸዋለን። ከአህባሾች ጋር የማንግባባው

- እነርሱ "ተወሱል" በሚል ካባ ወሊዮችን በአላህ ላይ እንድናሻርክ ስለሚጋፋፉን (ማለትም አላህ ለወሊዮች የሰጣቸው ሸፈዓ ሀጃችንን አሁኑኑ ይሞላልናል የሚል እምነት አላቸው። ስለዚህ ሰዎች ጉዳያቸውን በቀጥታ ለአላህ ከመንገር ይልቅ አላህ ለሚወዳቸው ወሊዮች ቢናገሩ ወሊዮች በአላህ ፊት በአማላጅነት ይቆሙላቸዋል" ይላሉ። እኛ ግን እንዲህ አንልም። ወሊዮች ለምልጃ የሚቆሙልን በየውመል ቂያማ እለት ነው። በዚህ አለም ምልጃ የሚቆሙበት አንዳች ስልጣን አልተሰጣቸውም)።
- አህባሾች "ተበሩክ" የሚለውን ነገር ትርጉሙን እያዛነፉ ወደ መቃብር አምልኮ ይገፋፉናል።
  እርግጥ የሙስሊሞችን መቃብር መዘየር ይፈቀዳል። "ተበሩክ" ነው እያሉ መቃብሮችን መሳም፤ በመቃብር ላይ እርድ መፈጸም፤ መውሊድ ማካሄድ፤ መቃብሮችን ሸቶ መቀባት፤ እጣን ማጨስ ወዘተ.. የመሳሰሉ ድርጊቶች በጃሂሊያ ዘመን ሲፈጸሙ የነበሩ የሽርክ ተግባራት ናቸው እንጅ ተበሩክ አይደሉም።
- በመቃብሮች ላይ ደሪህ (Shrine) መገንባት በየትኛውም መዝሀብ አይፈቀድም። አህባሾች ግን በአውሊያ መቃብሮች ላይ ግንብ መገንባትንና ቀለም መቀባትን እንደ ቅዱስ ነገር አድርገው ያስተምራሉ።

- ወሊይነት ዘር፤ ጎሳ፤ ቀለም ፤ ቤተሰብ አይመርጥም፡፡ አላህ የሚፈልገው ሰው ወሊይ ይሆናል፡፡ አህባሾች ግን ወሊይነት በዘር ሀረግ ከአባት ወደ ልጅ የሚተላለፍ አይነት ነገር አድርገው ነው የሚያስተምሩት፡፡
- ኡለማ የአንቢያ ወራሾች ናቸው፡፡ እንወዳቸዋለን፡፡ እናከብራቸዋለን፡፡ ለአላህ ስንልም ሄደን እንዘይራቸዋለን፡፡ አህባሾች ግን ይህንን ያጣምሙታል፡፡ በነርሱ ዘንድ ዚያራው የሚደረገው ለአላህ ሲባል ሳይሆን የሸይኹን በረካ ለማግኘትና በከራማው ለመፈወስ ሲባል ነው፡፡
- አህባሾች አውሊያ ብለው የሚዘይሩት ሼይኽ የሰዎችን “ሲር” (ድብቅ ነገር) ያውቃል ባዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ “ከኛ የተደበቀውን ነገር ማየት ይችላል” ይላሉ፡፡ ለዚህም በትንሹም ሆነ በትልቁ ጉዳይ ምክርና በረካ ለማግኘት በሚል ሰበብ ወደ ሼኽ ዘንድ ይበራሉ፡፡ ታዲያ ይህ ጥንቆላ ነው ወይስ ሽሪዓ?

በአጭሩ አህባሾች የሚባዝኑለት ነገር ሁሉ ወደ ሽርክ የሚገፋፋ ነው፡፡ ባለፈው ክፍል ስለተሰውፍ ስጽፍ እንደገለፅኩት አህባሾች በተሰውፍ ስም የሚነዙት ነገር በጠቅላላ ወደ ሽርክ የሚነዳ ነው፡፡ ስለ አውሊያ (የአላህ ባሮች) ሲናገሩም መጀመሪያቸውና መጨረሻቸው ሽርክ ነው፡፡ ታዲያ በሽርክ ላይ መደራደር ይቻላል? በፍጹም!!

የአላህ ወዳጆችን እንወዳለን፡፡ እናከብራቸዋለን፡፡ በነርሱ ስም የሚሰበክልንን ሽርክ ግን በፍፁም አንቀበልም፡፡ ነኡዙቢላህ ሚነል ሺርክ!!

አላህ ከሽርክ ይጠብቀን!! አሚን!!

## ክፍል ዘጠኝ፡ አህባሽ እና "ሺዓ"

በዚህ ክፍል የአህባሽን ነገር ከሺዓ ጋር እያነጻጸርኩ እንድናየው ፈለግኩ። ከዚያ በፊት አንድ ነገር ልናገር።

አንዳንድ ሰዎች ይህንን ርዕስ ሲያዩ "ሁለቱም ጠማሞች ናቸው፤ ለምን ስለነርሱ መጻፍ አስፈለገ" ማለታቸው አይቀርም። የኔም አላማ ከሁለቱ አንዱን ለወዳጅነት እንድንመርጥ መገፋፋት አይደለም። ይህንን ጽሁፍ ለመጻፍ የተነሳሳሁት አንዳንድ የፌስቡክ ጓደኞቼ አህባሽን ከሺዓ ጋር ሲያመሳስሉ በማየቴ አባላላቸው ስህተት መሆኑን ለማስረዳት ነው። ለዚህም የሁለቱን መመሳሰልና ልዩነታቸውን አብረን እናያለን።

### *የአህባሽና የሺዓ መመሳሰል*

አህባሽ የሚባለው አንጃ እና የሺዓ ሙስሊሞች በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ተመሳሳይ (ተቀራራቢ) አቋም አላቸው።

1. ሰሞኑን እንዳየነው አህባሾች ስለ "ተወሱል" እና "ተበሩክ" በሀይለኛ ሁኔታ ይከራከራሉ። ሺዓዎችም በዚህ ላይ ተቀራራቢ አቋም አላቸው። ነገር ግን ሺዓዎች ለተወሱልና ለተበሩክ የሚመርጡት "አውሊያ" ከአህሉል በይት (የፋጢማ ዛህራ እና የአሊ ኢብን አቡጣሊብ የዘር ሀረግ የተገኘ) መሆን አለበት ይላሉ።
2. አህባሾች "በአውሊያ መቃብር ላይ ደሪህ መገንባትና መቃብሮችን ዚያራ ማድረግ የአውሊያዎችን በረካ የሚያስገኙ ተግባራት ናቸው" ይላሉ። ሺዓዎችም የኢማሞችን መቃብሮች ማሳመር፤ ደሪህ መገንባት፤ ዚያራ ማድረግ ወዘተ... በጣም አስፈላጊ ተግባራት እንደሆኑ ያምናሉ።
3. አህባሾች "ከኸሊፋ አሊ ኢብን አቡጣሊብ ጋር የተዋጉ ሰሃባዎችን መሳደብና መራገም ሀጢአት የለውም" ባዮች ናቸው። ሺኣዎችም በዚህ ላይ ተመሳሳይ አቋም አላቸው።
4. በረመዳን ወር ህዝበ ሙስሊሙ ለተራዊህ ሰላት ወደ መስጊድ ሲሄድ በሀገራችን ውስጥ ያሉት አህባሾ ደግሞ "ኢልም እንማራለን" እያሉ ወደ መርከዝ ነው የሚሄዱት። "ተራዊህ ለምን አትሰግዱም?" ብሎ ለጠየቃቸው ሰው "ተራዊህ ሱንና ነው። ኢልም መማር ግን ፈርድ ነው" የሚል መልስ ይሰጣሉ። ሺዓዎች ደግሞ መስጊድ ሄደው ተራዊህን

በጀመዓ አይሰግዱም። “ምክንያቱ ምንድነው?” ተብለው ሲጠየቁ “ይህ ዑመር የጀመረው ቢድአ ነው” ይላሉ።

5. አህባሾች የሚከተሉት የሱፊ ጠሪቃ “ሪፋዒያ” ይባላል። ይህ ጠሪቃ ሲልሲላውን (የሼይኾች የቅብብሎሽ መንገድ) ከነቢዩ ጋር የሚያገናኘው የሺዓ አማኞች አስራ ሁለቱ ኢማሞቻችን ናቸው የሚሏቸውን ሰዎች በመቁጠር ነው።
6. አህባሾች ለመውሊድ ከልክ ያለፈ ፍቅር አላቸው። ለህጋዊነቱም ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከራሉ። የነቢዩንና (ሰ.ዐ.ወ) የፋጢማ ዛህራን (ረ.ዐ) መውሊድ ጨምሮ ሌሎች በርካታ መውሊዶችን ያከብራሉ። ሺዓዎችም መውሊድን በጣም ይወዳሉ። (እንዲያውም መውሊድ ራሱ የተጀመረው በአህሉ ሱንና ሰዎች ሳይሆን ግብጽን ከ10ኛው-11ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ባስተዳደሩት የፋጢሚይ ገዥዎች ነው። ፋጢሚዮች ደግሞ ሺዓዎች እንጂ ሱኒዮች አልነበሩም)።
7. አህባሾች ሼይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህንና ሼይኽ ሙሀመድ ኢብን አብዱልወሃብን በጣም ይጠላሉ። ሺዓዎችም በነዚህ ምሁራን ላይ ተመሳሳይ አቋም ነው ያላቸው።

የአህባሽና የሺዓ መመሳሰል ከብዙ በጥቂቱ ይህንን ይመስላል። ይሁንና አህባሾች እነኝህን አቋሞች የወረሱት ከሺዓዎቹ አይመስለኝም። ከዚህ በፊት እንደገለጽኩት “አህባሽ” የሚባለው ፓርቲ ራሱ የተቋቋመው የአንጃው መስራች የሆኑት ሼኽ አብዱላህ አል-ሀረሪ በተበሩክ፤ ተወሱል፤ የመቃብር ዚያራ ወዘተ.. ላይ ለነበራቸው የተዛነፈ አቋም ሽሪአዊ መልክ ለማስገኘት በመፈለጋቸው ነው።

ሰሀባዎችን መስደብና ተራዊህን ዝቅ አድርጎ ማየት ደግሞ ከሺዓዎች የተወረሰ ሳይሆን “አለዊ” የሚባሉትን የሶሪያ ገዥዎች ለማስደሰት የተወሰዱ አቋሞች ይመስሉኛል። (ኡለማ ሙሉ በሙሉ ካፊር ነው በማለት የፈረጁት ይህንን አለዊ የሚባለውን “ፊርቃ” ነው። ሺዓዎችም ሆኑ ሱኒዮች “አለዊ ካፊር እንጂ ሙስሊም ቡድን አይደለም” በሚለው ላይ ተስማምተዋል።)

## የአህባሽና የሺዓ ልዩነት

አህባሾችና ሺዓዎች በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ከፍተኛ ልዩነት አላቸው።

1. አህባሾች የሚጠሉት እነ ኢብን ተይሚያህን ብቻ አይደለም። እነርሱ የሚወዷቸውን የአውሊያ መቃብሮች ያልነኩባቸውን እንደ ጀማሉዲን አል-አፍጋኒ፤ ረሺድ ሪዳ፤ አቡል አእላ መውዱዲ፤ ሰይድ ቁጥብ፤ ወዘተ የመሳሰሉ ምሁራንና ሙስሊም ታጋዮችንም በጣም ይጠላሉ። ሺዓዎች ግን ለነኝህ የተሀድሶ አራማጆችና የሙስሊም ህብረት አስተማሪዎች ከፍተኛ አድናቆት አላቸው። ለምሳሌ የቀድሞው የኢራን መሪ አያቱላህ ሩሑላህ ኾሜይኒ የአቡል አእላ መውዱዲን መጽሀፍት ከመውደዳቸው የተነሳ አንዳንዶቹን ወደ ፋርሲ (ኢራን) ቋንቋ ተርጉመዋል።
2. አህባሾች በዚህ ዘመን የሸሪአ ህግን የሚተገብር መንግስት መመስረት አይቻልም ባይ ናቸው። "የኸሊፋዎች አይነት አስተዳደርም ሆነ ኢስላማዊ ሪፐብሊክ መመስረት አይቻልም። ስለዚህ ሀይማኖቱን ብቻ ይዘን ከፖለቲካው መገለል አለብን" ባይ ናቸው። በአህባሽ አመለካከት መሰረት ጂሀድ እናካሂዳለን የሚሉት የሙስሊም ነጻነት ንቅናቄዎችም ጊዜ አልፎባቸዋል።
   ሺዓዎች ግን ከዚህ ተቃራኒ የሆነ አመለካከት ነው ያላቸው። "የሸሪዓ ህግ ከየትኛውም ዘመን ጋር የሚሄድ ወደር የለሽ ህግ ነው፤ በርሱ የሚመራ ኢስላማዊ መንግስት መመስረትም ይቻላል" ባይ ናቸው። "ጂሀድም ቢሆን ጥቃት ባለበት ጊዜ ሁሉ መካሄድ አለበት" ይላሉ።
3. አህባሾች በጣም ጽንፈኛ ናቸው። ከነርሱ ጋር የማይራመድ፤ የነርሱን ሀሳብ የማይቀበል፤ እነርሱ ሸሪአዊ መልክ ሰጥተው የሚያደርጉትን ድርጊት የሚቃወም ሁሉ "ካፊር" ነው።
   ሺዓ ግን እንዲህ አይልም። ማንም ሰው "ላ ኢላሀ ኢለላህ ሙሐመዱን ረሱሉላህ" ብሎ ካመነ ሙስሊም ነው። ከነርሱ የሚለዩትን ሙስሊሞች "መንገዱን ለቀዋል፤ ተሳስተዋል" ነው የሚሉት እንጂ "ካፊር" ያሉበት ወቅት የለም።
4. አህባሾች ከሙስሊሞች ይልቅ ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖችን ይጎዳኛሉ። የነርሱ ጓደኞች ምዕራባዊያን፤ ጽዮናዊያን፤ የሶሪያው አለዊ (ኑስራኒ) ሀይማኖት ተከታዮች ወዘተ.. ናቸው። ሺዓዎች ግን እንዲህ አይነት

አመል የለባቸውም። ሚስጢራቸውን እርስ በራሳቸው እንጂ ከአላህ ጠላቶች ጋር አያወሩም።

5. አህባሾች ዋነኛ ጠላታችን "ወሃቢያ" ነው ይላሉ። በነርሱ አመለካከት "እስልምናን እያጠፋ ያለውና ወደፊትም የሚያጠፋው "ወሀቢያ ነው"። በመሆኑም ወሃቢ የሚሉትን ሰው ለአላህ ጠላቶች አሳልፎ ከመስጠት ወደኋላ አይሉም።
   ሺዓዎች ግን "ዋነኛው የኢስላም ጠላት ጽዮናዊያንና ተባባሪዎቻቸው ናቸው" ይላሉ።

ከላይ ከቀረበው ንፅፅር እንደምንረዳው መጥፎ የሚባለው ነገር ሁሉ መጥፎነቱ እኩል አይደለም። ከመጥፎው ሁሉ የተሻለ መጥፎ አለ። ከመጥፎዎች ሁሉ የሚበልጥ የመጥፎ መጥፎ አለ።

"አህሉሱንና ወል-ጀመዓ" ነኝ የሚለው አህባሽ ከኛ ጋር በብዙ መልኩ የሚለያየውን የሺዓ አንጃ ያህል እንኳ ለኢስላም አይቆረቆርም። ሺዓዎች የኢስላም ጠላቶች "ጽዮናዊያን ናቸው" ነው የሚሉት። አህባሽ "የኢስላም ጠላቶች ወሀቢዎች ናቸው ይላል"። አስተግፊሩላህ!!

የአህባሽ ጠላቶች እኛ ሙስሊሞች ነን። አላህ ብቻ አይጣላን እንጂ አህባሽና ግብረ አበሮቹ እንደፈቀዳቸው ይበሉን። እኛ በአላህ ስለምናምን እንደ አህባሽ የኢስላምን ክብር ለአላህ ጠላቶች አናስረክብም።

ድል የኢስላም ነው። አላሁ አክበር!!!!

## ክፍል አስር፡ በ"አህባሽ" ኑፋቄና ጥመት ዙሪያ የአለም ሙስሊሞች ምን ይላሉ?

አህባሽ የተባለው አንጃ በቤይሩት ከተማ ሲመሰረት የእድር አይነት መልክ ነበረው። ከጥቂት አመታት በኋላ ግን ጠንከር ያለ ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ቡድን ሆኖ ብቅ አለ። ለዚህ የረዳው ቡድኑ በረጅሙ የሊባኖስ የርስ በርስ ጦርነት ወቅት ንቁ ተሳትፎ ያልነበረው መሆኑና ይልቁንም የሊባኖስ ህዝብ እንደ ነጻ አውጪ በሚመለከተው የሶሪያ የጦር ሀይል መታገዙ ነው። የሚገርመው ነገር ቡድኑ በሶሪያም እየተደገፈ ከእስራኤልና ከምእራባዊንም ጋር አስገራሚ ቁማሮችን የሚጫወት መሆኑ።

የአህባሽ መርዘኛነት እዚህ ላይ ነው! "ሶሪያን እኛ የምናውቃት የምእራባዊያን ጠላት ናት" በሚል ነው። ይህንን የሚያስብ ሰው "አህባሽ ከጽዮናዊያን ጋር የጠነከረ ወዳጅነት ይመስርታል" ብሎ አይጠረጥረም። ግን አድርጎታል!! ትንሽ ጥቅም የሚያገኝ ከሆነ ከማንም ጋር አደገኛ ቁማሮችን ይጫወታል። ቡድኑ ነጋ ጠባ የሚወርፈውን "ወሀቢያ" የሚባል ቡድን "አብረን እንታገለው" የሚለውን ሰው ካገኘማ ደስታውን አይችለውም። አንድ የሚያሳዝነኝ ነገር ቢኖር "አህባሽ" የሚቀርባቸው ቡድኖችና መንግስታት ሁሉ "ጸረ-ኢስላም" መሆናቸው ነው። የሶሪያዎቹ የ"አለዊ" እምነት ተከታዮች፤ የአይሁድ ጽዮናዊያን፤ የአሜሪካ ኢምፔሪያሊዝም፤ የቱርክ ወታደራዊ መኮንኖች ወዘተ... ሁሉም ጸረ-ሙስሊም ናቸው።

አህባሽ "የሙስሊሙን ዓለም እንዴት ጸጥ እናድርገው?" እያሉ ሲጨነቁ ለነበሩት ምዕራባዊያን ተመችቷል። በተለይ ከሴምቴምበር 11/2001 ወዲህ ተፈላጊነቱ በጣም ጨምሯል። ለዓለም ሙስሊሞችስ ምን አስገኝቷል?

በዚህ በኩል አንጃው ምንም የቀናው ነገር የለም። የታሪክ መዝገቡ በአሳፋሪ ፋይሎች የታጨቀ ነው። ከፊሊፒንስ እስከ ካናዳ፤ ከፊንላንድ እስከ ደቡብ አፍሪካ ያሉት ሙስሊሞች በሙሉ "አህባሽ" የጥመት እና የኑፋቄ ቡድን መሆኑን በይፋ አውጀዋል። በርካታ ምሁራን፤ እስላማዊ ተቋማትና ቡድኖች አህባሽን ያወገዙባቸውን ልዩልዩ ፈትዋዎች ሰጥተዋል። ከነዚህ መካከልም አንዳንዶቹ እንደሚከለተው ቀርበዋል።

1. አለም አቀፍ የፈትዋ አስተዳደርና የምርምር ተቋም (በማሌዥያ የሚገኝ) በአህባሽ ጥመትና ኑፋቄ ላይ የተላለፉ በርካታ ፈትዋዎችን መዝግቧል። ከነርሱ መካከል አንዱን በሚከተለው የኢንተርኔት አድራሻ ማየት ትችላላችሁ።
   http://www.e-infad.my/FMS_en/index.php?option=com_fatwa&task=viewlink&link_id=2489&Itemid=59
2. አህባሾች "የሱፊያ" እና "የሱፊዎች" ጠበቃ እንደሆኑ ይናገራሉ። ትክክለኛው "ተሰዉፍ" (Sufism) ከነርሱ ዘንድ እንዳለም ያወራሉ። የሱፊ ቡድኖች ግን አህባሽ ጠማማ አንጃ መሆኑን በይፋ ሲያሳውቁ ነበር፡ ለምሳሌ ያህልም የአለም ትልቁ የሱፊዎች ማእከል መሆኑ የሚነገርለት የነቅሽባንዲያ ቡድን በአህባሽ ጥመትና ኑፋቄ ላይ ያሳለፋቸውን ልዩ ልዩ ፈትዋዎች ከሚከተለው ዌብ ሳይት ላይ ማንበብ ይቻላል።
   http://naqshbandi.org/topics/refute/aicp/default.htm
3. የሰሜን አሜሪካ የሱኒ (አህሉ ሱንና ወልጀመዓ) ሙስሊሞች ማህበር የአህባሽን ጥመት አስመልክቶ ያስተላለፈው ፈትዋ ከማህበሩ ድረ-ገጽ ይገኛል።አድራሻውም www.sunnah.org ነው።
4. ይህንኑ የአሜሪካ ሙስሊሞች ማህበር ከሚመሩት ምሁራን አንዱ የሆኑት ዶ/ር ጂብሪል ፉአድ ሀዳድ ለልዩልዩ ጥያቄዎች መልስ በሚሰጡበት ዌብ ሳይት ላይ አንድ ሰው "ወደ አህባሾች መርከዝ ሄጄ ትምህርታቸውን መከታተል ይፈቀድልኛል?" ብሎ ሲጠይቃቸው "ከነዚህ የውሸት ሱኒዮች (Pseudo-Sunni) አንድም አይነት ትምህርት መቀበል አይፈቀድም" በማለት መልሰዋል። ሙሉውን ጥቄና መልስ ከሚከተለው አድራሻ ማየት ትችላላችሁ።
   http://qa.sunnipath.com/issue_view.asp?HD=7&ID=12879&CATE=1

5. እኚሁ እስላማዊ ምሁር በአህባሽ ላይ የሰጧቸውን ልዩ ልዩ ፈትዋዎች ለማንበብ የሚከተለውን የዌብሳይት አድራሻ ይክፈቱ።

http://groups.google.com/group/soc.religion.islam/browse_thread/thread/726707766da1d1ce/f10a69559ba994dc?lnk=gst&q=Al-Ahbash#

6. አህባሾች የፊቂህ መዝሀባቸው "ሻፊዒይ" እንደሆነ ደጋግመው ያወራሉ። አቂዳን የሚያስተምሩት በኢማም አቡል ሀሰን አል-አሸዐሪ መንገድ እንደሆነም ይጽፋሉ። በአለም ዙሪያ ያሉትና የሻፊዒን መዝሀብና የአሸዓሪን የአቂዳ ትምህርት የሚቀበሉ ሙስሊሞች ግን አህባሽ የጥመትና የኑፋቄ ቡድን እንደሆነ በአንድ ድምጽ ይናገራሉ። በሺዎች የሚቆጠሩ ሙስሊሞች ስለ አህባሽ ያደረጉትን የኢንተርኔት ውይይት ከሚከተሉት ሁለት ዌብሳይቶች ማየት ትችላላችሁ።
   a.) http://www.sunniforum.com/forum/showthread.php?2953-ANSWERED-Who-are-the-habashis-%28al-ahbash%29
   b.) http://www.marifah.net/forums/topic/2774-sheikh-abdullah-al-harari-and-the-ahbash/
7. አህባሾች ከሺዓ ቡድኖች ጋር እንዳማይስማሙ ከዚህ ቀደም ተናግሬ ነበር። ማስረጃ ከፈለጋችሁ አህባሽ በዓለም ዙሪያ ከታወቀውና "ሂዝቡላህ" ከተሰኘው የሺአ ቡድን ጋር ባለፈው አመት በቤይሩት ጎዳና ላይ ያደረጉትን ውጊያ ከሚከተለው ድረ-ገጽ ተመልከቱ።
   http://www.dailystar.com.lb/News/Politics/Aug/25/3-killed-in-clashes-between--Hizbullah-Ahbash-elements.ashx#axzz1XS1rEWeY

የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን እንዲመራ የተመረጠው ቡድን የኋላ ታሪኩ ይህንን ይመስላል። እኛም የምንፋለመው የአለም ሙስሊሞች በጥመትና በኑፋቄ ካወገዙት ከእንደዚህ አይነቱ ቡድን ጋር ነው። ቡድኑ ለዲናችን ጠንቀኛ መሆኑ በአንድ ቃል የተመሰከረ ሀቀኛ ነገር ስለሆነ በዚህ ላይ ጥርጣሬ አይግባችሁ። የጀመርነውን ፍትሃዊ ትግል በሰላማዊና ህጋዊ መንገዶች ሁሉ እንቀጥልበታለን።

ድል የኢስላም ነው! አላሁ አክበር!

**ክፍል አስራ አንድ፡ "አህባሽ"፤ "ወሃቢያ" እና "የብሪታኒያው ሰላይ"**

እነዚህ አህባሾች ቀላል ህዝቦች እንዳመስሏችሁ!! አባላቶቻቸው ሀቁን እንዳይመለከቱ በበርካታ መጋረጃዎች ይጋርዷቸዋል። እነርሱ የሚጠሉትን ሰውና ግለሰብ ሌላው ሰው እንዳይቀበለው ለማስጠነቀቅ በርካታ "ተረቶችን" ያስወሩባቸዋል። ለዛሬው አህባሾች "ወሀቢያ" በሚሉት ቡድን ላይ ከሚያስወሯቸው ተረቶች አንዱን እናያለን።

***የ"ቱርኮች" ያልተረሳ ቂም***

ወደዋናው ታሪክ ከመግባታችን በፊት እስቲ ስለ ታሪክ ትንሽ እናውራ።

አብዛኛውን የአረቢያ ልሳነ-ምድር የምትሸፍነው የዛሬዋ ሳኡዲ አረቢያ ከ18ኛው እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ድረስ የሀይለኛ ጦርነቶች አውድማ ነበረች። በጦርነቱ በዋናነት የሚዋጉት ሂጃዝ የተባለውን ክፍለ-ሀገር የሚያስተዳድሩት ከነቢዩ የዘር ሐረግ እንደተወለዱ የሚናገሩት የ"ሸሪፍ አሊ" ቤተሰቦችና ነጆድ የተሰኘውን በረሀማ ክልል የሚገዙት የአል-ሱዑድ ቤተሰቦች ነበሩ። ታዲያ በሚገርም ሁኔታ የነጆድ ገዥዎች ከማንም ተጽእኖ ነጻ ነበሩ። የሂጃዝ ገዥዎች ግን ተጠሪነታቸው የዘመኑ ሀያል ገዥ ለነበረው የቱርክ ሱልጣን ነው። የነጆድ ገዥዎች እያሸነፉ መካና መዲናን በያዙ ቁጥር ግዙፉ የቱርክ ጦር እየበረረ ይመጣና ያስወጣቸዋል። ከዚያም ሀገሩን ለሸሪፎች ያስረክባል።

ጦርነቱ እንዲህ እያለ እስከ ሀያኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ድረስ ዘለቀ። በመጨረሻም ቱርክ በአንደኛው የአለም ጦርነት ስትገባ የሀይል ክፍተት ተፈጠረ። ከነጆድ የተነሳው የሳኡዲ ጦር ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የሂጃዙን የሸሪፍ ቤተሰብ ድል በማድረግ ከሀገሩ አባረረ። በኋላም ከኸሊፋዎች ዘመን ወዲህ በአንድ መንግስት ስር ተሰባስቦ የማያውቀውን የአረቢያ በረሃ አንድ ላይ በማጠቃለል *"አል-መምለከቱል ዐረቢያቱስ ሳዑዲያ"* (Kingdome of Saudi Arabia) የተባለ ሀገር መሰረተ። ከሂጃዝ የተባረረው የሸሪፍ አሊ ቤተሰብ ደግሞ ወደ ዮርዳኖስ በማቅናት ዛሬ "መምለከቱል ሀሺሚያቱል ኡርዱኒያ" (Hashimite Kingdom of Jordan) የሚባለውን ሀገር ፈጠረ።

ሳኡዲዎች በዚያ ዘመን የተደረገውን ጦርነት የጀግንነታቸው መገለጫ አድርገው ይቆጥሩታል። "ሳኡዲ አረቢያ ዛሬ ለደረሰችበት እድገት መሰረት የሆናት ንጉስ መ·ሀመድ ኢብን ሱኡድ በሸሪፎቹ እና በቱርኮቹ ላይ ያሳየው

አልገዛም ባይነት ነው" ይላሉ- ሳኡዲዎች። የዮርዳኖስ ንጉሳዊያን ቤተሰቦችና ቱርኮች ግን የያኔውን ጦርነት እንደ ክፉ ጠባሳ ይቆጥሩታል። እንዲያውም "ጦርነቱን የፈጠሩትና በጦርነቱ የተሳተፉት ሁሉ የነቢዩን ቤተሰቦች የሚጠሉና እስልምናን ለማጥፋት የተነሱ የይሁዲ ወኪሎች ናቸው" ይላሉ። ይህንን ነገር በሰፊው የሚተርኩት ግን ቱርኮች ናቸው።

"ቱርኮቹ ለምን እንዲህ ያመርራሉ?" ካልን በቂ መልስ የለንም። እነርሱ ምክንያቱን ሲያስረዱ ግን *"ያንን የመሰለ ግዛታችንን የበጠበጠውና በመላው ሙስሊም ዓለም የነበረንን ተቀባይነት ያረከሰው ከነጅድ የተነሳው የወሃቢ ሀይል ነው"* ይላሉ። ለመሆኑ ወሃቢ ያኔም ነበረ?

## *የሰላዩ ማስታወሻ*

ከዚህ በፊት በጻፍኩት አንድ ጽሁፍ አህባሾች *"ወሀቢያ የተፈጠረው በሙሐመድ ኢብን ሱኡድ እና በሙሀመድ አብዱል ወሃብ አማካኝነት ነው፤ ሁለቱን ሰዎች መልምሎ በማሰልጠን ለግዳጅ ያሰማራው አንድ እውቅ እንግሊዛዊ ሰላይ ነው"* ይላሉ" በማለት ገልጬ ነበር። በእውነትም ይህ ታሪክ ለአንድ የአህባሽ ምልምል አባል የሚነገረው ገና ወደ ቡድኑ እንደተጠጋ ነው። ስለ"ወሃቢያ" መጥፎነት ለማስረዳት የመጀመሪያ ማስረጃ ሆኖ የሚቀርበውም ይህ ታሪክ ነው።

ይህንን ታሪክ የሚተርክ መዝገብም ሆነ መጽሀፍ ለረጅም ጊዜ ሳፈላልግ ሊቀናኝ አልቻለም ነበር። አሁን ተሳክቶልኝ አግኝቼዋለሁ። እናንተም ሙሉ መጽሀፉን ከሚከተለው ድረ ገጽ ማግኘት ትችላላችሁ።

http://www.hakikatkitabevi.com/download/english/14-ConfessionsOfABritishSpy.pdf

**የመጽሀፍ ርዕስ** "Memoirs of Mr. Hempher, The British Spy To The Middle East" ይሰኛል፡ ይህ መጽሀፍ ሚስተር ሄምፈር በሚባል እንግሊዛዊ ሰላይ ነው የተጻፈው ይባላል። ሰውየው መጽሀፉን የጻፈው ድሮ በሰራው ስራ ጸጸት ስለገባው ነውም ተብሏል። ሚስተር ሄምፈር (የአባቱ ስም አልተገለጸም) እንደሚለው *"የእንግሊዝ መንግስት ሙስሊሞች ጠንካሮች ናቸው። እነርሱን ለማጥፋት ከውስጣቸው ገብተን መበታተን አለብን።"* ከሚል አቋም በመነሳት ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሀገራት ለስለላ ላከኝ፤ በአንድ ጉዞዬ መሀመድ አብዱል ወሀብ ከሚባል ወጣት ተማሪ ጋር በበስራ ከተማ ተዋወቅኩ። ከዚያም

*በእስልምና ውስጥ አክራሪ የሆነ አዲስ አንጃ እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ሰፊ ስልጠና እየሰጠሁ ለግዳጅ አሰማራሁት"* ይላል።

እንግዲህ *መ*ሀመድ አብዱል ወሃብና *መ*ሀመድ ኢብን ሱኡድ *መ*ስሊሙን ከውስጥ ሆነው እንዲያጠቁ የተላኩ የእንግሊዝ ምንደኞች ናቸው ማለት ነው። ዛሬ ከሳኡዲ አረቢያ ወደ ልዩ ልዩ ሀገራት ኤክስፖርት የሚደረገው የ"ወሀቢያ" ትምህርትም በእንግሊዝ የተፈበረከ መርዝ መሆኑ ነው። ለመሆኑ የተባለው ነገር እውነት ነው?

## *የመጽሀፉ እርግጠኝነት*

አህባሾች ስለዚያ *መ*ጽሀፍ ከነገሩኝ በኋላ በነገሩ ላይ ስንወያይ "ይህ የምታወሩት ወሀቢያ የሚባለው ነገር ስለመኖሩ ራሱ እጠራጠራለሁ" አልካቸው። እነርሱም ወዲያኑ በ"ወሀቢያ" ታሪክ ዙሪያ የተጻፈ ሌላ *መ*ጽሀፍ ሰጡኝ።

የዚያኛው *መ*ጽሀፍ ርእስ "*Wahhabism: A Critical Essay*" ይሰኛል። የመጽሀፉ ደራሲ ፕሮፌሰር ሀሚድ አልጋር የሚባሉ ታዋቂ የ"ሺዓ" ምሁር ናቸው። ታዲያ ደራሲው በመጽሀፋቸው የ"ወሀቢያ ሀቅ" ነው ያሉትን ታሪክ በሰፊው ይተርኩና በአንደኛው ገጽ የግርጌ ማስታወሻ ከላይ የጠቀስኩትን የሚስተር ሀምፈር ታሪክ ያነሱታል። በመደምደሚያቸውም *"ያ መጽሀፍ ፊርጅድ ሳይሆን አይቀርም"* ይላሉ።

አህባሾች የሚያወሩት ነገር ከግማሽ በላይ ሀሰት ነው። ስለ ሚስተር ሀምፈር የተነገረኝን ነገር የሰማሁትም እየጎረበጠኝ ነው። በኋላ የሺዓው ምሁር ("የወሀቢ ጠላት ነኝ" ነው የሚሉት) በጨረፍታ የተናገሩት ነገር ትልቅ ማስጠንቀቂያ ሆነኝ። እስከቅርብ ጊዜ ድረስ *መ*ጽሀፉን ባላነበውም ወሬው በሀሰት የተፈጠረ መሆኑ ገብቶኛል። ለመሆኑ ወሬውን ማን ፈጠረው?

ዊኪፒዲያ እንደሚለው ይህንን የፈጠራ *መ*ጽሀፍ ጽፎ ያሰራጨው *አዶብ ሰብሪ ፓሻ* የሚባል የኦቶማን ቱርክ የባህር ሀይል ባልደረባ ነው። በንጉስ *መ*ሐመድ ኢብን ሱኡድ እና በሼይኽ *መ*ሀመድ አብዱል ወሃብ የተቀጣጠለው የለውጥ አብዮት ቱርኮችን በአረቢያ ከነበራቸው ግዛት ላይ ሲያባርራቸው በምቀኝነት ይህንን የፈጠራ ወሬ አሰራጩ።

በሌላ በኩል በርካታ ሙስሊም ምሁራን ይህ ተጻፈ የሚባለው መጽሀፍ "እውነት መሆኑን እናጣራ" በማለት በታላላቅ የአውሮፓ ቤተ መጽሀፍት አሰሳ አድርገው ነበር። በተለይ ቀደምትና ጥንታዊ መጽሀፍት የሚቀመጡባቸውን ክፍሎች ፈትሸዋል። ሆኖም ሚስተር ሀምፈር በሚባል ስም የተመዘገበ ተመሳሳይ ርእስ ያለው መጽሀፍ አላገኙም። ስለዚህ "የፈጠራ ተረት ነው" ከሚል መደምደሚያ ላይ ደርሰዋል።

## *ሀጸጹ (fallacies)*

መጽሀፉ በፈጠራ የተጻፈ መሆኑን በውስጡ ካሉት በርካታ ህጸፆች (fallacies) መረዳት ይቻላል።

ለምሳሌ

- መጽሀፉ ሙሀመድ ኢብን አብዱል ወሃብ "ይሁዲ ናቸው" ይላል። ነገር ግን ሼኽ ሙሐመድ አብዱል ወሃብ "ተሚም ከተባለ ጎሳ የተወለዱ አረብ ናቸው።
- መጽሀፉ ሼይኽ ሙሀመድ ኢብን አብዱል ወሃብ "አረብኛ፤ ፋርሲ እና የቱርክ ቋንቋ ይናገራሉ" ይላል። ሆኖም ሼይኽ ሙሀመድ ኢብን አብዱል ወሃብ ከአረብኛ ውጪ ሌላ ቋንቋ በፍጹም አይናገሩም።
- መጽሀፉ እንደሚለው ሚስተር ሀምፈር ከወጣቱ ሙሀመድ አብዱል ወሃብ ጋር በበስራ ከተማ የተገናኘው በ1912 ነው። ነገር ግን በዚህ ዓመት ሙሀመድ ኢብን አብዱል ወሃብ እዚያው በተወለደበት አካባቢ የሚኖር የዘጠኝ ዓመት ህጻን ነበር። ስለዚህ ከቤተሰቦቹ ተነጥሎ ወደ በስራ ሄደ የሚለው ተረት አይሰራም።
- ሌላው ቀርቶ በመጽሀፉ ላይ የተጠቀሰው "በእንግሊዝ ግዛት ላይ ጸሀይ አትጠልቅም " የሚለው አባባል እጅግ በጣም ዘግይቶ በ20ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ የመጣ ነው እንጂ በዚያ ዘመን እንዲህ አይነት አባባል አልነበረም። በወቅቱ እንግሊዝ በእስያና በአፍሪካ ምድር አንድም ኮሊኒ (ቅኝ ግዛት) አልነበራትም።

አህባሾች እንግዲህ ይህንን በተረት የታጨቀውን ተራ ወሬ ነው እንደ ግዙፍ ነገር አድርገው የሚያስተጋቡት። በነርሱ ቤት የማይነቃባቸውና እውነታው የማይገለጽ መስሏቸዋል። ፈጠራ፤ ተረት፤ ሀሰት ወዘተ...

የመናፊቆችን ቀልብ ሊማርክ ይችላል። የመእሚኖችን ልብ በፈጠራና በተረት መክፈት አይቻልም።

በመጨረሻ! ይህ አይነ-ደረቅ የሆነ የኑፋቄ ቡድን አባላቶቹን ይዞ መቀጠል እጅግ ይከብደዋል። ምክንያቱም እርሱ ውሸትን እንደሚፈልገው እየቀጣጠፈ ሲሄድ አባላቱ እየነቁበት "ወራጅ አለ!" ይሉታል። ከዛሬ በኋላም በርሱ ዙሪያ የተሰበሰቡ ወንድሞችና እህቶቻችን "ውሸቱን" እየነቁ "ወራጅ አለ" እንዲሉት እንጠይቃቸዋለን።

ድል የኢስላም ነው። አላሁ አክበር!!

**ክፍል አስራ ሁለት፡ "አህባሽ፣ ቱርክና የ"ወሀቢያ ተረት"**

በዚህኛው ክፍልም አህባሾች የሚያምታቱባቸውን የፈጠራ ተረቶችና ከነርሱ ጀርባ ያሉትን ድብቅ አላማዎች እንዳስሳለን። ይህንን በትክክል ለማስረዳት እንዲያግዘኝ አህባሾች ከቱርኮች ጋር የፈጠሩትን የህብረት ግንባር እንደምሳሌ እወስዳለሁ። ወደዚያ ከማለፋችን በፊት በዚህ ጸሁፍ ውስጥ ያለው "ቱርክ" የሚለው ቃል በዚህ ዘመን ከአህባሾች ጋር የሚሞዳሞዱትን ቱርካዊያን ብቻ የሚያመለክት እንደሆነ ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

***የቱርክ ሱልጣኔትን ማን ነው ያፈረሰው?***

ዛሬም ወደ ታሪክ ምእራፎች ሄደን አንዳንድ እውነቶችን ማውራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። ስለዚህ የጥንቱ የኦቶማን ቱርክ ሱልጣናዊ መንግስት ከአረቦች ምድር የወጣበትን ሁኔታ የሚያስረዳ እውነተኛ ታሪክ በመጠኑ ልንገራችሁ።

ቱርኮች እስከ አንደኛው የዓለም ጦርነት ድረስ አብዛኛውን የሰሜን አፍሪካና የመካከለኛው ምስራቅ መሬቶችን ይገዙ ነበር። በነዚህ አካባቢዎች ከነበሩት ግዛቶች መካከል ቱርኮች ያልያዙት ነጅድ (መካከለኛውና ምስራቃዊው የሳኡዲ አረቢያ ክፍል)፤ ነፉድ (የሳኡዲ አረቢያ ማእከላዊ ክፍል)፤ ሀድረመውት (ደቡብ ምስራቅ የመን)፤ የተወሰኑ የኦማን ክፍሎች፤ ሞሮኮና የተወሰኑ የመግሪብ ክፍሎች፤ እንዲሁም የሰሜን አፍሪካው የሰሀራ በረሀ ብቻ ነበሩ። ባለፈው ክፍል እንደገለጽኩት ከነጅድ በተነሱት የአል-ሱኡድ ጎሳዎች የሚመራው የአረብ ጦር ቱርኮች የወከሏቸውን የአካባቢ ገዥዎች ቀስ በቀስ እያባረረ ዛሬ ሳኡዲ አረቢያ የምትባለውን ሀገር መስርቷል።

ቱርኮች በታክቲክ ስህተት የገቡበት የአንደኛው የአለም ጦር ለከፍተኛ አዙሪት ሲዳርጋቸው ለጦርነቱ ማስኬጃ የሚሆነውን ገንዘብ ለመሰብሰብ በሚገዟቸው ህዝቦች ላይ ተደራራቢ ታክስና ልዩልዩ ክፍያዎችን መጣል ጀመሩ። በዚህን ጊዜም ከነርሱ ስር የነበሩት የመካከለኛው ምስራቅና የሰሜን አፍሪካ ህዝቦች ወደ አመጽ ገቡ። ቱርኮቹ አመጹን በሀይል ለመጨፍለቅ ተንቀሳቀሱ። አማጺያኑ ግን ለግዙፉ የኦቶማን ጦር ሳይበገሩ በአመጹ ገፉበት። እነዚህ አማጺ ህዝቦች በአብዛኛው አረቦች ናቸው።

አረቦች ውጊያቸውን ያካሄዱት በራሳቸው ሀይል ነው። ከጀርባቸው የማንም ረዳት ሳይኖራቸው ነበር የተንቀሳቀሱት። ሆኖም በአንዳንድ አጋጣሚዎች አስገራሚ ኩነቶች ታይተዋል። ለምሳሌ አረቦቹ የሞት ሽረት ውጊያ

በሚዋጉበት በዚያ ቀውጢ ወቅት አንድ አዛዥ አግኝተዋል።

ይህ ሰው ድሮ ለአርኪዮሎጂ ምርምር በአረብ በረሃ ውስጥ ይንከራተት ነበር። ምርምሩን ጨርሶ በሰላም እየኖረ በነበረት ወቅት የእንግሊዝ የመረጃ ክፍል "አንተ ሀገሩን በደንብ ስለምታውቅ መረጃ በማሰባሰብ ትረዳናለህ" በማለት ወደ መካከለኛው ምስራቅ አመጣው። ሰውየው ወደስፍራው ሲመጣ ግን የመረጃ ማቀበሉን ስራ ተወና ከአረቦቹ ጋር ተቀላቅሎ እንደ ተራ ወታደር ሆኖ ይዋጋ ጀመር። የውጊያ ችሎታውን ያዩት አረቦች የክፍለ ጦር መሪ አደረጉት። ሰውዬው የአረቦቹን ሀይል እየመራ ቱርኮቹን ድል በማድረግ በርካታ ግዛቶችን ተቆጣጠረ። በመጨረሻም ኢራቅ፤ ሶሪያ፤ ዮርዳኖስ ፤ፈለስጢን እና ሊባኖስ ከቱርክ አገዛዝ ስር ነጻ ወጡ። ሆኖም አረቦቹ የተመኙትን ነጻነት እንዲህ በቀላሉ አላገኙም። ቱርኮች ሲባረሩ በቦታቸው እንግሊዝና ፈረንሳይ ተተክተው "የባለአደራ መንግስት" በሚል ፈሊጥ ሀገራቱን እስከ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማገባደጃ ድረስ ገዝተዋል (እንግሊዝ ፈለስጢንን ከዓለም ካርታ ላይ ያጠፋችው በዚያን ጊዜ ነው)።

ቱርኮች ከአረቢያ እንደ ተባረሩት ሁሉ በሀገር ቤትም ሰላም አላገኙም። በሙስጠፋ ከማል አታቱርክ የሚመራ የወጣት መኮንኖች ቡድን የመጨረሻውን የቱርክ ሱልጣን በማንበርከክ አዲሲቷን የቱርክ ሪፐብሊክ መስርቷል። ታዲያ ይህኛው የወጣት መኮንኖች ቡድን *"ቱርክ በአለም ፊት ለገጠማት ታላቅ ውርደት ያበቃት የእስልምና ሀይማኖት አስጠባቂ ነኝ ማለቷ ነው"* የሚል አስነዋሪ አስተሳሰብ በማራመድ ኢስላም ከቱርክ ምድር የሚጠፋበትን ስልታዊ ዘዴ በስራ ላይ በማዋልና ዛሬ በቱርኮች ምድር የሚታየውን ዝብርቅርቅ ሁኔታ ፈጥሯል።

የቱርክ ሱልጣናዊ መንግስት የፈረሰው በዚህ ሁኔታ ነው። ይህንን ታሪክ ከመቋጨቴ በፊት ከአረቦች ጋር ሆኖ ቱርኮችን ከተዋጋው እንግሊዛዊ ጋር በትንሹ ላስተዋውቃችሁ።

የአረቦችን ጦር የመራው እንግሊዛዊ በእውነተኛው ስሙ ቶማስ ኤድዋርድ ለውሬንስ (T.E. Lawrence) ይባላል። የአለም ህዝብ የሚያውቀው ግን "የአረቢያው ለውሬንስ" (Lawrence of Arabia) በሚለው ቅጽል ስሙ ነው። እንግሊዞች ከብሄራዊ ጀግኖቻቸው እንደ አንዱ ይቆጥሩታል። በአንደኛው የአለም ጦርነት ባደረገው ንቁ ተሳትፎ በበርካታ ሀገራት (በአረቦችም ጭምር) ተሸልሟል።

ለውሬንስ ከአረቢያ ምድር ወደ ሀገሩ ተመልሶ የጻፈውና *The Seven Pillars of Wisdom* የሚል ርዕስ ያለው መጽሀፉ ከፍተኛ ተቀባይነትን ከማግኘቱም በላይ በ1962 ዓ.ል. ወደ ሲኒማ ተቀይሮ ተሰርቷል። ሲኒማው በጊዜው ሰባት የኦስካር ሽልማቶችን በመቆጣጠር በበርካታ ሀገራት በሰፊው ተችብችቧል። ስለ "አረቢያው ለውሬንስ" የበለጠ ለማንበብ የሚከተለውን የዊኪፒዲያ ገጽ ተመልከቱ።
http://en.wikipedia.org/w/index.php?title=Lawrence_of_Arabia&redirect=no

ይህንን ታሪክ ማውራቱ ለምን አስፈለገ? የሰሞኑ መነጋገሪያችን ከሆነው የአህባሽ ጉዳይ ጋር ይያያዛል?

በእርግጥ ከአህባሽ ጉዳይ ጋር በቀጥታ የሚያገናኘው ነገር የለም። ሆኖም አህባሾች "ወሀቢ" በሚለው ቡድን ላይ የሚያስወሩት የፈጠራ ታሪክ "መሰረት የለሽ" መሆኑን ለማሳወቅ ስለምፈልግ ነው ወደ ታሪክ የሄድኩት። አሁን ወደ ዋናው ነገር ልምጣ።

ዛሬ አህባሾች እንደ "ትልቅ ሚስጢራዊ ግኝት" አድርገው የሚያስወሩት "የእንግሊዛዊው ሰላይ ታሪክ" የተፈጠረው በቱርኮች እንጂ በአህባሾች አይደለም። የኦቶማን ቱርኮች በአረቦች መሸነፋቸው ስለቆጫቸው ***"አረቦች ከእንግሊዝና ከፈረንሳይ ጋር ወግነው ወጉን"*** እያሉ ያወራሉ። ለዚህ እንደዋነኛ ምክንያት አድርገው የሚያቀርቡት "ወሀቢ" የሚባለውን ሀይል ነው።

ሆኖም የኦቶማን ቱርክ ሱልጣናዊ መንግስት የፈረሰው በራሱ ውስጣዊ ችግርና በአመጸኛ ህዝቦች አልገዛም ባይነት እንጂ በወሀቢዎች ተንኮል አይደለም። እነርሱ "ወሀቢ" የሚሉት የሙሀመድ ኢብን ሱኡድ ጦር እና የሼይኽ ሙሀመድ አብዱልወሃብ ደረሳዎች ቡድን ከዛሬዋ ሳኡዲ አረቢያ ምድር ውጪ እግሩን አላነሳም። የአል-ሳኡድ ጦር አንድ የሚታማበት ነገር ቢኖር "ጂዛን" የተባለውን ክፍለ ሀገር ከየመን መቀማቱ ብቻ ነው። ይህንን አንደብቅም።

ለማጠቃለል ያህል

1. ከዚህ ቀደም የገለጽኩት የሚስተር ሀምፈር ታሪክ "የበሬ ወለደ" አይነት ፈጠራ ነው እንጂ አንድም እውነት የለበትም። ታሪኩን በቅድሚያ የጻፉት ቱርኮች ናቸው። ሆኖም ቱርኮች የሚያወሩት "ሰላይ" በአረቢያ ምድር ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም። ከአረቦች

ጋር ወግኖ ቱርኮችን የተዋጋ እንግሊዛዊ ቢኖር ከላይ የገለጽኩት ***"የአረቢያው ለውሬንስ"*** ብቻ ነው። ቱርኮች ስለርሱ አንድም ቀን ተናግረው አያውቁም። ምክንያቱም ለውሬንስ በአለም ታሪክ ውስጥ ስመገናና ከሆኑ ሰዎች መካከል አንዱ በመሆኑ በርሱ ላይ ውሸት ማስወራት አመቺ አይደለምና።

2. የቱርክ ሱልጣኔትን ያፈራረሰው የህዝቦች አመጽ ነው። በኢስታንቡል ከተማ የሱልጣኔቱን መፍረስ በይፋ ያበሰሩት ግን አረቦች ሳይሆኑ በሙስጠፋ ከማል የተመሩት የቱርክ ወጣት መኮንኖች ናቸው። ሙስጠፋ ከማል ***"እስልምና ቱርክን ለሰድሰት መቶ አመታት ወደኋላ አስቀርታታል"*** በማለት በግልጽ የተናገረ ሰው ነው። "ከዛሬ ወዲህ የሸሪአ ህግ አይሰራም። መስጅድ መገንባት ክልክል ነው። መድረሳዎችም ይዘጉ" ወዘተ፣.. የመሳሰሉ አዋጆችንም ያወጀው ቱርካዊው ሙስጠፋ ከማል ነው።

ዛሬ ቱርኮች የሚያወሩት ግን ሌላ ነው። "ሱልጣናዊ መንግስታችን ያፈራረሰው ወሀቢ ነው" ነው የሚሉት። አህባሽም የቱርኮችን ፕሮፓጋንዳ በመከተል *"ወሀቢ እስላማዊውን የቱርክ ሱልጣኔት ያፈረሰ ጸረ-ኢስላም ቡድን ነው"* ይለናል። ደግነቱ ግን የአለም ታሪክ የሚጻፈው አህባሾች እንደፈለጉት አይደለም። ታሪክ ማለት በአህባሽ ጀመኣና በመርከዝ ሰበካ ላይ የሚወራው ተረት ሳይሆን ምሁራን ሰፊ ጊዜ ሰጥተው በምርምር የሚጽፉት ውድ ቅርስ ነው።

***የቱርካዊያኑ "ጸረ-ወሃቢ" ዘመቻ***

በሀገራችን ውስጥ ለእርዳታና የልማት ስራ ለመስራት በሚል ሽፋን በርካታ የቱርክ ዜጎች ተበትነዋል። አንዳንዶቹም ለንግድ ጉዳይ በማለት ነው የሚመጡት። ከነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ከአህባሽ ቱጃሮች ጋር ሸሪክ በመሆን የንግድና የአገልግሎት መስጫ ድርጅቶችን ከፍተዋል።

ታዲያ እነዚህ ቱርኮች በአንድ ነገር ላይ ተጠምደዋል። ከእናት ሀገራቸው የሚመጡት አንድ ቁና ሙሉ መጽሀፍ በመያዝ ነው። እነዚህን መጽሀፍት በደረሱበት ቦታ ሁሉ ያለ ክፍያ ያሰራጫሉ።

ከመጽሀፍቱ መካከል አንዳንዶቹ በጣም ጥሩ ናቸው። ለምሳሌ ኡስታዝ ኡስማን ኑሪ ቶፕባሽ የሚባሉት ቱርካዊ የጻፏቸው መጽሀፍት እጅግ ምርጥ የሚባሉ ናቸው። የኝህ ቱርካዊ መጽሀፍት በተሰውፍና በአኽላቅ ላይ ነው

የሚያተኩሩት። ጥሩ ቱርካዊ ናቸው ማለት ነው። አላህ ምንዳቸውን ይክፈላቸው።

አብዛኞቹ መጽሀፍት ግን በጣም የተበከሉ ናቸው። ሁሉም የሚያስተምሩት "የወሀቢያን" መጥፎነትና በታኝነት ነው። ሁሉም በአንድ ድምጽ "ወሀቢያን እናጥፋ" ነው የሚሉት።

እነዚህን መጽሀፍት ለመጀመሪያ ጊዜ ሳያቸው የአህባሽ ጀመዓ ራሱ ጽፎ የሚያሰራጫቸው የፕሮፓጋንዳ ድርሰቶች መስለውኝ ነበር። መጽሀፍቱ በአህባሽ እጅ እንዳልተጻፉ ያመንኩት ሌሎች ገጽታዎቻቸውን ካየሁ በኋላ ነው። ለምሳሌ መጽሀፎቹ ስለፊቅሂ ጉዳይ ብዙም አያወሩም። እንደ አህባሽ መጽሀፍት የሺዓ ኢማሞችን እንደ ማስረጃ አይጠቅሱም ። ለሰሀባ ተገቢውን ክብር ይሰጣሉ። በተለይ አንደኛው መጽሀፍ ስለ ሞአዊያ (ረ.ዐ) ልብ የሚነካ አስደሳች ታሪክ ሲተርክ ማንበቤን አስታውሳለው።

ሆኖም መጽሀፍቱ "ለወሀቢ" ምህረት የላቸውም። "ወሀቢያ" ያሉትን ሰው ባለ በሌለ ሀይላቸው ይዘልፋሉ። እርግማናቸውም ሌላ ነው። ኢብን ተይሚያህ፤ ኢብን አብዱል ወሃብ፤ ሰይድ ቁጥብ፤ አቡል አእላ መውዱዲ፤ ጀማሉዲን አል-አፍጋኒ ወዘተ... አንድ የሚቀራቸው ምሁር የለም። እጅግ የሚገርመው ነገር ደግሞ ከላይ የጻፍኩትን የፈጠራ ታሪክ ያለ አንዳች ሀፍረት ይዘከዝካሉ። "ወሀቢ በአረብ የዘረኝነት ስሜት በመነሳሳት ኢስላማዊውን የቱርክ ሱልጣኔት አፈራረሰው" ይላሉ።

### *"ቱርካዊው" እስልምና*

ቱርኮቹ በዚህ ጨዋታ ውስጥ ለምን ገቡ? ይህንን በትክክል መመለስ የሚችሉት እነርሱ ብቻ ናቸው (ከነርሱ በላይ የሚያውቀው ደግሞ አላህ ነው)። ለኔ የሚመስለኝ ግን የሚከተለው ነው።

ቱርካዊያኑ ለሀይማኖታችን ተጨንቀው አይደለም ይህንን የሚያደርጉት። ነገር ግን "ኢስላማዊው የለውጥ ፈላጊ ክፍል ሀገራቱን ይወርስና ቱርክ ኢስላማዊት ሀገር ናት ብሎ ያውጃል" የሚል ፍርሃት አላቸው። ስለዚህ *"የሸሪዓ ሀግ ክቡር ነው፤ ሂጃብ ለሴት ልጅ ክብሯ ነው"* የሚል አመለካከት ያለውን ማንኛውንም ግለሰብና ቡድን በጥርጣሬ አይን ያዩታል። በነርሱ አስተሳሰብ ከዚህ ጀርባ ያለው ሀይል በሙሉ "ወሀቢ" ነው።

በቱርካዊያኑ አመለካከት “ወሀቢ” ቱርክን ተቆጣጠረ ማለት ሀገሪቷ የምትኮራበት አውሮፓዊ ማንነቷን አጣች ማለት ነው። ስለዚህ የወሀቢ አመለካከትን ከስረ-መሰረቱ ማጥፋት ያስፈልጋል። የወሀቢ ሽታ የተጠናወተውን ሰውና ቡድንም እየተከታተሉ መቅጣት አስፈላጊ ነው”።

ቱርካዊያኑን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ወሀቢን የሚዘልፉት በዚህ ምክንያት ነው። ይህንን አላማቸውን ለማሳካት እንደ አህባሽ የመሳሰሉትንና “እስልምና በፖለቲካ ውስጥ መግባት የለበትም” የሚሉትን “ዘመናዊ ሙስሊሞች” ይፈልጋሉ። ለነዚህ ቡድኖች የሚያስፈልጉትን ገንዘብና የማቴሪያል እርዳታ በገፍ ያቀርቡላቸዋል።

ታዲያ ቱርካዊያኑ የሚፈልጉት እስልምና ምን አይነት እንደሆነ አውቃችኋል? ይህንን ለመረዳት በቀላሉ በቱርክ የባህል ተቋም ዌብሳይት ላይ የተጻፉትን ትንታኔዎች መመልከት ነው። የዌብሳይቱ አድራሻም የሚከተለው ነው http://www.turkishculture.org

ለምሳሌ ኢስላማዊውን አቂዳ በማስተማር ጉልህ ሚና የተጫወተውን የኢማም አቡ መንሱር ማቱሪዲ የህይወት ታሪክ የቱርክ የባህል ተቋም እንዴት አድርጎ እንደጻፈው ታነቡ ዘንድ የሚከተለውን መግቢያ (link) ክፈቱ። http://www.turkishculture.org/philosophers/ebu-mansur-maturidi-22.htm

በአጭሩ ቱርኮቹ “ወሀቢያ በእስልምና ስም የአረብ ባህልን የሚያስፋፋ የባህል አብዮት ነው” ይላሉ። “ስለዚህ ከእስልምና ውስጥ አለባበስ፤ አመጋገብ፤ አስተዳደር፤ ማህበራዊ ግንኙነት ወዘተ.. የመሳሰሉትን ጉዳዮች የሚመለከተውን አረባዊ የሆነውን ክፍል እናስወግድና ኢማንና ሰላትን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩረውን ኢስላማዊ የሆነውን ክፍል እንወስዳለን። ከዚያ በኋላም ቱርካዊ ይዘት እንዲኖረው እናደርጋለን” ባይ ናቸው።

ይህ ምን ማለት? ሂጃብ መልበስ የአረብ ባህል ነው? መልሱን ለናንተ እተወዋለሁ።

አህባሽ በአንድ ጊዜ ከበርካታ ሀይሎች ጋር ቁማር መጫወት ይችላል። ምእራባዊያኑና ጽዮናዊያኑ "ወሀቢያ" የሚባለውን አክራሪ ሀይል እንመታበታለን" ይላሉ። የሶሪያዎቹ አለዊዎች በበኩላቸው ብዙሀኑ ሙስሊሞች የመብት ጥያቄዎቻቸውን እንዳያነሱ ለማድረግ አህባሽን በመሳሰሉ ታማኝ ሀይሎች ይጠቀማሉ። የቱርኮቹ "ዘመናዊያን" ደግሞ "የአረብ የባህል ወረራን እንመክትበታለን" ይላሉ። አዑዙቢላሂ!

ዛሬ እኛን እንዲመራ የተመረጠው ቡድን እንዲህ አይነት የቁማር ጨዋታዎችን ሲጫወት ነው የከረመው። ወደኛ የተላከውም እነዚህን ጸረ-ኢስላም ሐይሎች የሚያስደስት ሆኖ ስለተገኘ ነው። አላማው ደግሞ እስልምናን ማውደም ነው። ነገር ግን አላህ (ሱ.ወ.) ኢስላምን ይጠብቀዋል። እነርሱ ያሰቡትን ተንኮል ወደነርሱ ይመልሳል።

ድል የኢስላም ነው። አላሁ አክበር!!!!

## ክፍል አስራ ሶስት፡ *አራቱ አህባሾች*

አህባሾች ስንት ዓይነት እንደሆኑ አውቃችኋል? የሰበካ ስልቶቻቸውንስ? ወደነርሱ ጀመዓ ለማስገባት የሚያድኗቸውን ሰዎችስ? በብዛት የተበተኑባቸውን ስፍራዎችስ?

በዚህ ክፍልና በሚቀጥለው ክፍል በነዚህ ርዕሶች ላይ እናተኩራለን። ታዲያ በሁለቱ ክፍሎች የተጠቀሱት በሀገራችን ውስጥ ተሰራጭተው የምናገኛቸው የአህባሽ ሰዎች ብቻ መሆናቸውን ለማሳወቅ እፈልጋለሁ።

### *አህባሾች በየፈረጃቸው ሲታዩ*

በዚህ ወቅት በሀገራችን ውስጥ የተበተኑትን አህባሾች በአራት ቡድኖች ከፍሎ ማየት ይቻላል።

*ሀ/. **ዓለም አቀፍ አህባሾች*** ፦ እነዚህኛዎቹ አህባሾች በሀገራችን ውስጥ በብዛት የሉም። ሆኖም በመርከዞቻቸው በአስተማሪነት የሚመደቡት እነርሱ ናቸው። ከነርሱ ውስጥም የሚበዙት የሊባኖስ አረቦች ናቸው ። ከተማሪዎቻቸውና ከሌላው ህዝብ ጋር የሚነጋገሩትም በአረብኛ ነው (በሌላ ቋንቋ ሲነጋገሩ አይቼ አላውቅም)። ከዋናው ሼኽ አጠገብ ደግሞ ሁለት ያህል ረዳት ኡስታዞች ይመደባሉ። እነዚህኛዎቹ ኡስታዞች ኢትዮጵያዊያንም ሊሆኑ ይችላሉ)።

እነዚህ ሊባኖሳዊ አህባሾች ለ"ወሀቢያ" ያላቸው ጥላቻ የትየለሌ ነው። በምሳ ሰዐትም ሆነ በትምህርት ክፍለ ጊዜ የሚያወሩት ስለ "ወሃቢያ" ነው። ኢብን ተይሚያህን ሳያወግዙ ቀኑ አይመሽላቸውም። ታዲያ ሊባኖሳዊያኑ ውሸትን ተክነውበታል። ደኢፍ የሆነውን ሀዲስ ሰሒህ፤ ሰሒህ የሆነውን ሀዲስ ደኢፍ አድርጎ ማውራት ለነርሱ ቀላል ነው። ነገር ግን እነርሱን ሆን ብሎ የተከታተላቸው ሰው ቀጣፊነታቸውን በጥቂት ቀናት ውስጥ ለማወቅ ይችላል።

*ለ/. **የሀገር ውስጥ ጽንፈኛ አህባሾች***፦ ከኢትዮጵያዊያን አህባሾች መካከል አንዳንዶቹ የለየለት ጽንፈኝነት ይታይባቸዋል። እነዚህ ወገኖች ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በላይ የአህባሽን መስራች ነው የሚያደንቁት። ለትንሽ ለትልቁም "ሼኽ እንዲህ ብለዋል" ማለት ይቀናቸዋል። ከነርሱ ጋር ያልተሰለፈውን ሁሉ "ካፊር ነው" ብሎ የመጥራት አባዜ ተጠናውቷቸዋል። ይህንንም የምትረዱት ከነርሱ ጋር ክርክር ስትጀምሩ ነው። ለምሳሌ በኢብን ተይሚያህ ዙሪያ ክርክር ጀምራችሁ "እርሱ እኮ ትክክለኛ ሙስሊም ነው" ካላችሁ በቀጥታ ነው የሚያከፍሯችሁ።

እነዚህ ጽንፈኛ አህባሾች ከሌላው የማህበረሰብ ክፍል ጋር ብዙም አይቀላቀሉም። ከስራ ሰዓት ውጪ ያለውን ጊዜ የሚያሳልፉት በመርከዝ፤ በቤት ወይም እንደነርሱ የአህባሽ ተከታይ በሆነ ግለሰብ ቤት ነው። በሌላ በኩል ጽንፈኞቹ አህባሾች ከሌሎች ሰዎች ጋር በጀመዓ አይሰግዱም (ሰውየው አህባሽ ካልሆነ በስተቀር)። የጁምዓ ሰላትን በየትኛውም መስጊድ አይሰግዱም። ምክንያታቸውን ስትጠይቁ "ኢማሙ የአቂዳ ችግር አለበት" ይላሉ። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ የራሳቸውን ጁምኣ እየመሰረቱ እንደሆነም ሰምተናል።

ከጽንፈኞቹ አህባሾች መካከል አንዳንዶቹ ኮፍያና ጀለቢያ ማድረግን ይወዳሉ። ሴቶቹ ግን ሙሉ አባያ ይለብሱና ከስር የጂንስ ሱሪ ያደርጋሉ። ሴቶቹ በቡድን ተሰብስበው ወደ መርከዝ ሲሄዱ ያያቸው ሰው ይህንን በደንብ ይረዳል። ሆኖም ጽንፈኞቹ ታይት ሱሪ አያደርጉም። አንዳንድ ሰዎች "አህባሽ" ስለሆኑ ብቻ "ሴቶቻቸው ታይት እየለበሱ መርከዝ ይገባሉ" እያሉ በሀሰት ይወነጅሏቸዋል። ይህ ግን ትክክል አይደለም።ታይት ወይም ጅንስ እየለበሱ ጸጉራቸውን ብቻ የሚሸፍኑት ለዘብተኞቹ ናቸው (ከወደ ታች እንመጣበታለን)።

ታዲያ እንደ ሊባኖሳዊያኑ ሁሉ ጽንፈኞቹ አህባሾችም ወሬያቸው "ወሀቢ... ወሀቢ...ወሀቢ..." የሚል ቅኝት ያለው በመሆኑ ከአንድ ቀን በላይ አብራችሁ መቆየት አትችሉም። በቶሎ የምትናደዱ ከሆነ ከነርሱ ጋር ባትቀራረቡ ይሻላል።

እነዚህን ጽንፈኞች ወደ ትክክለኛው መንገድ መመለስ ቀርቶ በትእግስት ማዳመጡ ራሱ በእጅጉ ይከብዳል። ስለዚህ ዳኢዎች በነርሱ ላይ ጊዜ ባያጠፉ ይመረጣል። ሆኖም እነርሱን መለየቱ በጣም ቀላል እንደሆነ መታወቅ አለበት። ለምሳሌ ከላይ ያነሳሁትን "ወደ ጀመዓ እና ጁምአ አይመጡም" የሚለውን አባባል የተከተለ ሰው ጽንፈኞቹን በቀላሉ ለመለየት ይችላል።

ሐ/. ***የሀገር ውስጥ ለዘብተኛ አህባሾች***፦ ከአህባሾቹ መካከል ከማንኛውም ሰው ጋር የሚቀራረቡ ለዘብተኞችም አሉ። እነዚህ ወገኖች ሰላተል ጀመኣንም ሆነ ጁምአን ከኛ ጋር ሊሰግዱ ይችላሉ። ከስራ ሰኣት ውጪም ከኛ ጋር ሊቀላቀሉ ይችላሉ። እነዚህኛዎቹም ቢሆኑ ግን የአህባሽ መለያዎቻቸውን አይተውትም። "ወሀቢ" ማለቱን፤ ኢብን ተይሚያህን መዝለፉን፤"ገውሠል አዘም መጀመን" ማለቱን ወዘተ.. አይተውትም። በነርሱ ላይ የሚታየው ጥሩ ነገር እንደ ጽንፈኞቹ "ከፊርክ" የሚል ቃል የማይወጣቸው መሆኑ ነው። በተጨማሪም "ወሀቢ"ን በየደቂቃው እየደጋገሙ ጭንቅላታችሁን አያሳመምትም። ከእንዲህ

አይነቱ አህባሽ ጋር በዲን ጉዳይ ጨዋታ ጀምራችሁ አካሄዱ ሳይጥማችሁ ቢቀርና "ወሬ ቀይር" ብትሉት እንደ ጽንፈኞቹ አያኮርፍም።

በሌላ በኩል ለዘብተኛ የአህባሽ ሴቶች በጣም ዘናጮች ናቸው። ከወጣቶቹ መካከል ከፊሉ አባያ ይለብሳሉ። ብዙዎቹ ግን ጅንስ ሱሪ ነው የሚለብሱት። የተወሰኑት ደግሞ ወደ ታይት ሱሪ ያደላሉ። በእድሜ የገፉት "ዲሪአ" ወይም "አባያ" ይብሳሉ።

ታዲያ አንድ ሀቅ መረሳት የለበትም። እነዚህን ለዘብተኛ አህባሾች ወደ አህባሽ ጀመኣ ያስጠጋቸው የእውቀት ማነስ ነው። ከፊሎቹ ደግሞ በጓደኞችና በዘመዶቻቸው ግፊት ነው ወደ አህባሽ የሚሄዱት። ትእግስት ያለው ሰው ጊዜ ወስዶ ዳእዋ ካደረገላቸው ወደ ትክክለኛው መንገድ ሊመለሱ ይችላሉ።

መ/ ***"እኩራፊ አህባሾች"***፦ እነዚህኛዎቹ አህባሾች በትልልቅ ከተሞች አካባቢ የሉም። ብዙዎቹ በአነስተኛ ከተሞችና በአንዳንድ የገጠር ክፍሎች ይገኛሉ። ከነርሱ መካከል አብዛኛው ስለሼኽ አብዱላህ አል-ሐረሪም ሆነ ስለ አህባሽ ምንም ሳያውቅ በንዴት ብቻ ከአህባሾች ጋር ግንኙነት የመሰረተ ነው። እነዚህ ወገኖች የት ነው ያሉት? ይህንን ማስረዳት ቀላል ነው።

በሀገራችን ውስጥ ሰዎች ለዚያራ የሚጎርፉባቸው የአውሊያ ደሪሆችና ሀድራዎች በብዛት አሉ። ለምሳሌ የባሌው ዲሬ ሼኽ ሁሴን፤ የወሎው ጀማ ንጉስ፤ አኒይ፤ ዳኒይ፤ ወዘተ.. የጉራጌዉ የቃጥባሬ ሀድራ፤ በምስራቅ ኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ቦታዎች ያሉ ሀድራዎች ወዘተ... ይጠቀሳሉ። የነዚህ ደሪሆችና የሀድራ አስተዳዳሪዎች የሚከተሉት እስልምና ከትክክለኛው እስልምና በእጅጉ ይራራቃል። ባህልና ልማድ ተቀላቅለውበታል።

ባለፉት ሀያ አመታት ውስጥ ዳኢዎች ስለ "አላህ" ተውሂድ ሲያስተምሩ እነዚህ የሀድራ ሰዎች "ከአባቶቻችን የወረስነውን ዲን ለማራከስ ነው የመጣችሁት" በማለት ከዳኢዎች ጋር ግብግብ ይገጥሙ ነበር። "ወሀቢ" እያሉ ይወርፏቸዋል። እንደዚያም ሆኖ ግን "ወሀቢ" ከሚሉት ቡድን ጋር አልተቆራረጡም። ሁለቱም በአንድ መስጊድ በሚሰገድ የተራዊህ ሰላት ላይ በሀይለኛ ሁኔታ ተጣልተው በማግስቱ አንድ ላይ የሚሰግዱበት ሁኔታ አለ። የዚህ ምክንያቱ ሁለቱም "ከፍረሃል" የማይባባሉ በመሆናቸው ይመስለኛል።

ነገር ግን ወጣቱ ክፍል የተውሂድን ትርጉም እየተረዳ በመምጣቱ ከዚያራና ከሀድራ እየሸሸ ነው። በዚህም የተነሳ የሀድራ ሰዎች "ወሀቢያ" በሚሉት

የወጣቱ ክፍል ላይ የቋጠሩት ቂም እንዳለ ነው ያለው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "አህባሽ" እነዚህን "አኩራፊ" ወገኖቻችንን እያደነ "እጅግ የረቀቀ" ፍልስፍናውን እያስተማራቸው ነው። በዚህም የተነሳ ጥንት በሀድራ ሰዎች ዘንድ የማይታወቀው "ኢብን ተይሚያህ" ዝነኛ ሰው እየሆነ ነው። (ማለትም የሀድራ ሰዎች "ወሀቢ" የሚባለው ቡድን የሼይኽ ሙሀመድ ኢብን አብዱል ወሃብን ትምህርት የሚከተል እንደሆነ ነው የሰሙት። አህባሽ ግን "ወሀቢ"ን የጀመረው ኢብን ተይሚያህ የሚባል ፈላስፋ ነው" እያለ ያስተምራቸዋል።)

እነዚህ ወገኖች የአህባሾች ሰለባ የሚሆኑት ዳኢዎች በሚያሳዩዋቸው የሂክማ (አካሄድና አቀራረብ) ጉድለቶች ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ዳኢዎች "ሀቅ መደበቅ የለበትም" ይሉና ሰውየው እንዲገለጽበት የማይፈልገውን ደካማ ጎኑን ይነካኩታል። አንዳንዶቹ ዳኢዎች ጭራሽ ከመስመር ይወጣሉ። (ለምሳሌ የሽርክን አስፈሪነት በዘዴ እየተነተነ ማስተማር የነበረበት አንድ ዳኢ የአንድ ታዋቂ ቤተሰብን ስም እየጠቀሰ "እነ እገሌ እኮ ሙሽሪኮች ናቸው" እያለ ዳእዋ ሲያደርግ አጋጥሞኛል)። በዚህም የተነሳ የሀድራ ሰዎችና በሀድራ ዙሪያ የሚኖሩ ማህበረሰቦች በእልህ ወደ አህባሽ ይከበልላሉ።

ስለዚህ እነኝህ ወገኖቻችን የአህባሽ ሰለባ እንዳይሆኑብን ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ዳኢዎች የአላህን ቃል በሂክማና በጥበብ ማስተማር አለባቸው።

አህባሾች በኔ ትንተና ይህንን ይመስላሉ። ከኔ በበለጠ ሁኔታ ስለ አህባሽ የሚያውቁ አንባቢዎች የሚያዉቁትን ሁሉ ለወንድሞቻችንና ለእህቶቻችን እንዲናገሩ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

አላህ ከአህባሽና ከፈተናው ይጠብቀን። ድል የኢስላም ነው። አላሁ አክበር!!!!

**ክፍል አስራ አራት፡ የአህባሽ የሰበካ ስልቶችና የጥቃት ዒላማዎች**

አህባሾች ምን አይነት ሰዎችን ነው ለጀመኣ አባልነት የሚመለምሉት? ምን አይነት ስልቶችን ነው የሚጠቀሙት? በዚህ ክፍል በነዚህ ላይ እናተኩራለን፡፡

***በሀገራችን ያለው የአህባሽ ጀመዓ ስርጭት***

ዛሬ አህባሽ ጠንካራ ጀመኣ የመሰረተባቸው ከተሞች

- አዲስ አበባ (ትልቅ መርከዝ አለው)
- ሀረር (መርከዝ አለው)
- ድሬዳዋ (መርከዝ ያለው አልመሰለኝም)
- ጎንደር (ጀመኣው ጠንካራ ነው ይባላል፡፡ ሆኖም የራሳቸው መርከዝ ያላቸው መሆኑን አላረጋገጥኩም)፡፡

የ"አህባሽ"ን ፍልስፍና በትክክል የሚያውቁ ሰዎች ያሉት በነዚህ ከተሞችና በአካባቢያቸው ነው፡፡ ከነርሱ ውስጥም ብዙዎቹ ወደ መርከዝ እየሄዱ የታእሊም ፕሮግራማቸውን ይከታተላሉ፡፡ አንዳንዶቹም (በተለይም የቢሮ ሰራተኛ የሆኑት) እሁድና ቅዳሜ ወደ መርከዝ ይሄዳሉ፡፡

አህባሽ መሰረቱን ለማስፋት ጥረት የሚያደርግባቸው ሌሎች ቦታዎች

- በኦሮሚያ ክልል ብዙ ስፋራዎች
- በወሎ ክፍል ሀገር በብዙ ስፍራዎች
- በትግራይ ክልል አንዳንድ ስፋራዎች ናቸው፡፡

በነዚህ አካባቢዎች "ወሀቢያ የአባቶቻችንን እምነት አራክሷል" በማለት ያኮረፉ በርካታ ሰዎች በመኖራቸው ነው አህባሽ በነርሱ ላይ ትኩረት ያደረገው፡፡ አንጃው ከነርሱ ጋር ግንኙነት መፍጠር የጀመረው ቆይቶ ነው፡፡ ምክንያቱም በሀገራችን ውስጥ የተከለው ማዕከል ውሱን አቅም ነው ያለው፡፡ በሌላም በኩል አህባሽ "ትክክለኛው የአህሉ-ሱንና አቂዳ እኔ ጋር ነው ያለው" በማለት ስለሚጀነን (ስለሚኩራራ) እነዚህን አኩራፊ ወገኖች ዝቅ አድርጎ የማየት ነገርም አለበት፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ከአኩራፊዎቹ ጋር ያለውን ቀረቤታ እያሻሻለ ነው፡፡ ለምሳሌ የአህባሽ ቀንደኛ ሰዎች ከአኩራፊዎቹ ጋር መቀራረብ፤ በነርሱ ጀመኣ መስገድ ወዘተ... የመሳሰሉ ለውጦችን እያሳዩ ነው ::

አኩራፊዎቹ እስካሁን ድረስ የአህባሽን ፍልስፍና ሙሉ በሙሉ የተረዱት አይመስለኝም። ለምሳሌ "አላሁማ አጂርና ሚነን-ናር" (አላህ ሆይ! ከእሳት ቅጣት ጠብቀን) የሚለው ታዋቂ ዱኣ በአህባሽ ዘንድ እንደማይፈቀድ አኩራፊዎቹ የሰሙት አይመስለኝም።(ይህ ዱኣ በወሎ ገጠራማ መንደሮች ባሉ ሀድራዎች የሚማሩ ደረሳዎች በጀመዓ የሚያደርጉት ታዋቂ ዱዓ ነው)።

## *የአህባሽ ዒላማዎች*

አህባሽ በጣም የሚያተኩረው ለአቅመ አዳም ባልደረሱ ልጆች ላይ ነው። በተለይ ቁርአንና አረብኛን በቤትና በመድረሳ አካባቢ የተማሩ ህጻናትን ወደ ጀመኣው ለመቀላቀል ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል። አንጃው ይህንን የሚያደርግበት ምክንያት ግልጽ ይመስለኛል። መናገር ካስፈለገም እነዚህ ህጻናት ሌላ አይነት የአቂዳና የፊቅህ ትምህርት ስላልተማሩ የአንጃውን ፍልስፍና ያለአንዳች ክርክር ይቀበሉለታል። ከትምህርት በኋላም አንጃው በሚፈልገው መልኩ እነርሱን ማሰማራቱ ችግር አይሆንበትም።

ከአዋቂዎች መካከል አንጃው የሚያተኩረው

- ከላይ የጠቀስኳቸው አኩራፊዎች በሚበዙባቸው አካባቢዎች ያሉ ማህበረሰቦች (ለምሳሌ የባሌው ዲሬ ሼኽ ሁሴን ባለበት ስፍራ የሚኖሩ ሰዎች)
- በ"ወሀቢያ" ላይ ቂም የቋጠሩ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና ታዋቂ ግለሰቦች (ለምሳሌ በመጅሊስ ውስጥ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ጸረ-ወሀቢያ መሆናቸውን ለማሳወቅ ሲጥሩ ይታያሉ። አህባሽ እነዚህን ሰዎች በጣም ይፈልጋቸዋል)።
- በአንዳንድ ልማዶቻቸው ገዘፈው የሚታዩ ሰዎች (ለምሳሌ በቤታቸው የ"መውሊድ" ድግስ የሚደግሱ ሰዎች )
- በቅርብ ጊዜ ወደ ኢስላም የገቡ ሰዎች
- ወዘተ...

አህባሽ በሀገራችን ውስጥ በሚያደርገው እንቅስቃሴ በወጣቱ ክፍል ላይ ብዙም አያተኩርም። እንዲህ የሆነውም ፍላጎቱ ጠፍቶት ሳይሆን የሀገራችን ወጣቶች እርሱ የሚፈልጋቸው አይነት ስላልሆኑ ነው። ለምሳሌ ወጣቶቻችን በትምህርት ክፍለ ጊዜ "ለምን፤ እንዴት፤ ምክንያቱስ፤" የመሳሰሉ ጥያቄዎችንና "ማስረጃውን ከቁርአንና ከሀዲስ አምጣ" ማለትን ተክነውበታል።

አህባሽ ግን "አሊም የነገረህን ሳትጠራጠር ተቀበል፤ ክርክር አታብዛ" ባይ ነው። በዚህ የፍራቻ አቋሙ ከወጣቶቻችን ፊት የሚቆምበት ወኔ የለውም።

በውጪ ሀገራት የሚንቀሳቀሰው አህባሽ ግን በርካታ ወጣቶችን ለመሳብ ችሏል። የዚህ ምክንያት እንደየሀገሩ ይለያያል። ለምሳሌ በሰሜን አሜሪካ በርካታ የፈረንጅ ወጣቶች ስለእስልምና ለማወቅ ይፈልጉና ወደ አህባሾች ጀመኣ ይጠጋሉ። አህባሽም በእስልምና ስም ፍልስፍናውን ያስተምራቸዋል። በሊባኖስ፤ በሶሪያና በቱርክ ደግሞ ጤናማ የሆነውን እስልምና በሚያስተምሩ ቡድኖች ላይ ከፍተኛ ተጽእኖና ጭቆና ስለሚደረግ ወጣቱ ዘንድ ለመድረስ በጣም ይቸገራሉ። የተበከለውን እስልምና የሚያስተምሩት አህባሽና ቢጤዎቹ ግን በነጻ ነው የሚንቀሳቀሱት።

## *የምልመላና የሰበካ ስልቶች*

- አህባሽ ጽንፈኝነቱ እንዳይታወቅበት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጋል። ባለፈው ክፍል የጠቀስኳቸው ጽንፈኛ አባላቱ እንኳ ይህንን ደካማ ጎናቸውን ላለማሳየት በጣም ነው የሚጠነቀቁት። ለምሳሌ በደንብ ከማያውቁት ሰው ጋር በዲን ጉዳይ አይከራከሩም። ከሰውዬው ጋር ተከራክረው አስጨናቂ ውጥረት ውስጥ ሲገቡ ደግሞ ራሳቸው የሚያስተምሩትን ነገር እንኳ የሚክዱበት ወቅት አለ።
- አንጃው ዋነኛ የማስተማሪያ መጽሀፍቱን ለማንም ሰው አይሰጥም። እነዚህን መጽሀፍት የሚያገኙት አንጃው ሙሉ እምነት የሚጥልባቸው አባላት ናቸው። ለሌሎች ሰዎች የሚቀርቡት በራሪ ጽሁፎችና በአነስተኛ ገጾች የተዘጋጁ ትንንሽ መጽሀፍት (pocket book የሚባሉት) ናቸው። (ለምሳሌ በሀረማያው ስልጠና የተበተኑት መጽሀፍት የአንጃውን ድብቅ እምነቶች አያሳዩም። እነዚያ መጽሀፍት "ፈዲሀቱል ወሀቢያ" (የወሀቢ ጥፋት) እና ከዚህ ጋር የሚመሳሰሉ ርእሶች ነው ያላቸው።)
- አንጃው አዲስ ገቢዎችን ለመጥለፍ እንዲመቸው ቴጃሮችንና ታዋቂ ግለሰቦችን ይጠቀማል።
- የአንጃው አባላት ጓደኞቻቸውን ይጀነጅናሉ። በገንዘብና በጉርብትና በኩልም ሰዎችን ለመጥለፍ ይሞክራሉ። ይህንን የሚያደርጉት ግን ብዙ ኢልም የሌላቸውን ሰዎች እየመረጡ ነው።

- የአህባሽን መስራች ከልክ በላይ እያገዘፉ ማወደስም ሌላው ዘዴ ነው። ስለ ሼኽ አብዱላህ ብጹእነት፤ ስለ እውቀታቸው፤ ስለዘር ሀረጋቸው፤ ስለ ከራማቸው ወዘተ... እየተደጋገመ ይጻፋል፤ ይወራል።
- ትልቁ የፕሮፓጋንዳ ስልታቸው ግን "ወሀቢያን" እንደ ጭራቅ አድርጎ መሳል ነው። በመሆኑም "ወሀቢ" በሚሉት ቡድንና ኢብን ተይሚያህ፤ ኢብን አብዱል ወሃብ፤ ሰይድ ቁጥብ፤ ኢብን ባዝ ወዘተ... በመሳሰሉ ምሁራን ላይ የማያቋርጥ እርግማን ይወርድባቸዋል። በቅጥፈት የተፈበረኩ ወሬዎችና ተረቶች ይወራባቸዋል። ለምሳሌ ከዚህ ቀደም የነገርኳችሁ "የእንግሊዛዊው ሰላይ የጸጸት ማስታወሻ" አህባሾች ለፕሮፓጋንዳ ከሚጠቀሙባቸው ታላላቅ መሳሪያዎች አንዱ ነው።
- በአለም አቀፍ ደረጃ የሚጠቀሙበት ዋነኛው መሳሪያ ኢንተርኔት ነው። የኢንተርኔት ገጾችንና ብሎገሮችን በድርጅት ስም ብቻ ሳይሆን በግለሰቦችም ስም ይከፍታሉ። (በኢንተርኔትም ቢሆን ትልቁ ዘመቻ የሚካሄደው በ"ወሀቢያ" ላይ ነው።)

በመግቢያዬ ላይ እንደለጽኩት አህባሽ ወደ ሀገራችን ከገባ ድፍን አስር አመት ሆኖታል። በዚህ ቆይታው አስር ሺህ አባላትን እንኳ አላፈራም። አንድ ሰሞን ረብሻ ለመፍጠር ሞክሮ ሰው "ሆይ ሆይ" ሲለው ድምጹን ወዲያዉኑ ነው ያጠፋው። አብዛኛው የኢትዮጵያ ህዝብ "አህባሽ" የሚለውን ስም የሰማው ዘንድሮ ነው። ይህ ቡድን እስከዛሬ ድረስ በሺዎች በሚቆጠሩ ተከታዮቹ ብቻ ተገድቦ የቆየው በምን ተአምር ይሆን?

ይህ የአላህ ተአምር ነው እላለሁ። አላህ በጥበቡ ከመርከዝ ውጪ እንዳይሰማ አድርጎታል። ለወደፊቱም እዚያው ባለበት ያቁምልን! አሚን!!!

## ክፍል አስራ አምስት፡ የኑፋቄ እና የጥመት ፊርቃዎች ከ"ሙርጂዓ" እስከ "አል-አህባሽ"

ባለፈው ክፍል ባቀረብኩት ጽሁፍ የሙስሊሙን አንድነት ከአህባሽ ፈተናዎች መጠበቅ እንደሚገባን ተናግሬ ነበር። ከዚህ በማስከተልም በኢስላም ታሪክ የተከሰቱትን ታላላቅ የኑፋቄና የጥመት ፈተናዎች፤ በኢስላም ላይ ያስከተሉትን አደጋዎችና ኡለማዎች ፈተናዎቹን ለመቋቋም የወሰዷቸውን እርምጃዎች እንቃኛለን።

በዚህ ክፍል የምንዳስሰው ዘመን ተሻግረው እስከአሁን ድረስ ሊቆዩ ያልቻሉትን ጥንታዊ ፊርቃዎች ብቻ ይሆናል። የተቀሩትን በሚቀጥለው ክፍል እናያቸዋለን።

### *በኢስላም ጥንታዊ ዘመን የተከሰቱ የኑፋቄና የጥመት ቡድኖች*

1. **ሙርጂዓ (በ7ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ የተከሰተ)፡-** ይህ ቡድን *"ትልቅ ሀጢአት የሰራ ሰው ይከፍራል"* ለሚለው የኸዋሪጃ አቋም ምላሽ አስገኝለሁ በማለት ነበር የተነሳው። የቡድኑ ጀማሪ ማን እንደሆነ አይታወቅም። ኡለማ ከቀደምት ታቢኢዮች መካከል ከኸዋሪጃ ጋር ጦር የተማዘዙ ወገኖች ይህንን ቡድን ሳይፈጥሩ እንዳልቀሩ ይገምታሉ።
   ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ሙርጂአዎች "ትልቅ ሐጢአት የሰራ ሰው ወዲያውኑ ነው የሚከፍረው" ለሚለው የኸዋሪጃ አቋም መድሃኒት አለን ባይ ነበሩ። ታዲያ ሀጢአተኛ የሆኑ ሙእሚኖችን ከኸዋሪጅ "ተክፊር" ለማዳን በሚል ምክንያት የያዙት አቋም በኋላ ላይ *"ሀይማኖት ማለት እምነት ብቻ ነው። ማንም ሰው በአላህ ካመነ ጀነት ይገባል"* ወደሚለው አስተሳሰብ ተቀየረ። ይህም በሌላ ቋንቋ "የኢማን መሰረቶች እንጂ የኢስላም መሰረቶች አስፈላጊ አይደሉም" እንደማለት መሆኑ ነው። እነዚህ ወገኖች በዚህ አቋማቸው በሙስሊም ኡለማዎች በሰፊው ተወግዘዋል።
2. **ቀደሪያ (ከ700ዎቹ መጀመሪያ እስከ 750 አጋማሽ) ፡-** ይህኛውም ፊርቃ በማን እንደተመሰረተ በውል አይታወቅም። በሙስሊሙ ምድር ከግማሽ ምእተ አመት በላይ ለመቆየትም አልቻለም። ሆኖም በዚህ ፊርቃ የተነሱ የኑፋቄ ትምህርቶች በሌሎች ፊርቃዎች ተወርሰው ለተወሰኑ ዘመናት ቆይተዋል።

ቀደሪያ በጣም የሚታወቀው *"አላህ የጻፈው ቀደር (predestination) የለም። ሰዎች የየራሳቸው "ቀደር" (Free will) አላቸው፤ እጣ ፈንታችን በፈጣሪያችን ዘንድ ሳይሆን በእጃችን ውስጥ ነው ያለው"* በሚለው አስተምህሮው ነው።

3. **ጀህሚያ (750ዎቹ እስከ 800ዎቹ መጀመሪያ)** ከቀደሪያ ቀጥሎ የሚጠቀሰው የኑፋቄ ፊርቃ (አንጃ) ጀህሚያ ይባላል። ይህ ፊርቃ በጀህም ኢብን ሰፍዋን (በ746 በኡመያዊያን ኸሊፋዎች በሞት የተቀጣ) ጠንሳሽነት ነው የተጀመረው። ታዲያ ይህኛውም ፊርቃ ብዙ ሳይቆይ ነው እንደ "ቀደሪያ" ብንን ብሎ የጠፋው።
ጀህሚያዎች *"አላህ ዛት (እርሱነት ወይም Essence) እንጂ ሲፋት የለውም"* ባይ ናቸው። ምክንያታቸውንም ሲያስረዱ "አላህ ሲፋት አለው ማለት ፈጣሪን ከፍጡራን ጋር ማመሳሰል ነው" ይላሉ።
በዚህም የተነሳ "አላህ ይናገራል፤ ያያል፤ ይሰማል፤ ይደሰታል" የመሳሰሉ ቁርአናዊ አባባሎችን ሲተረጉሙ ከመደበኛ ፍቺያቸው ያጣምሙዋቸዋል።
በሌላ በኩል "ቁርአን መኽሉቅ ነው" የሚለውን ፍልስፍና ያመጡት ጀህሚያዎች ናቸው። የዚህንም ምክንያት ሲያስረዱ "ፈጣሪ ከሰው ጋር የሚመሳሰልበት ባህሪ የለውም። በመሆኑም ፈጣሪ አይናገርም። ስለዚህ ቁርአን የርሱ ንግግር ሳይሆን በርሱ የተፈጠረ መጽሀፍ ነው።" ይላሉ።

## *"ሙዕተዚላ" - ስመ-ገናናው የኑፋቄ ቡድን (ከ750ዎቹ እሰከ 1200 ዓ.ል)*

በኢስላማዊው ዓለም ከታዩ ታላላቅና እጅግ አነጋጋሪ የኑፋቄ ፊርቃዎች አንዱ "ሙዕተዚላ" ነው። ከዚህ ቀደም እንደገለጽኩት የዚህ ፊርቃ ጥንስስ የተጣለው ዋሲል ኢብን አጣእ የሚባለው የሐሰን አል-በስሪ ተማሪ "ትልቅ ሀጢአት የሰራ ሙስሊም መጨረሻው ጀሀነም ነው ወይስ ጀነት?" በሚለው ጥያቄ ላይ ከመምህሩ ጋር በነበረው መጠነኛ የስነ-መለኮት ልዩነት ነው። ዋሲል ከሀሠን አል-በስሪ (ረ.ተ) ከተለየ በኋላ በርካታ ተማሪዎችን በማሰባሰብ በሌሎችም የአቂዳ ጉዳዮ ላይ ልዩ ልዩ ትንተናዎችን ማካሄድ ጀመረ። የዋሲል ተማሪዎችም ኢስላማዊውን አቂዳ በግሪኮች የፍልስፍና መንገዶች መተንተኑን በስፋት ተያያዙት። በዚህም "የእምነት መሰረት ምክንያታዊነት ነው እንጂ ወህይ አይደለም" የሚልና መላውን ኡማ ያስደነገጠ አቋም ያዙ። በአጭሩ

“መኢተዚላ” በኢስላም ቋንቋ የሚናገር ግሪክ-ቀመስ የስነ-አመክንዮ ቡድን ሆኖ ተገኘ።

የመኢተዚላ ፊርቃ በደንብ ከሚታወስባቸው አቋሞቹ መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

- አላህ “ዛት” እንጂ “ሲፋት” የሉትም።
- ቀደርንና ቀዷ በኢማን መሰረቶች ውስጥ አይካተቱም።
- የእምነት መሰረቱ አመክንዮ እንጂ “ወህይ” አይደለም።
- ቁርአን መኽሉቅ ነው እንጂ የአላህ ንግግር አይደለም። ዘላለማዊም (eternal) አይደለም።
- አል-መንዚላ በይነል መዚለተይን (በሁለቱ ቤቶች መካከል ሶስተኛ ቤት) መኖሩ እርግጥ ነው። (እንዲህ ሲሉ “ታላላቅ ሐጢአቶችን ሰርቶ ተውባ ሳያደርግ የሞተ ሙስሊም ጀነትም ሳይገባ፤ ወደ ጀሀነም ሳይወረወር ለዘላለም የሚኖርበት ቦታ አለ” ማለታቸው ነው)።

መኢተዚላዎች በነዚህ አቋሞቻቸው ሙስሊሙን ህዝብ ማስደንገጣቸው ሳያበቃ በ9ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነገሰው ኸሊፋ አል-ማእሙን ፍልስፍናቸውን ተቀብሎ በማጽደቅ በኡማው ላይ በሀይል ለመጫን ተነሳ። በተለይ “ቁርአን መኽሉቅ እንጂ የአላህ ንግግር አይደለም” የሚለውን የመኢተዚላ አቋም የማይቀበለውን ማንኛውንም አሊም አይቀጡ ቅጣት ለመቅጣት ቆረጠ። ለዚህም “ሚህና” የሚባል “የፈተና ሽንጎ” አቋቋመ። በዚህ ሽንጎ ፊት ቀርቦ “ቁርአን መኽሉቅ ነው” የሚል ቃል ያልሰጠ አሊም በይፋ እንዲገረፍና ሀብቱ እንዲዘረፍ አወጀ።

በዘመኑ የነበሩት ኡለማ በእጅጉ ተሰቃዩ፤ ተገረፉ። በርካቶችም የኸሊፋውን ቅጣት በመፍራት “ቁርአን መኽሉቅ ነው” አሉ። አንዳንዶችም ከሀገር ተሰደዱ። ታዲያ በዚያ የመከራ ዘመን ትክክለኛውን የአህሉ-ሱንና አቂዳ ለመጠበቅ ሰበብ ይሆን ዘንድ አላህ አንድ አስገራሚ ጀግና አስነሳ።

ይህ ጀግና ታዋቂው አሊም ***ኢማም አህመድ ኢብን ሀንበል*** (ረ.ተ) ነው። ኢማም ኢብን ሀንበል ለማእሙን “ሚህና” ሳይሸበር *“ቁርአን የአላህ ቃል ነው፤ የአላህ ቃል “መኽሉቅ ነው” የሚሉ ሰዎች ከኢስላም ወጥተዋል”* ብሎ ተናገረ። ኸሊፍ አል-ማእሙን ቃሉን እንዲያጥፍ ቢመክረው “እንቢ አለ። በሹመት ቢያባብለውም በአቋሙ ጸና። በነገሩ የተናደደው አል-ማእሙን ኢብን-ሀንበል

በህዝብ ፊት እንዲገረፍ አዘዘ። ከዚያም ወደ እስር ቤት ወረወረው። አል-ማእሙን ከሞተ በኋላ የነገሱት አል-ሙእተሲም እና አል-ወሚቅ የተባሉ ኸሊፋዎችም ኢብን ሀንበልን የሚችሉትን ያህል አሰቃይተውታል። ኢብን ሀንበል ግን ለቅጣት ሳይበገር በአቋሙ ላይ እንደጸና ቆየ።

በ833 የተጀመረው የአል-ሚህና ፈተና ያበቃው በ861 አል-ሙተወኪል የተባለው ኸሊፋ ሲነሳ ነው። ይህኛው ኸሊፋ እውነተኛ ሙስሊም በመሆኑ የሚህናን ሸንጎ ወዲያውኑ ነው የበተነው። ኢብን ሀንበልንም ከነበረበት እስር ቤት በማውጣት በክብር አኑሮታል።

ኸሊፍ ሙተወኪል "ሙዕተዚላ የሚያስተምረው የኑፋቄ መንገድ ነው" በማለት የሙዕተዚላ ምሁራን በቃዲነትና በሙፍቲነት እንዳይሰሩ እገዳ ጥሎባቸዋል። በዚህ ብቻም ሳያበቃ የሙዕተዚላ ምሁራን በሙስሊሙ ምድር እንዳያስተምሩ አድርጓቸዋል። በመሆኑም በበስራ እና በባግዳድ ተጠናክረው የነበሩት ትምህርት ቤቶቻቸው ተዘግተዋል። ከሙተወኪል በኋላ የተነሱ ኸሊፋዎችም የሙእተዚላን ፍልስፍና ከሙስሊሙ ዓለም ለማስወገድ ከፍተኛ እርምጃዎችን ወስደዋል። ሆኖም ሙእተዚላዎች ከኸሊፋ ቤተመንግስት ለሚመጣባቸው ጫና አልተበገሩም። እንዲያውም አደገኛ የሙእተዚላ ሊቃውንት በየክፍለ ሀገሩ እንደ አሸን ፈልተዋል።

## *የአሀሉስ ሱንና ኡለማ ትግል እና የሙእተዚላዎች ፍጻሜ*

ሙእተዚላዎች በቆዩባቸው አምስት ክፍለ ዘመናት በእጅጉ የተፈታተናቸው ሐይል ቢኖር ***የአሀሉስ ሱና ኡለማዎች*** ቡድን ነው። ይህ ቡድን በቀደምት ዘመናት በሲራ (ታሪክ)፤ በፊቅህ እና በሀዲስ ላይ እንጂ በአቂዳ ጉዳዮች ላይ ብዙ ምርምርና ምልልስ አያደርግም። ምክንያቱም እውነተኛው የሙስሊሞች አቂዳ በትክክል ስለሚታወቅና ሙስሊሙ ያለ አንዳች ልዩነት ስለሚያምንበት በርሱ ላይ መከራከሩ አስፈላጊያቸው አልነበረም። ሆኖም እንደ ሙርጂአ እና ጀህሚያን የመሳሰሉ ቡድኖች ሲነሱ የሱኒ ኡለማዎች ተገቢ መልሶችን ሰጥተዋቸዋል።

ኸሊፋ ማእሙን "አል-ሚህና" የተሰኘውን የአፈርሳታ ሸንጎ ካቋቋመ በኋላ ግን "ሙእተዚላ" በትክክለኛው የኢስላም አቂዳ ላይ ታላቅ አደጋ እንደ ደቀነ ታወቀ። "ከስፔን እስከ ህንድ በተዘረጋው የሙስሊም ምድር ውስጥ የተበተነው የሙእተዚላ ፍልስፍና በጊዜ ካልተመነጠረ የኢስላም ህልውና ያበቃለታል"

በሚለው ሀሳብ ላይ ሙስሊሞች ተስማሙ። በዚህም ታዋቂ ኢማሞች ከሙእተዚላዎች ጋር ግልጽ የሆነ ክርክር ማድረግ ጀመሩ። የአቂዳ መፅሀፍትንም በገፍ ይጽፉ ገቡ።

በዚህ ሂደት ስማቸው ጎልቶ ከሚጠቀሰው የአቂዳ ኢማሞች መካከል ኢማም አቡል ሐሰን አል-አሽዓሪ በኢራቅና በአረቢያ፤ ኢማም አቡ ጃእፈር አል-ጠሃዊ (የአቂደቱ ጠሃዊያ ደራሲ) በግብጽ፤ እንዲሁም ኢማም አቡል-መንሱር ማቱሪዲ በኹራሳን (መካከለኛው እስያ) ያደረጓቸው ተጋድሎዎች በቀዳሚነት ይነሳሉ (ሶስቱም ኢማሞች ከ9ኛው-10ኛው ክፍለ ዘመን ድረስ ነው የኖሩት)። እነዚህ ሶስት ኢማሞች ባደረጉት ትግል አላህ የሙእተዚላን ተጽእኖ በጣም ነው የቀነሰው። በተለይ ሙእተዚላዎች በተራው ህዝብ ዘንድ ድጋፍ እንዳይኖራቸው ሰበብ የሆነው የነዚህ ኢማሞች ትግል ነው።

ሆኖም ሙእተዚላ በሊቃውንቶች አካባቢ የነበረው ድጋፍና ተጽእኖ ለተጨማሪ ሁለት ከፍለ ዘመናት ቀጥሏል። በተለይ አል-ፈረቢ እና አል-ኪንዲን የመሳሰሉ ሊቃውንት ለግሪክ ፍልስፍና በነበራቸው እውር ፍቅር ምክንያት የሙእተዚላዎች የስነ-አመክንዮ ሙግት በሙስሊሙ ዓለም ዳግም እንዲያንሰራራ የቻሉትን ያህል ጥረዋል። እነዚህ ሰዎች ስለ ሳይንስ የሚጽፉ እያስመሰሉ ደንበኛውን የሙእተዚላ አቂዳ መስበክን ተያያዙት። አላህ ልቦና የሰጣቸው አስተዋዮች ግን ይህንን አደገኛ አካሄድ ለማስቆም ተንቀሳቀሱ። በዚህም ሂደት የሙእተዚላ ኑፋቄ ሙሉ በሙሉ የተወገደበት ሁኔታ ተከሰተ።

እነዚህ አስተዋዮች እነማን ናቸው? መልሱ አንድና ሁለት አይደለም። ነገር ግን በዚያ ዘመን ከሁሉም ጎልቶ የታየው ስራ የቀረበው በኢማም አቡል ሀሚድ አል-ገዛሊ ነው። ኢማም ገዛሊ የጻፉት "አል-ተሀፉተል ፈላሲፋ" (የፈላስፋዎች ውድመት) በቀጥታ ያነጣጠረው የሙእተዚላን አቂዳ በሚያቀነቅኑት ፈላስፋዎች ላይ ነው። ይህ መጽሀፍ ከተጻፈ ወዲህ የሙእተዚላዎች አስተሳሰብ ራሱን ቀና ማድረግ አልቻለም። በመጨረሻም በየቦታው የተበታተነው ሽርፍራፊ ቀስ በቀስ እየመነመነ ወደ መቃብር ገብቷል።

## *ማጠቃለያ*

የ"ኑፋቄ"ና የጥመት አራማጆች በሙስሊሙ አለም የታዩት ዛሬ አይደለም። ኸሊፋ ኡስማን ኢብን አፋን(ረ.ዐ) በግፍ ከተገደሉበት ጊዜ ጀምሮ ጠማማዎችና

የኑፋቄ አፍቃሪዎች ከሙስሊሙ አለም አልተለዩም። ሆኖም ዲኑን ያሸነፉበት ወቅት የለም። አላህ ኑፋቄዎቹን የሚያስነሳው ለፈተና ነው። ዛሬ በሀገራችን ቦታ አገኘሁ ብሎ የሚኩራራው አህባሽም ቢሆን ለፈተና ነው የተላከብን። ስለዚህ በኛ ዘመን ብቻ የታየ ክስተት ተደርጎ መታየት የለበትም። እኛ በብርታት ከተጋፈጥነው አላህ ፈተናዎችን ያቃልልልናል። ስለዚህ እንበርታ ያ ጀመዓ!

ቀሪውን ክፍል በሚቀጥለው ጽሁፍ እዳስሰዋለሁ።

ድል የኢስላም ነው!!

**ክፍል አስራ ስድስት፡ አል-አህባሽ እና ዘመናዊ የጥመትና የኑፋቄ ፊርቃዎች**

ባለፈው በክፍል ዘመናትን መሻገር ያልቻሉትንና በሙስሊሙ አለም የታዩትን ቀደምት የኑፋቄና የጥመት ፊርቃዎች በትንሹ ለመዳሰስ ሞክሬአለሁ። በዚህ ጽሁፍ ደግሞ በቅርብ ዘመናት የታዩትን ሁለት ፊርቃዎች ከአህባሽ ጋር እያስተያየን እንገመግማቸዋለን።

***አህመዲያ***

ይህ ፊርቃ በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ላይ (በ1890 ዓ.ል.) በፓኪስታን ሀገር ላሆር ከተማ የተመሰረተ ሲሆን መስራቹም ሚርዛ ጉላም አህመድ ይባላል። ይህ ሰው "የአዲሱ ዘመን ነቢይ እኔ ነኝ" በማለት ነበር የተነሳው።

ሚርዛ ጉላም አህመድ የነቢይነት ጥያቄው ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ በቅዱስ ቁርኣን ሱረቱል ሶፍ 6ኛው አያህ የተጠቀሰውን የነቢዩ ኢሳን ትንቢት እንደ ማስረጃ ይጠቅሳል። በዚህ አያህ የተጠቀሰው "አህመድ" የሚባለው የአላህ መልዕክተኛ እኔ ነኝ" ብሏል። "ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፤ ነገር ግን የአላህ መልእክተኛና የነቢያት መደምደሚያ ነው" የሚለው የሱራ አል-አህዛብ 40ኛ አያት በነቢይነቱ ላይ እንቅፋት እንዳይሆንበት የአያውን ትርጉም በማጣመም "ኻተሙን ነቢይዩን" የሚለው አባባል "የነቢያት መጨረሻ" ማለት ሳይሆን የነቢያት ጌጥ ማለት ነው" የሚል ፍቺ ሰጥቷል። ይህንን ትርጉም ሲያስፋፋ "ከአላህ ሸሪዓ ተቀብለው የሚላኩ ነቢያት የሚላኩበት ዘመን በነቢዩ ሙሐመድ ላይ አብቅቷል። ነቢያችን የተላኩበት ቁርአን ከሁሉም የላቀና እንከን የማይወጣለት የአላህ ቃል በመሆኑ ሙሐመድን የነቢያት ጌጥ እንዲሆን አድርጎታል። ሆኖም ኢሳ የተነበየው ነቢይ አህመድ የሚባል እንጂ ሙሐመድ አይደለም። ያ ባለ ትንቢተኛው ነቢይም እኔ ነኝ" የሚል ሙግት አምጥቷል።

ኡለማእ ሚርዛ ጉላም አህመድን ወዲያዉኑ ነበር ያወገዙት። "እርሱና በርሱ ያመኑት ሁሉ ካፊሮች ናቸው" በማለት አውጀዋል። ነገር ግን ሰውየው በዘመኑ አነስተኛ ተከታዮችን ለማፍራት ችላል። ለዚህ የረዳውም በዘመኑ የሰፈነው ጁህል (መሃይምነት) እና ከእንግሊዝ ቅኝ ገዥዎች ያገኘው ድጋፍ ነው። ይህ አንጃ ከኢስላም የወጣ መሆኑ ቢታወቅም በዛሬው ዘመንም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተከታዮች አሉት።

ታዲያ ይህ አንጃ ከአህባሽ ጋር የሚመሳሰለው "ጂሀድ በልብና በጭንቅላት እንጂ በሰይፍ አይደረግም" በሚለው አቋሙ ነው። በአጭሩ አህመዲያ እንደ አህባሽ "ካፊሮች ቢጨቁኗችሁና ዜግነታችሁን ቢገፉት እንኳ ችላችሁ እደሩ" ይላል። በዚህ ምክንያት ይመስለኛል የጋራ ብልጽግና ማህበር (Common Welth of Nations) አባል በሆኑ ሀገራት (የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበሩት ሀገሮች) ሁሉ ለአህመዲያዎች ከፍተኛ እንክብካቤ የሚደረግላቸው።

ስለ አህመዲያ ኑፋቄ በዝርዝር ለመረዳት የሚከተለውን ዌብሳይት ይጎብኙ http://en.wikipedia.org/wiki/Ahmadiyya

### *የኢስላም ማህበረ-ህዝብ (The Nation of Islam)*

ይህ ፊርቃ በአሜሪካ በነገሰው የዘር መድልዎ ፖሊሲ የተከፉ ጥቁር አሜሪካውያንን እውነተኛ ፍላጎት ለማሟላት በሚል ምክንያት ነው በ1930 ዓ.ል. በሰሜን አሜሪካ የተቋቋመው። የማህበሩ መስራች "ዋላስ ፊርድ መሀመድ" ይባላል። የፊርቃውን የፍልስፍና ሀሳቦች በተከታዮቹ አእምሮ ውስጥ ለማስረጽ በጣም የለፋው ሰው ግን ኢሊጃህ መሀመድ ነው። አንጃው የጥቁሮች ጭቆና በተባባሰበት ዘመን የተወለደ በመሆኑ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ብዙ ተከታዮችን ለማፍራት ችሏል።

ይህ አንጃ ከትክክለኛው የአህሉ ሱንና መንገድ የሚለየው በሚከተሉት የኑፋቄ እና የጥመት ፍልስፍናዎቹ ነው።

- አንጃው "አላህ በዋላስ ፊርድ መሀመድ ውስጥ ሰርጿል" በማለት ያስተምራል።
- "ዋላስ ፊርድ መሐመድ የክርስቲያኖቹ እየሱስና የሙስሊሞቹ ማህዲ ነው" ብሎ ያምናል።
- "ጥቁር ህዝብ ከማንኛውም ህዝብ የበለጠ እና ያልተበከለ ትክክለኛ ህዝብ ነው" በማለት ያስተምራል። ጥቁሮች ከአደምና ከሀዋ በፊት እንኳ ለብዙ ሚሊዮን አመታት በምድር ላይ ነበሩ ይላል።
- ስለ ፈለክና ስለህዋ ያለው ግንዛቤ ከቁርአን ጋር በእጅጉ ይራራቃል። (ለምሳሌ ፊርቃው "መሬትና ጨረቃ ጥንት በአንድ ላይ ነበሩ" በማለት ያምናል)።

ስለዚህ ፊርቃ የበለጠ ለማንበብ ይህንን የኢንተርኔት ገጽ ይጫኑ *http://en.wikipedia.org/wiki/Nation_of_Islam*

ይህ አንጃ በአንድ ዘመን ማልኮም ኤክስና ታዋቂውን ቦክሰኛ ሙሀመድ አሊን የመሳሰሉ ጥቁሮችን በስሩ ለማሰለፍ ችሎ ነበር። ሆኖም እነዚህ ሰዎች የአንጃውን ኑፋቄ ከተረዱ በኋላ ወደትክክለኛው የእስልምና መንገድ ተመልሰዋል።

ይህ አንጃ ከአል-አህባሽ ጋር የሚመሳሰለው በሁለት መልኩ ነው።

1. አንጃው እንደ አህባሽ ከልክ በላይ ጽንፈኛ ነው። የርሱን መንገድ ያልተከተሉ ወገኖችን "ካፊር" ናቸው ይላል። በዚህ ጽንፈኝነቱም በከሀዲነት የወነጀለውን ማልኮም ኤክስን አስገድሏል።
2. አህባሾች "መሬት ጠፍጣፋ ናት እንጂ ክብ አይደለችም፤ መሬት ክብ ናት ያለ ሰው ይከፍራል" እንደሚሉት ሁሉ ይህኛውም አንጃ በጣም የተሳሰቱ የአስትሮኖሚ ትምህርቶችን ይሰብካል።

(ማሳሰቢያ፤ አህባሾች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ "ሼኻችን መሬት ጠፍጣፋ ናት አላሉም። መሬት ክብ ሳትሆን እንደ እንቁላል የመሰለ ሞላላ ቅርጽ ነው ያላት" በማለት ነው ያስተማሩት" የሚል ፕሮፓጋንዳ እያካሄዱ ነው። ሆኖም "መሬት ጠፍጣፋ እንጂ ክብ አይደለችም" እያሉ አማኞቻቸው የቂብላ አቅጣጫ እንዲቀይሩ ያዘዙበት ዶክትሪን ተመዝግቦ ስለሚገኝ ማንንም ለማታለል አይችሉም)።

## *አል-አህባሽና የፊርቃዎች ውድቀት*

ባለፉት ሁለት ክፍሎች ያየናቸው ፊርቃዎች የመነጋገሪያ ርእሶቻችን የሆኑት በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛ ፊርቃዎቹ ኢስላማዊ ካባ ደርበው ከትክክለኛው ኢስላማዊ አስተምህሮ የወጡ የኑፋቄና የጥመት ትምህርቶችን ለመስበክ መነሳታቸው ነው። ሁለተኛ የነርሱን አስተሳሰብ የማይቀበለውን ሙስሊም በኩፍርና በፊስቅ የሚወነጅሉ መሆናቸው ነው። እነዚህ ፊርቃዎች ራሳቸውን ችለው አዲስ ሐይማኖት መስርተናል ቢሉ አንድ ነገር ነው።(ለምሳሌ እንደ "ባሃኢ" እና እንደ "ዱሩዝ" አማኞች ማለት ነው)። ፊርቃዎቹ ግን ሙስሊም ነን እያሉ ሙስሊሞችን በኩፍር ይወነጅላሉ።

የዛሬው አህባሽም ከነርሱ ጋር ተመሳሳይ ነው። አንጃው ባለፉት አስር አመታት በሀገራችን መኖሩን እያወቅን ከተከታዮቹ ጋር አልተጋጨንም። ዛሬ ግን በአሜሪካ አጋፋሪነትና በኢትዮጵያ መንግስት አደፋፋሪነት የኔን እምነት ብቻ ተቀበሉን ሊለን ተነስቷል።

አህባሾች የዘነጉት ነገር በፖለቲካዊ ውሳኔ የሚካሄድ የማጥመቅ ዘመቻ የትም የማያደርሳቸው መሆኑን ነው። የጥንቱ ሙእተዚላ በባግዳድ ቤተ-መንግስት ባገኘው ጊዜያዊ የበላይነት ተደፋፍሮ "ቁርአን መኽሉቅ ነው" የሚለውን ፍልስፍና ለማስረጽ ቢሞክርም የትም አልደረሰም። በኋላ ፊርቃው ራሱን እንኳ መከላከል ሳይችል ነው ያጠፋው። አህባሾች ያገኙት ጊዜያዊ የመጅሊስ ድልም በነርሱ ላይ ጥላቻ እንዲጠናከር ከማድረጉ ውጪ ኢስላማዊውን ስነ-መለኮት የሚለውጡበት እድል ሊያሰጣቸው አይችልም። ምክንያቱም የኢስላም ጠባቂ እኛ ሳንሆን ፈጣሪያችን አላህ ነው።

ስለዚህ አህባሾች ቅጥፈቱንና በጊዜያዊ ወንበር መኩራራቱን ትተው ወደ ትክክለኛው ጎዳና እንዲመጡ በአላህ ስም እንጠይቃቸዋለን። በኢስላም ላይ ለሚያሴሩ ሀይሎች መሸቆጥቆጥ የአላህንና የመእሚኖችን ጥላቻ ከመጥራት ውጪ ምንም ፋይዳ የለውም።

**ክፍል አስራ ሰባት፡ አህባሽና የሙስሊሙ አንድነት**

በዚህ ክፍል አህባሽ አደጋ በደቀነበት የሙስሊሙ አንድነት ዙሪያ ቆይታ እናደርጋለን፡፡

***"አህሉ ሱንና ወል-ጀመዓ"***

እኛ ሙስሊሞች የምንከተለው ዲን (ሀይማኖት) ኢስላም ነው፡፡ ኢስላምን የሚከተል አንድ ግለሰብ "ሙስሊም" ነው፡፡ ሁሉም ሙስሊሞች አንድ ላይ "ኡማ" ይባላሉ፡፡ በሌላ በኩል እኛ አሁን ያለንበት መንገድ ጥንት ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እና ከሰሀባዎች ዘመን የተነሳው ቀጥተኛ ጎዳና መሆኑን ለማመልከት የሰለፍ ኡለማ "አህሉ ሱንና" (በሱንና ላይ ያሉ ህዝቦች) የሚል ቅጽል ሰጥተውናል፡፡ በተጨማሪም የአላህን ቀጥተኛ ገመድ የያዝንና በውስጣችንም ክፍፍል የሌለብን መሆኑን ለማስረዳት "አህሉል ጀመዓ" (በአንድነቱ የጸና ህዝብ) በማለት ጠርተውናል፡፡ ሁለቱ ስሞች አንድ ላይ በመጣመር ***"አህሉ ሱንና ወል-ጀመዓ"*** (በሱንና ላይ ያለውና ያልተከፋፈለው ህዝብ) የሚለውን መጠሪያችንን አስገኝተዋል፡፡

እኛ ሙስሊሞች "አህሉ ሱንና" ነን፡፡ እኛ ሙስሊሞች "አህሉል ጀመዓ" ነን፡፡ አንድነት የኛ መለያ ነው፡፡ አንድነታችን ጌጣችን ነው፡፡ አንድነታችን ክብራችን ነው፡፡ ኢስላምን በጠላቶቹ ፊት ክብር ያሰጠው የሙስሊሙ አንድነት ነው፡፡ የኢስላም ጠላቶች ከጦር በላይ የሚፈሩት መሳሪያ ቢኖር የሙስሊሙ አንድነት ነው፡፡

የዚህ ኡማ አንድነት በቀላል ልፋትና ትግል አይደለም እዚህ የደረሰው፡፡ በርካታ የ"ፊትና" ዘመናት ታልፈዋል፡፡ ሰሀባዎችና ተቢኢዮች በሺዓ እና በኸዋሪጃ ፊርቃዎች የተነጠሉትን ወገኖቻቸውን ወደ ኡማው ለመመለስ እልህ አስጨራሽ ትግል አድርገዋል፡፡ ኸሊፋዎችና ታላላቅ ኡለማዎች በየወቅቱ ይነሱ የነበሩትን የአመለካከት ልዩነቶች በዘዴ እየፈቱ የኡማውን አንድነት አስጠብቀዋል፡፡ አላህ እነዚያ ጥረቶችን ሰበብ ስላደረገ ነው አንድነታችን ተጠብቆ እዚህ የደረሰው፡፡

***የአመለካከት ልዩነት በራሱ መጥፎ አይደለም***

ኢስላም ህያው ሀይማኖት ነው፡፡ ህያው የሆነ እምነት በውስጡ የአመለካከት ልዩነቶች መታየታቸው አይቀርም፡፡ ልዩነት በራሱ መጥፎ አይደለም፡፡

የአመለካከት ልዩነት በመከሰቱ ብቻ የኡማውን አንድነት ይንደዋል ማለት አይደለም። እንዲያውም አላህ በልዩነት ውስጥ ለኢስላም ውበት የሰጡ በርካታ ጸጋዎችን አጎናጽፎናል። ለምሳሌ አራቱ የፊቅሂ መዝሀቦች ጸጋዎቻችን ናቸው። ሰባቱ የቂራአት (የቁርአን ንባብ ደንብ) መንገዶችም እንዲሁ የኢስላም ውበቶች ናቸው። እነዚህ ክስተቶች ጸጋዎቻችን ሊሆኑ የቻሉት ኡለማዎች የልዩነት መንገዶች ስላላደረጓቸው ነው። ልዩነቱን ያመጡት ቀዳሚ ሰዎች በአመለካከት የተለዩትን ሰው ወደ መዝለፍና ማጥላላት አልገቡም። "እኔ ያልኩት እንጂ ሌላው ትክክል አይደለም" በሚል ስሌት "ቡራ ከረዩ" አላሉም። በልዩነታቸው ውስጥ ይከባበሩ ነበር።

ለምሳሌ አቡ ሀኒፋ፤ ማሊክ ኢብን አነስ፤ ሙሀመድ ኢብን ኢድሪስ አል-ሻፊኢ፤ አህመድ ኢብን ሀንበል አንዳቸው ለአንዳቸው ተማሪና አስተማሪ ነበሩ። እነርሱ የነበራቸው የህግ አተረጓጎም ልዩነት ነው አሁን ያሉትን አራት መዝሀቦች ያስገኘው። ታዲያ እነዚህ ኡለማ በአመለካከት ቢለያዩም በጣም ይፈቃቀሩ ነበር። እኛም ዛሬ ያለነው ሙስሊሞች አራቱንም ኢማሞች በጣም ነው የምናከበራቸው።

ከዚህ እንደምትረዱት የአመለካከት ልዩነት ሁልጊዜ የጀመዓ መነጣጠልን የሚያስከትል ተደርጎ መታየት የለበትም። በቅን ልቦና ካየነው ልዩነት ተጨማሪ ጸጋዎችንም ሊያጎናጽፈን ይችላል።

### *ልዩነትን በጥበብ መያዝ*

ከላይ እንደገለጽኩት የአመለካከት ልዩነት በመፈጠሩ ብቻ ወደ መነጣጠል የሚወስድ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ከይሲዎችና ደካማዎች ግን መጠነኛ ልዩነቶችን እያገዘፉ ትልቅ የመገንጠል ገደል ይቆፍሩበታል። የኢስላም ታሪክ የሚያስረዳው ይህንኑ ነው። አላህ ቅን ልቦና የሰጣቸው አርቆ አስተዋዮች ግን በሃሳብ መለያየቱን ብቻ ሳይሆን መጠነ ሰፊ ልዩነት ለመፍጠር በሚችሉበት ሁኔታ ሲገኙ እንኳ ጥበባዊ ችሎታቸውን ያሳዩበታል። ለዚህም ሁለት ምሳሌዎችን ከታሪክ ልጥቀስ።

1. ዋሲል ኢብን አጣእ የታዋቂው ኢስላማዊ ምሁር የሐሰን አል-በስሪ ተማሪ ነበር። ታዲያ ይህ ሰው ከእለታት አንድ ቀን ከአስተማሪው ጋር ክርክር ይገጥማል። ክርክሩ የተነሳው "አንድ በአላህ የሚያምን ሰው ሀጢአት ቢሰራ ወደ ጀሀነም ይገባል ወይስ አይገባም?" በሚል ጥያቄ

ነው። መምህሩ "ሰውየው ኢማን እያለው ሀጢአት ቢሰራና ተውባ ሳያደርግ ቢሞት ለሰራው ሀጢአት በጀሀነም ይቀጣል። ነገር ግን ጀሀነም እንደገባ በዚያው አይቀርም። ቅጣቱን ሲጨርስ ወደ ጀነት ይገባል" በማለት ትክክለኛውን የ"አህሉ ሱንና" መልስ ሰጡት።

ዋሲል ግን "ይህማ አይሆንም፤ ሰውየው በጀሀነምና በጀነት መካከል የሚቆይበት ቦታ መኖር አለበት" በማለት አዲስ ሀሳብ ወለደ። አስተማሪው "እንዲህ አትበል" ቢሉትም "እንቢ" አለ። በዚያው ከርሳቸው "ደውር" (የመማሪያ ቦታ) ወጣ። ይህንን አመለካከት እርሶ በማድረግም "ሙእተዚላ" የተሰኘውን ጥንታዊ ፊርቃ ፈጠረ። ይህ ፊርቃ በመፈጠሩ ሙስሊሙ ኡማ ለአራት ምእተ አመታት ፍዳውን አየ። በኋላ ላይ ግን አላህ ፊርቃውን በራሱ ጥበብ አከሰመው።

2. ታዋቂው ጀግና ኻሊድ ኢብን አል-ወሊድ(ረ.ዐ) ስሙ በጠላቶቹ ፊት እየገነነ በሄደበት ዘመን አንዳንድ ሰሀባዎች ድል የሚያጎናጽፈው አላህ መሆኑን ዘነጉትና "ኻሊድ የሚመራው ጦር ሁሌ አሸናፊ ነው፤ እርሱ ባለበት ቦታ ድል አለ" የሚል አስተሳሰብ አመጡ። ታዲያ ኸሊፋ ዑመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ) ይህንን መጥፎ አመለካከት ለመስበር ፈለጉና ኻሊድን ከቦታው አንስተው አቡ ኡቤይዳ ኢብን ጀራህን (ረ.ዐ) መሾማቸውን የሚገልፅ ደብዳቤ ላኩለት።

ኻሊድ ደብዳቤው ሲደርሰው በልቡ ቅሬታ ቢገባውም የኸሊፋውን ትእዛዝ ለመፈፀም አላመነታም። በጊዜው የነበረበት አጣዳፊ ሁኔታ እስኪያልፍለት ድረስ በቦታው ላይ ቆየ። ከዚያም አዛዥነቱን ያለ አንዳች ክርክር ለአቡ ኡቤይዳ አስረክበና ተራ ወታደር ሆኖ መዋጋት ጀመረ። ሙስሊሞችም ያለ ኻሊድ መሪነት ድል አደረጉ። ኻሊድ ሁሉም ነገር ካበቃ በኋላ ወደ ኸሊፋው ዘንድ ሄደና "ምን ጥፋት ሰርቼ ነው የተሻርኩት?" በማለት ጠየቀ። ኸሊፋውም እውነተኛውን ምክንያት ነገሩት።

ኻሊድ በዚያን ጊዜ የኸሊፋውን ትእዛዝ አልቀበለም ቢል ምን ይፈጠር ኖሯል? ይህንን የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው። በአለም ታሪክ ከታዩት ክስተቶች ተነስቼ ግምቴን ብሰነዝር ግን ዛሬ የምንማረው የኢስላም ታሪክ በሌላ መልኩ የሚጻፍ ይመስለኛል። ባጭሩ "አንድ አደገኛ ፊርቃ ተፈጥሮ የሙስሊሙ ዓለም ይከፋፈል ነበር" ያሰኛል። አላህ እንኳንም አላደረገው! (ደግነቱ ሰውየው ኻሊድ ነው! የአላህ ሰይፍ! እንደ ዋሲል ኢብን አጣ ያለ ተልካሻ ፍጡር አይደለም)።

ከካሊድ ታሪክ እንምንረዳው ቅሬታ ሲሰማን የመስሊሙን ኡማ ለክፍፍል የሚዳርጉ እርምጃዎችን መውሰድ የለብንም። ቅሬታ፤ ልዩነት፤ አለመግባባት ካለ በጥበብ መያዝና መፍታት ይገባል።

## *የአህባሽ የስንጠቃ ጥረት እንዳይሰምርለት*

አህባሽ በመሰረቱ "ቀሽም" ፊርቃ ነው። የእምነት ፍልስፍናውም ሆነ አካሄዱ ጤናማ አእምሮ ያለውን ሙስሊም የመሳብ ሀይል የላቸውም። አንጃው በሺህ ተከታዮች ብቻ የተገደበው ሀቅን ባለመያዙ ብቻ ሳይሆን ፍልስፍናውን የማስረዳት ብቃትም ስለሌለው ነው። ዛሬ በሀገር አቀፍ ደረጃ መነጋገሪያ የሆነበት ምክንያት ከጀርባው ያሉ ሐይሎች "እርሱ ይምራችሁ! እርሱ የሚያስተምረውን ፍልስፍና ብቻ ተከተሉ" የሚል አስገዳጅ አካሄድ በመጀመራቸው ነው።

"አህባሽ" ፍላጎቱ እንደማይሰምርለት እራሱ አበጥሮ ያውቃል። እስከዛሬ ድረስ ራሱን ከሌሎች ሲያሸሽ የኖረበት ምክንያትም ይኸው ነው። በዚህ በኩል ስጋት የለብንም። አህባሽ የኛ ስጋት የሚሆነው ግን እርሱ የሚሰነዝራቸው የማታለያ ዘዴዎች፤ ከልክ በላይ የሚደጋግማቸው የማዘናጊያ አመለካከቶች፤ ሆን ብሎ የሚወረውራቸው የማጭበርበሪያ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ወዘተ.. በኛ ውስጥ ገብተው የልዩነት መስመር ማበጀት ከቻሉ ብቻ ነው። ባጭሩ አህባሽ በየትም የትም እያለ አንድነታችንን መሰነጣጠቅ ሲችል ፍላጎቱ ሰመረለት ማለት ነው። ስለዚህ የኡማውን ህብረት የሚንድበት ቀዳዳ እንዳያገኝ በንቃት መጠበቅ ይጠበቅብናል።

ከታሪክ ምእራፎች እንደምንረዳው ይህ ኡማ አንድነቱን ካጠበቀ ሁሌም ድል ያደርጋል። አንድነቱን ሲያላላ ግን ጠላቶቹ ይበረክታሉ። አህባሽም የጠላቶቻችን ፊት አውራሪ ሆኖ ለዘመቻ የመጣው በጠባቂዎቹ ጉልበት ስለተማመነ ብቻ ሳይሆን "አንድነት የላቸውም" የሚል ተስፋ ስለያዘ ነው።

ስለዚህ ያ ጀመዓ! አህባሽ ወሀቢ የሚለው "አላህ ከአርሽ በላይ ነው" ያለውን ሰው ብቻ አይደለም። "ካፊር!" በማለት የፈረጃቸው ኡለማ በአንድ መዝሐብ ብቻ የታቀፉ አይደሉም። ከዚህ ቀደም እንዳስረዳሁት አህባሽ እርሱን የማይቀበሉትን ሙስሊሞች በሙሉ "ወሃቢ ናችሁ" ነው የሚለው። የተለያዩ ሰበቦችን እየፈጠረ "ተክፊር" ማወጁም ልማዱ ነው። ይህ ክፉ ቡድን የደቀነብንን አደጋ በእንጭጩ ለመቅጨት የምንችለው በአንድነት ስንቆም

ነው።።

አህባሽና ጀሌዎቹ ትላንት "ኸዋሪጃ" እያሉ ሲዘምሩ አንዳልነበረ ሁሉ ዛሬ "ኸዋሪጃ የለም አክራሪ የተባለ በሙሉ ወሃቢያ ነው" የሚል መፈክር አምጥተዋል።። ዛሬ "ወሀቢ" የሚለው ቅኝት ነገ ተቀይሮ "ኢኽዋን" የሚል መዝሙር የማይጀመርበት ምክንያት የለም።። ተነገ ወዲያ ደግሞ "ተብሊግ ጠላታችን ነው" ይባል ይሆናል።። ከዚያ በማስከተልም "ሱፊዎች ካፊሮች ናቸው"! ከዚያ በክልልና በብሄረሰብ ላለመምጣታቸው ምንም ዋስትና የለንም።። ዋስትናችን አላህ ብቻ ነው!

ስለዚህ መፈራረጅ፤ መጠላለፍ፤ መሻኮት፤ ወዘተ... ይቅርብን።። ሁሉም የጋራ ህብረት ይፍጠር።። ይህንን የፈተና ጊዜ ህብረታችንን የምናጠናክርበት አጋጣሚ እናድርገው።። እስከዛሬ ላጠፋነውም ተውባ እናድርግ! ሁላችንም ሙስሊሞች ነን!! አላህ በኢስላም ላይ ያጽናን።። ዲናችንን ከጠላቶቹ ይጠብቀው።። የነቢዩን ሱንና በጥበቡ ይጠብቀው።። በነገዋ እለት በርሱ ፊት ከሚዋረዱት አያድርገን።። አንድነታችንን ያጠናክርልን!

የአላህ ሰላምና የአክብሮት እዝነት በነቢዩ፤ በቤተሰቦቻቸው፤ በሰሀባዎቻቸው፤ የአህሉስ ሱንናን መንገድ ለመጠበቅ በጉልበታቸው፤ በእውቀታቸውና በሀብታቸው በታገሉ የአላህ ወዳጆችና የነርሱን ፈለግ በተከተሉት ሙእሚኖች ላይ ይስፈን።። አሚን!! ወሰላሙ አለይኩም ወራሕመቱላሂ ወበረካቱህ!!

(ተፈፀመ)